# ሐመር

## ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ

4ኛ ዓመት ቁጥር 1

ሚያዝያ 1988



አንደራቻ መድኃኔ ዓለም ቤተክርስቲያን


### ኒቆዲሞስ

ዮሐ.3፥2

ወርቅነሽ ቱፋ

ፈሪሳዊው እውቅ መምህር
ሊቅ አልነበርክ ያገር ክብር?
የምርጥ ምርጥ ከእውቅም እውቅ
ነበርክ እኮ የአይሁድ ሊቅ
ግና–ሕግ አዋቂ ነህ መባሉ
መምህር ነው ቢልህ ሁሉ
የውስጥህን ስታይ ገልጠህ
ሚዛን ባይደፋ እውቀትህ
የሰው ሙገሳ ድለላ
ውስጠ ባዶህን ባይሞላ
አስገራሚው ድብቅ ጉዞህ
ከቀን ለሊት አስመርጦህ
ወደጌታ መገስገስህ
ሊቅ ስትባል መጠየቅህ
ሕይወት አሲዞ መለሰህ።

የሽፋን ስዕል
ቱሪዝም ኮሚሽን



የአቡነ ይምዓታ ቤተክርስቲያን የጣራ ላይ ሥዕል

©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

# ከአንባቢያን ለአንባቢያን

## ሥርዓት ይከበር

በአሁኑ ጊዜ በአንዳንድ በተለይም የቱሪስቶች መስህብ በሆኑት እንደ ቅዱስ ላሊበላ ባሉት አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት ሥርዓት እየተፋለሰ ይገኛል። ይኸውም ሥርዓተ ቅዳሴ በሚፈፀምበት ወቅት ብዙ ምእመናንና ካህናት ቤተ መቅደስ ውስጥ በተመስጦ ሲጸልዩ የውጭ አገር ዜጎችና አንዳንድ ደንታ ቢስ ኢትዮጵያውያን እንዳሻቸው ወደ ቤተ መቅደሱ በመግባትና በመውጣት እንዲሁም ወዲያ ወዲህ በመዘዋወር ይረብሻሉ። ስለዚህ ለእነዚህ ሰዎች አስፈላጊው ትምህርት (መመሪያ) ተሰጥቶ ጸሎተ ሥርዓቱ እንዲከበር፣ ጐብኝዎችም ሙሉ ሥርዓቱን ጭምር ተመልክተው እንዲሄዱ ቢደረግ መልካም ነው።

ተጠምቀ ገ/ሕይወት – ከላሊበላ

## ☞ ስምዐ ጽድቅ

### ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ

እግዚአብሔር አምላክ የሠራቸውን ድንቅ ገቢረ ተአምራት፣ በዘመናችን ለተነሡ የኑፋቄ ትምህርቶች መልስ፣ በክርስቲያናዊ ሕይወት ለሚገጥሙ ችግሮች መፍትሔ እና የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርትን በሰፊው የያዘች ጋዜጣ ናትና አታምልጥዎት። በሀገር ውስጥም ሆነ ከሀገር ውጭ ላሉ አንባብያን ለማዳረስ ተዘጋጅተናል።

| ለደንበኝነት | | |
|---|---|---|
| ለክፍለ ሀገር | የዓመት | 15.00 |
| | የ6 ወር | 7.50 |
| ለአዲስ አበባ | የዓመት | 14.40 |
| | የ6 ወር | 7.20 |
| ከሀገር ውጪ | የዓመት | 12 ዶላር |
| | የ6 ወር | 6 ዶላር |

አድራሻዎንና የከፈሉበትን በፖ.ሣ.ቁ. 80078 ይላኩልን።
ለወ/ት ዓይናለም ታዬ ደመቀ
4 ኪሎ ባንክ ቅርንጫፍ – የሂሳብ ቁጥር 79808
ፖ.ሣ.ቁ.80078
ስልክ 55–00–99 Exe 46

## ሥነ ግጥም

ርቀን ከቆምን – ከተዋሕዶ አምባ፣
ምግባረ ኀዶሉ – እንዳንሆን ገለባ፣
ለማይበጀን ዓለም – ጭራሽ ለማይረባ፣
በማይሆነን ሁሉ – ስንል ወጣ ገባ፣
ያቺ ቀን ሳትመጣ – ሣናውቅ እንደሌባ፣
ተዘጋጅተን እንኑር – ንስሐም እንግባ።

ገብረየስ ገቢቶ
(ቦንጋ)

## ይታረም

አልፎ አልፎ፥ በሰንበት ትምህርት ቤቶችና በሠርከ ጉባዔያት አንድ እየተለመደ ያለ፣ ነገር ግን ስህተት የሆነ አባባል አለ። ይኸውም የጉባዔው መሪ ለዕለቱ አስተማሪ ወይም ሥነ–ጽሑፍ (ድራማ) አቅራቢ፣ ዘማሪ፣ ወዘተ. መድረኩን (አውደ ምሕረቱን) በሚለቅበት ሰዓት «አሁን መድረኩን ለእገሌና ለመንፈስ ቅዱስ እለቃ ለሁ» ይላል። የመንፈስ ቅዱስን ቦታ የሚያዝና የመልቀቅ ሥል ጣን ያለው ወይም በተቃራኒው እርሱ ያለ መንፈስ ቅዱስ መሪነት ጉባዔውን የሚ መራ ያስመ ስልበታልና ቢታረም መልካም ነው።

ጌታመሣይ ተንኮሉ
(ቱሉቦሉ)

## ከባለቅኔው

ሥጋህን በልቼ ደምህን ጠጥቼ
ሲያል ብታወርደኝ፣
አብረን እንወርዳለን
እኔን ምን ቸገረኝ።

©ማኅበረ ቅዱሳን 

# ሐመር

4ኛ ዓመት ቁ.1

አራተኛ ዓመት ቁጥር አንድ

ሚያዚያ – 1988 ዓ.ም


## ይዘት


ከአዘጋጁ . . . . . . . . . . . . . 1

የማኅበሩ መልእክት . . . . . 2

ደብዳቤዎች . . . . . . . . . . . 3

ከሰሞኑ በረከት

✣ ጾም– የጽድቅ በር . . . . . . . 5

ትምህርተ ሃይማኖት

✣ ምሥጢረ ቁርባን . . . . . . . 7

✣ የእግዚአብሔር ሕግ . . . . 10

ኪነጥበብ

✣ ሶልያና . . . . . . . . . . . . . 13

እናስተዋውቃችሁ

✣ አንደራቻ መድኃኔዓለም ገዳም . . . . 14

✣ የአቡነ ይምዓታ ቤተ ክርስቲያን . . . . 16

✣ አፌን በምሳሌ እከፍታለሁ . . . 17

ዓምደ ወራዙት

✣ ንስሐ–ለምንና እንዴት? . . . . . 18

✣ በጸጋው መዳን እንዴት ነው? . 21

✣ ደካማ ጎንን እንዴት ማሸነፍ ይቻላል? . . . . . . . . . 23

ክርስትና በማኅበራዊ ኑሮ

✣ ሰው እግዚአብሔርን ይሰርቃልን? . . 24

✣ አዲስ ኪዳን – በብሉይ ኪዳን . . . . . 25

✣ ጥያቄዎቻችሁ . . . . . . . 26

ቤተ ክርስቲያንህን ዕወቅ

✣ የንዋየ ቅድሳት ዝርፊያ– ከትናንት እስከ ዛሬ . . . . . . . . . 27

✣ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ . . . . . 29



በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የሰንበት ት/ቤቶች ማስተባበሪያ መምሪያ በማኅበረ ቅዱሳን የመዝሙርና ሥነ ጽሑፍ ክፍል የሚዘጋጅ ትምህርታዊ መጽሔት።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያንን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓትና ትውፊት ጠብቆ የሚወጣ።


# ከአዘጋጁ

## እንኳን አደረሳችሁ!

በስመአብ ወወልድ፣ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ– አሜን።

ላለፉት ሦስት ዓመታት ሐመር መጽሔታችን ምግበ ነፍስ ለምእመናን ስታቀብል ቆይታለች። በቤተ ክርስቲያናችን አንዣብቦ ከነበረው የመናፍቃኑ የተሐድሶ እንቅስቃሴን ከማጋለጥ ጀምሮ በትምህርተ ሃይማኖት ዙሪያ ለሚነሱ ጥያቄዎች መልስ መስጠትን ጨምሮ በማኅበራዊ ኑሮ የሚገጥሙ ችግሮችን መፍትሔ በማፈላለጉ ስትደክም ሰንብታለች።

በአራተኛ ዓመቷም ይህንኑ በማጠናከር ለመቀጠል አቅዳለች። ለዚህም የአንባብያን ተሳትፎ ወሳኝ ነውና በርታ እንበል። መጽሔቷ– መጽሔታችን፣ የጋራ የሥራችን ውጤት ናትና– አስተያየት በመስጠት፣ መጣጥፎችን በማበርከት፣ ማቴሪያል በመረዳት፣ በጸሎት በማሰብ መልካም ሥራን እንሥራ።

የአራተኛውን ዓመት እትምም አሐዱ የምንለው የተለመደውን መንፈሳዊ ማዕድ በማቅረብ ነው።

እነሆ...

ወለእግዚአብሔር ስብሐት


ዋና አዘጋጅ – ብርሃኑ ጎበና ካሣ

ም/ዋና አዘጋጅ – ዲ.ደጀኔ ሺፈራው

ስልክ – 550099 Ext. 46

ፖስታ – 80078

አዲስ አበባ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# የማኅበሩ መልእክት

## ሰንበት ትምህርት ቤት – የአባቶችን አደራ መቀበያ

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን።

ዕለተ ሰንበት መልካም ሥራ የሚሠራባት፣ ምእመናን ዕድሜና ጾታ ሳይለዩ ወደ ቤተክርስቲያን በመሄድ በአንድነት ተሰብስበው ለእግዚአብሔር ምሥጋናና ልመና የሚያቀርቡባት ለመንፈሳዊ ሕይወት የሚሆን በጐ ሥራ የሚሠሩባት የተቀደሰች ዕለት ናት።

በዚህች ዕለት ወላጆች ልጆቻቸው ከሕፃንነት ዘመናቸው ጀምሮ የእግዚአብሔር በረከት ተካፋዮች እንዲሆኑ፣ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንንም እንዲያውቁ፣ ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን እየተቀበሉ፣ ጸበሉን እየጠጡ፣ በክቡር መስቀሉ እየተዳሰሱና እየተፈወሱ እንዲያድጉ እያደረጉ ይገኛሉ። ይህም «እናንተ አባቶች ሆይ ልጆቻችሁን በጌታ ምክርና ተግሣጽ አሳድጓቸው።» ኤፌ.6፥4 ብሎ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ያዘዘውን መሠረት ያደረገ ነው።

ልጆችም በየአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናቸው በተቋቋሙት የሰንበት ትምህርት ቤቶች እየተገኙ የቤተ ክርስቲያንን እምነት፣ ሥርዓትና ትውፊት በመማር መንፈሳዊ ሕይወታቸውን አንጸው ባላቸው ተሰጥኦም ቤተ ክርስቲያናቸውን በልዩ ልዩ መንገድ ሲያገለግሉ ማየት እግዚአብሔር ትውልዱ የአባቶቹን መልካም ፈለግ እንዲከተል እያነቃቃው መሆኑን ያስገነዝበናል።

በአንጻሩ አንዳንድ ወላጆች ደግሞ ሕፃናት ወደ እኔ ይመጡ ዘንድ አትከልክሏቸው የሚለውን አምላካዊ ቃል በመዘንጋት በሥጋዊ ትምህርት ቤት ብቻ ልጆቻቸው እንዲማሩ ለማድረግ በየትምህርት ቤቱ ለማስመዝገብ ዘመድ በመፈለግ፣ ስጦታ በማቅረብ ሲወጡ ሲወርዱ የዘለዓለማዊ ሕይወት መገኛ ወደ ሆነው የቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሰንበት ትምህርት ቤት ልጆቻቸው እንዲገቡ ግን ምንም ጥረት ካለማድረጋቸውም በላይ በራሳቸው ፍላጐት የሚሄዱትንም ሲከለክሉ ይታያሉ።

በሌላም በኩል ሰንበት ትምህርት ቤት የዕድሜ ገደብ ሳይደረግበት ክርስቲያን ሁሉ የሃይማኖቱን ትምህርት የሚማርበት ሆኖ ሳለ አብዛኛው ምእመን ግን የሕፃናትና የወጣቶች ብቻ እየመሰለው ከቤተ ክርስቲያን ትምህርት ርቆ ይገኛል።

ስለዚህ እያንዳንዱ ምእመን ሕይወትን የሚያለመልመውን ቃለ እግዚአብሔር ቢቻል በየዕለቱ አሊያም ቢያንስ የክርስቲያኖች የዕረፍት ቀን በሆነችው ዕለተ ሰንበት በየአጥቢያ ቤተ ክርስቲያኑ ሰንበት ትምህርት ቤት ተመዝግቦ መማር ያስፈልገዋል። ለዚህም የእያንዳንዱ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ኃላፊዎች ለምእመናን በጊዜ፣ በቦታና በዕድሜ ደረጃቸው የተከፈለ መርሐ ግብር በማዘጋጀት እምነታቸውንና ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያናቸውን አውቀው የእግዚአብሔር በረከት ተካፋዮች ይሆኑ ዘንድ ሁኔታዎችን የማመቻቸት አባታዊ አደራ አለባቸው።

በየሰንበት ትምህርት ቤቱ የሚማሩ ወጣቶችም የልጅነትና የወጣትነት ስሜታቸውን በመቆጣጠር የቀጥተኛይቱን ቤተ ክርስቲያን መሠረታዊ የሃይማኖት ትምህርት ለማወቅ «አባትህን ጠይቅ ያስታውቅህማል ሽማግሌዎችን ጠይቅ ይነግሩህማል» ዘዳ.32፥7 ተብሎ እንደ ተጻፈ ወደ ቤተ ክርስቲያን አባቶችና ሊቃውንት ቀርቦ በመማር በክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር በመታነፅ ተተኪ ትውልድ መሆናቸውን ማስመስከር ይጠበቅባቸዋል።

የቤተ ክርስቲያናችን አባቶች፣ ሊቃውንት፣ የሰበካ ጉባኤ አመራር አካላትም ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለቅዱስ ጴጥሮስ «ግልገሎቼን አሰማራ፣ ጠቦቶቼን ጠብቅ በጐቼን አሰማራ» ዮሐ.21፥15 ብሎ የሰጠውን አደራ መሠረት በማድረግ የእነዚህ ወጣቶች ጉዞ መልካም ፍፃሜ እንዲኖረው በየሰንበት ትምህርት ቤቱ በቅርቡ እየተገኙ የማስተማር፣ የማጠናከርና የማበረታታት ኃላፊነት አለባቸው።

ቃለ እግዚአብሔርን መማርም ሆነ ቤተ ክርስቲያንን ማገልገል በተወሰነ ጊዜ ብቻ ተከናውኖ ቢቃኝ የሚባል አይደለም። የሰው ልጅ በአካለ ሥጋ እንዲኖር በየዕለቱ ምግብና መጠጥ እንደሚያስፈልገው ሁሉ መንፈሳዊ ሕይወቱም እንዲጠበቅና የሰይጣንን ፈተና ለመቋቋም ሁል ጊዜ ወደ ቤተ ክርስቲያን መሄድና ምግበ ነፍስ የሆነውን ቃለ እግዚአብሔርን መመገብ ያስፈልገዋል። ለዚህም ነው መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም» በማለት ያስተማረን። ማቴ.4፥4።

በአጠቃላይ የሰንበት ትምህርት ቤቶች የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ማዕከላት ስለሆኑ የቤተ ክርስቲያን አባቶችና ሊቃውንት ሊያጠናክሯቸው የሰንበት ትምህርት ቤት አባላትም እርስ በርስ በመተሳሰብ በመመካከርና በመማማር ችግር የሚፈጥሩ አዝማሚያዎችን ማስወገድ ይገባቸዋል። ጥንተ ጠላታችን ሰይጣን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የሰንበት ትምህርት ቤት መርሐ ግብሮችን በማዳከም፣ ልዩነቶችን በመፍጠር፣ ምእመናንን ከቤተ ክርስቲያን በማስኰብለል በየመንደሩ ለማስቀረት ዘወትር የሚጥር መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። በመሆኑም የሰንበት ትምህርት ቤት አመራር አባላት መርሐ ግብሮች አባላቱን በአግባቡ የሚይዙ፣ የሚያስተምሩና የሚያሳትፉ ማድረግና የመለያያ ምክንያቶችንም ማጥፋት ይጠበቅባቸዋል።

ማኅበረ ቅዱሳንም ዓላማው ሰንበት ትምህርት ቤቶችና ሰበካ ጉባዔያት ተጠናክረው ምዕመናን የቤተ ክርስቲያን ጸጋ ተካፋዮች እንዲሆኑና ከእነርሱም የሚጠበቀውን አገልግሎት እንዲያበረክቱ የበኩሉን ጥረትና ድጋፍ ማድረግ በመሆኑ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሚቻለውን ሁሉ ያደርጋል።

የእግዚአብሔር ቸርነት የድንግል ማርያም ምልጃ አይለየን።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ደብዳቤዎች

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን።

## የምትናገሩትን ሁኑ

በቅድሚያ መጽሔቷ እንድትዘጋጅ ያነሣሣችሁ እግዚአብሔር አምላክ ይክበር ይመስገን። ጅምራችሁ በጣም የሚያስደስት በመሆኑ እስከ መጨረሻው ልትበረቱ ይገባል። በተለይ በትምህርታችሁ ለምትወልዷቸው የመንፈስ ልጆቻችሁ ምሳሌ ልትሆኑ ያስፈልጋል። ክርስቲያን በኑሮው፣ በሥራው፣ በአገልግሎቱ ሁሉ ፈተና ይኖርበታል። ቢሆንም በእግዚአብሔር ቸርነት ሁሉን እንደ አመጣጡ እየመለሳችሁ ተጋድሎአችሁን ፈጽሙ፤ የምትናገሩትንም ሁኑ። ንግግራችሁና ተግባራችሁ አንድ ከሆነ ፍሬ ማፍራት ትችላላችሁ። ለዚህም የመድኃኔዓለም ቸርነት የድንግል እናቱ ምልጃ አይለያችሁ።

(ማርታ ብርሃኑ — ያቤሎ)

ከአዘጋጁ — እህታችን ስለሰጡን አስተያየት ከልብ እናመሰግናለን። ዘርዝረው በሰፊው ያቀረቡልንን ሌሎች አስተያየቶችንም ተቀብለናል። የሚታረመውን እናርማለን። ጥያቄዎንም በግል አድራሻዎ እንመልስልዎታለን። በተሳትፎዎ ይግፉበት።

✣ ✣ ✣

## ታሪካቸውን ጻፉልን

የምታወጧቸው ጽሑፎች በጣም የሚያስደስቱና በተለይም መንፈሳዊ ሕይወትን ጀማሪ ለሆነው ወጣት ከፍተኛ ትምህርት ይሰጣሉ። በዚሁ ቀጥሉ። በተረፈ ባለፈው ወደ ደብረ ሊባኖስ ሄጄ ነበር። በዚያ አካባቢ የአባታችን አቡነ ሀብተማርያም ገዳም አለ። እኚህ አባት ለአብዛኛው ሕዝብ በተለይም እኔ ባለሁበት አካባቢ አይታወቁምና እባካችሁ በመጽሔቱ ገድላቸውንና ፎቶግራፋቸውን አውጡልን።

ዲ.በለጠ ኃ/ማርያም— አርሲ በቆጂ

ከአዘጋጁ — ስለአስተያየትዎ እግዚአብሔር ይስጥልን። የአባታችን አቡነ ሀብተማርያምን ታሪክ ወደፊት እናወጣለን። በዚህ አጋጣሚ ገድላቸውን በመስጠት የሚተባበረን ካለ በደስታ እንቀበላለን።

## ለአንድ ነፍስ እንደምትጨነቁ ተረድቼያለሁ

በቅድሚያ በልዑል እግዚአብሔር ስም ሰላም እያልኩ በመቀጠል ስለ ሐመር የተሰማኝን እገልፃለሁ። በ3ኛ ዓመት ቁጥር 3 እትማችሁ ላይ ለሰ.ወ. (ከአቴንስ ግሪክ) የሰጣችሁት መልስ ልቤን ነክቶኛል። ምን ያህልም ለአንድ ነፍስ እንደምትጨነቁ ተረድቼአለሁ። ሌላው የማኅበሩን መልእክት ሰፋ አድርጉት፤ ወቅታዊ የሆኑ ማስጠንቀቂያዎች ይሰጡበታልና። የኪነ ጥበብ አዘጋጁንም ለምን ታስጨንቀናለህ? ያለበለዚያ መጥተን ድርሰቶችህን እንዳንወስድብህ በሉልን። ለሁሉም የእግዚአብሔር ቸርነት የእመቤታችን ጸሎት የቅዱሳን ምልጃ ከእናንተ ጋር ይሁን።

(መ/ር ክፍሌ ጌታሁን— ጊምቦ ገ/መንፈስ ቅዱስ ሰንበት ት/ቤት/)

ከአዘጋጁ — አሜን። ስለሰጡን አስተያየት ከልብ እናመሰግናለን። ለኪነ ጥበብ አዘጋጅ መልእክቶን አድርሰናል። በተሳትፎዎ አይለዩን። በጸሎትዎም ያስቡን።

✣ ✣ ✣

## የአቡነ ሐራን ታሪክ ጻፉልን

ለሐመር መጽሔት አዘጋጆች

በኃያሉ ልዑል እግዚአብሔር ስም ሰላምታዬን አቀርባለሁ። ያለሁበት አካባቢ አቡነ ሐራ ድንግል የሚባል ቤተ ክርስቲያን አለ። ይሁን እንጂ ይህ በጻድቁ አባታችን አቡነ ሐራ ድንግል ስም የተሰየመው ቤተ ክርስቲያናችን ስለ ጻድቁ ገድልና ያከናወኗቸውን ታላላቅ ሥራዎች የሚገልጽ (የሚያስተምር) ምንም ዓይነት መረጃ የለውም። በመሆኑም የአካባቢው ክርስቲያን ማወቅ የሚገባውን ትልቅ ሀብት አያውቅም። ስለዚህ እባካችሁ ስለ ጻድቁ አባታችን ብላችሁ ትክክለኛውን ታሪካቸውንና ገድላቸውን በመጽሔታችሁ አሳውቁን ወይም በአድራሻችን ላኩልን።

እንዳለ ለማ ደምሴ

ከጌጫ አቡነ ሐራ ድንግል ሰ/ት/ቤት

(ከፍቾ—ሸኪቾ ኮን—ጌጫ)

ከአዘጋጁ — ወደ ፊት በእናስተዋውቃችሁ ዓምድ ሥር እናወጣለን፤ እስከዚያው በትዕግሥት ይጠብቁን። በዚህ አጋጣሚ የጻድቁ አባታችን የአቡነ ሐራ ድንግልን ታሪክ የምታገኙ ካላችሁ ብትልኩልን በደስታ እንቀበላለን። እናንተም ከበረከቱ ተካፋዮች ትሆናላችሁ።

✣ ✣ ✣

## ምንጩ ይጠቀስ!

በመጀመሪያ የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና በረከት የእናታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ጸሎትና ምልጃ አይለያችሁ።

አስቀድመው ለክብር የበቁትን ቅዱሳን ገድላት (ታሪክ) ለተተኪው ትውልድ በማስተላለፍ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ብዙ አከናውናለች። እያከናወነችም ትገኛለች። እናንተም በሐመር መጽሔት የምታወጧቸው ገድላትና ታሪኮች አስተማሪና ብዙ የሚያሳውቁን ሆነው እያለ ዋቢ መጻሕፍትንና አስፈላጊውን መረጃዎች ባለመጥቀሳችሁ መናፍቃን ገድላቱን ባለመቀበል በማንቋሸሽ እና በማጥላላት ላይ ይገኛሉ። ስለዚህ የሚቃወመንን የሰይጣን መንፈስ ለማሳፈርና የበለጠ ለማስተማር የምታቀርቧቸው ማናቸውም ገድላትና ተአምራት በዋቤ መጻሕፍትና ቢቻል በዓመተ ምኅረት ተደግፈው ቢቀርቡ መልካም ነው።

(ወንድማችሁ ታደሰ ኢማም ከከፋ—ትንሹ ጌሻ)

ከአዘጋጁ — ስለአስተያየትዎ እግዚአብሔር ይስጥልን። የሚቻለንን ሁሉ ለማድረግ እንጥራለን። እርስዎም በተሳትፎዎ አይለዩን።

✣ ✣ ✣

## ሥራ የሌላቸውን አጽናኑ!

ካለሁበት ሰላምታዬ ይድረሳችሁ እያልኩ አጭር አስተያየቴን እሰጣለሁ። አልፎ አልፎ በመጽሔቱ ውስጥ የቃላት መደጋገም ይታያልና እንዳያስለች እርማቱ ላይ ተጠንቀቃችሁ ብትሠሩ መልካም ነው። ሌላው ደግሞ ትምህርት ጨርሰው ሥራ አጥተው



©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

የተቀመጡ ብዙ ክርስቲያኖች አሉ። አብዛኛውን ጊዜ ግን በመጽሔቱ ዶ/ር፤ ነርስ፤ ወዘተ ወይም ተአምር የተደረገላቸውን ሰዎች ታሪክ ነው የምናነበው። ስለዚህ የእነዚህን ሥራ አጦች ሕይወት የሚዳስሱና የሚያጽናኑ ጽሑፎች ብታስነብቡን መልካም ነው። ምክንያቱም እንደዚህ ያሉ ወጣቶች ቤተ ክርስቲያን ሲያዘወትሩም ሆነ ሲያገለግሉ ሥራ ስለሌላቸው ብቻ እንደሚሄዱ ተደርገው ይታያሉና።

(ፍቃዱ ማሞ– ጅማ)

ከአዘጋጁ – አስተያየትዎን በደስታ ተቀብለናል። ሁለተኛውን አስተያየትዎን ግን ይህን ያህል እርስዎ እንዳሉት ወደ አንድ ወገን ያዳላን አልመሰለንም። ለማንኛውም መጽሔቷ በተቻለ መጠን ሁሉንም ክርስቲያን የምታስደስትና የምታጽናና እንድትሆን የበኩላችንን እንጥራለን። ለዚህ ደግሞ የእናንተ የአንባቢዎች ጸሎትና ተሳትፎ ያስፈልገናልና አትለዩን።

✣ ✣ ✣

## ዶ/ር አይዳ ግርማን አመስግኑልኝ

ባለፈው በ3ኛ ዓመት ቁጥር 3 እትም ላይ ከዶ/ር አይዳ ግርማ ጋር የተደረገው ቃለ ምልልስ በጣም አስደስቶኛል። ያነሣችውና ወደፊት ለቤተ ክርስቲያን ያሰበችው ሃሳብ የተቀደሰ ሃሳብ ነውና ሁላችንም የተቻለንን ብናደርግ እና ዓላማዋ ከግቡ እንዲደርስ ብንጥር መልካም ነው። ለሁሉም ረድኤተ እግዚአብሔር አይለየን።

ገብረ ትንሣኤ ይልማ
ከሻኪሶ ቅ/ማርያም ቤተ ክርስቲያን
(በድሉ ካሣ– ሚዛን ተፈሪ)

ከአዘጋጁ – አሜን። መልእክታችሁን እኛም ተቀብለናል፤ ለአንባቢዎችም አስተላልፈናል።

✣ ✣ ✣

## ሁለት ዓመት ወስዶብኛል!

ባለፈው መጽሔታችሁ የክርስትና በማኅበራዊ ኑሮ ዓምድ (በገጽ 22) ላይ አንድ ወንድሜ ‹የምኞትን ጾር› በጾምም ለማስወገድ ሞክሬ አልቻልኩም» ላልከው እኔም ከአንተ የባሰ ችግር ነበረብኝ፤ በብልሃት አልሆን ሲለኝ በጾምና በጸሎት በቅዱስ ዑራኤል አማላጅነት ነው እግዚአብሔር ያስወገደልኝ። ስለዚህ በርቷ፤ እኔ ከሁለት ዓመት በላይ ወስዶብኛል፤ አንተስ ለመሆኑ ምን ያህል ሞከረሃል? ሳትሰለች ትጋ። እግዚአብሔር ይርዳህ።

(ወልደሚካኤል– አ.አ)

ከአዘጋጁ – የክርስትናን ሕይወት መጻሕፍትን ብቻ ያነበበ ሳይሆን የኖረው ቢናገረው ያምራል። እናም ወንድማችን የምኞትን ጾር እንዴት ማሸነፍ እንደምንችል የመከሩን ለጠያቂው ወንድም ብቻ ሳይሆን ለሁላችንም ይሆናል እና ልንጠቀምበት ያስፈልጋል። የቀረውንም አስተያየትዎን የዝግጅት ክፍሉ ይጠቀምበታል። ስለ አስተውሎትዎና ምክርዎ እናመሰግናለን። እንደዚሁ በየጊዜው ያርሙን ይምከሩን።

✣ ✣ ✣

## ይልመድባችሁ!

ሰላመ እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ይሁን። በሐመር 3ኛ ዓመት ቁጥር 4 ላይ «ንዝህላልነት እና ቸልተኝነት በክርስትና ሕይወት» በሚለው ርዕስ ስር የተፃፉት ቁም ነገሮች እጅግ በጣም አስደስተውኛል። ምክንያቱም እያንዳንዱ ሰው እኔ ከየትኛው ወገን ነኝ ብሎ ራሱን እንዲጠይቅ የሚያደርግ ነውና። በየጊዜው እንዲህ ዓይነት ጽሑፍ መጻፍ ይልመድባችሁ።

(ሰሎሞን ወርቁ– ከናዝሬት)

ከአዘጋጁ – ወንድማችን እርስዎም የጐደለውን ማረሙና ጠቃሚ የሆነ አስተያየት መስጠቱ ይልመድብዎት።

✣ ✣ ✣

## የትኛውን እንቀበል?

በ3ኛ ዓመት ቁ.4 ኅዳር 1988 ዓ.ም መጽሔታችሁ ማኅበረ ቅዱሳን ባዘጋጀው የአዲስ ዓመት ካርድ ላይ የጾመ ነቢያት መግቢያ በኅዳር 15 ነው ተብሎ እንዲስተካከል ያስተላለፈውን እርምት አንብቤዋለሁ። ዓስራት ገ/ማርያም በ1983 ዓ.ም በጻፉትና ለንባብ ባበቁት መጽሐፋቸው «ትምህርተ መለኮት» የጌታ ልደት (ገና) ታኅሣሥ 28 ወይም 29 ቢውልም ጾሙ ሳይዛነፍ ኅዳር 16 እንደሚገባ ያስረዳሉ (ገጽ 306)። ስለዚህ የትኛውን እንቀበል? ማብራሪያችሁን እጠብቃለሁ።

(አክሊሉ– ለ.አ)

ከአዘጋጁ – የጾመ ነቢያት መግቢያ ቀን ብዙ ሰዎችን ግራ በማጋባቱ «አድሉ ለጾም» የሚለውን የሐዋርያት ትምህርት መሠረት በማድረግ በ1980 ዓ.ም ቅዱስ ሲኖዶስ ጾሙ ሁል ጊዜ ኅዳር 15 እንዲጀመር ወስኗል።

✣ ✣ ✣

ከዚህ በታች ስማችሁ የተዘረዘረው የመጽሔታችን አንባቢዎች ጥያቄዎቻችሁ፤ አስተያየቶቻችሁ፤ ጽሑፎቻችሁ እንዲሁም የልደት ካርዶቻችሁ ደርሰውናል። ጽሑፎቻችሁና ጥያቄዎቻችሁ እንደ ቅደም ተከተላቸውና ወቅታዊነታቸው እናወጣለን። ስለ አስተያየታችሁ እናመሰግናለን። ወደፊትም በተሳትፎአችሁ አትለዩን።

ማኅተመ ሥላሴ አያሌው (አዱት)፤ ከዲ.በለጠ ኃ/ማርያም (አርሲ–በቆጂ)፤ ተዋቸው እንዳለ (ባሕር ዳር)፤ አሸብር ተመስገን (አ.አ)፤ ተማሪ ታደሰ ነጋሽ (አዋሳ እርሻ ኮሌጅ)፤ ሰሎሞን ይልማ (አርባ ምንጭ)፤ ከተማ ብሹ (ፍቼ)፤ ጌታቸው አበበ (ደብረ ብርሃን ቅ/ሥ/ሰ/ት/ቤት)፤ ዮዲት ጉትማ (ይርጋ ጨፌ)፤ መ/ር ቴዎድሮስ ሀብቴ (ወልቂጤ)፤ ታምራት አረጋው (ድሬዳዋ)፤ ተክሉ ፀጋዬ (ሰኮሩ)፤ ምስጋናው ምሕረቱ (ጅጅጋ)፤ አሸብር ተመስገን (አ.አ)፤ አቶ በለጠ ከተማ (ዲላ)፤ መ/ር ዘረቀ ረዲ (ከሊሙ ገነት)፤ ተፈራ ሙሉጌታ (አቴንስ–ግሪክ)፤ ናዖድ ቤተ ሥላሴ (ዓለማያ ግብርና ዩኒቨርሲቲ)፤ ጥላሁን በቀለ (አ.አ.ኤርፖርት ጉምሩክ ዕቃ መደብር)፤ ታምራት ገብሩ (ጋምቤላ ሆስፒታል)፤ ኃይለአብ ትኩእ (መቀሌ)፤ ዲ.አዛዥ ሰውነት (ፓዌ)፤ ኪሩቤል ፀጋዬ (መተሐራ)፤ ስቶም ሲሳይ (አ.አ)፤ ወጣት ጌታቸው እንግዳየሁ (ደብረታቦር)፤ አዲስ ታደሰ (መልካ ሠዲ)፤ ሽመልስ ገብሬ (ሚዛን ተፈሪ)፤ አዋሳ አቡነ ተ/ሃይማኖት ሰንበት ት/ቤት ተማሪዎች፤ ዲ.ጌትነት ተካ (ጂንካ)፤ ተማሪ ፈረደ አልማው (ቡሬ)፤ ሳሙኤል (ከአዋሬ አ.አ)፤ ተማሪ አበበ ታደሰ (መቱ)፤ ብርሃኑ ገብሬ (ጅማ ዘር የቡ)፤ ሽመክት አሰፋ (መቂ)፤ አበበ ይርኮ (አ.አ)፤ አቦነሽ አሰፋ (ጅማ)፤ ዘላለም ማሞ (አ.አ.ዩ.4 ኪሎ)፤ እንግዳ ወርቅ መኩሪያ (ጌዶ)፤ ወ/ሪት ሰላማዊት በፈቃዱ (አርሲ ሮቤ)፤ ታዱ አበራ (ዶዶላ ባሌ)፤ ዓለምነህ አስጨናቂ (ባሌ–አዳባ)፤ አበባው አበራ ማሞ (አ.አ)። መስከረም በልሁ (ጅማ)፤ ወልደ ማሪያም (ሰሜን አሞ በዲቲ)፤ ሲሳይ አበራና ዳኜ አበራ (አ.አ)፤ ሀብታሙ ታዬ (ሀገረ ማርያም)፤ ተማሪ ነጋ ጣሴ (ባሕር ዳር)፤ ታከለ አርስ (ቡታጅራ)፤ አበባው ዘውዴ (አ.አ.ዩ)፤ ጥላሁን ዘሪሁን (ብቸና)፤ አንበሴ አልቶ (ጮንቻ)፤ መ/ር ዱፌራ ዲለሌሣ (ደራ)፤ ዲ.ታሪኩ ሞላ (ሊሙ–ካሣ)፤ ሲሳይ ተፈራ (ደምቢ ዶሎ)፤ ትዕግሥት ወ/ሰንበት (አ.አ)።



©ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

# ከሊቃውንት በረከት

ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ለልጆቿ ከምታስተምራቸው መንፈሳዊ ተጋድሎዎች መካከል ለሥጋ ፈቃድ ልጓም የሆነው ጾም እና ለመንፈሳዊ ሕይወት ማደሻ የሚሆነው ንስሐ ይገኙባቸዋል። እነርሱም ለአንድ ኦርቶዶክሳዊ ሰው የሥጋ ፈቃዱን እየገታ ነፍሱን የሚያለመልምባቸው ስንቆች ናቸውና። ቤተ ክርስቲያናችንም ሥርዓት ሠርታ ልጆቿን በሚገባ ታስተምራለች።

የጾም ወቅት መንፈሳዊ ተጋድሎዎች የሚበዙበት፣ ለእግዚአብሔር

## ጾም፣ የጽድቅ በር

(ከዓባይነህ ካሴ)

ያለንን ፍቅር የምንገልጥበት እምነታችን የሚጠነክርበት፣ ከዲያብሎስ ጋራ የምንዋጋበት፣ ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ቅርበትና ቤተሰባዊነት የምናሻሽልበት፣ ምሥጢራችንን ለአምላካችን የምንናገርበት፣ ድሆችን የምናስብበት ጊዜ ነው። ስለዚህም የሚጾም ሁሉ በሥጋ ፈቃዱ ላይ ድልን ይቀዳጃል፣ የለመነውን ያገኛል፣ ሰማያዊ የሆነውንም ምሥጢር ለማየት ከዓላማዊ ነገሮች ተለይቶ ይነጠቃል፣ በዓለም እየኖረ ከዓለሙ ይለያል። ዮሐ.15፥19።

### ሀ. ጾም ለምን?

ብዙ ሰዎች ለምን እንደሚጾሙ ስለማያውቁ ከእህል ከውሃ ተከልክሎ ለተወሰኑ ሰዓታት መቆየት፤ ከሥጋ፣ ከወተት፣ ከቅቤ መለየት ብቻ ጾም መስሎ ይሰማቸዋል። ይህም በመሆኑ ከውፍረታቸው ጥቂት የቀነሱ እንደ ሆን «ጾሙ አከሳኝ» ሲሉ ይሰማሉ። ይህ ግን በጭራሽ የጾም ዓላማ አይደለም። ዓላማው ለፈቃደ ነፍስ ለመገዛት፣ በዚህም ትሕትናን ገንዘብ ለማድረግ በትህትናም ከተናቁት ጋር አብሮ ለመዋል (የታረዙትን በማልበስ፣ የተራቡትን በማብላት፣ የታመሙትን በመርዳት) በእነዚህ ሁሉ ላይ ደግሞ ስለራሳችንና ስለሌሎች (ስለ ተጨነቁ፣ ስለታሠሩ፣ ስለተሠደዱ፣ በጦርነት ስለሚሰቃዩ...) ከእግዚአብሔር ምሕረትን መለመን ነው። በተጨማሪም:-

1. እግዚአብሔርን ለመለመንና ከእርሱም በረከትን ለመቀበል:- እንደ ዕዝራ እና አስቴር ስለራሳችን፣ ስለ ልጆቻችንና ወዳጆቻችን ምሕረት ለመለመን፣ ዕዝ.8፥21፣ ኢ.ስ.4፥3፣ 16

2. ለመጸጸት ንስሐ ለመግባት:- እንደ ነነዌ ሰዎች ከእግዚአብሔር ለመታረቅ፣ ዮና.3፥8–10። እንደ ዳንኤል ‹በድለናል ዐምፀንማል፣ አሁን ግን ይቅር በለን› ለማለት፣ ዳን.9፥5–8።

3. ለአገልግሎት:- ቅዱሳን ሐዋርያት ወደየክፍለ ዓለሙ ለስብከተ ወንጌል ከመለያየታቸው በፊት ጾመዋል። እኛም ልናበረክት ስላቀድናቸው መንፈሳዊ ሥራዎች በቅድሚያ ልንጾም ይገባናል (የሐዋ.13፥2–3)

### ለ. ጾም ከምን?

ከላይ የተጠቀሰውን ጾም ፍጹም ለማድረግም:-

1. ወቅት ተለያይቶለት የሚጾም። ይህም ለተወሰኑ ጊዜያት ከጥሉላት ምግቦች (ከሥጋ፣ ከወተት፣ ከቅቤና ከተመሳሳይ ውጤቶች) እና ከሚያሰክር መጠጥ ነው።

ቅዱስ ዳዊት በጾሙ ጊዜ «ሥጋዬም ቅቤ በማጣት ከሳ» መዝ. 108፥24 እና ነቢዩ ዳንኤልም «በዚያም ወራት እኔም ዳንኤል ሳዝን ነበርሁ። ማለፊያ እንጀራም አልበላሁም፣ ሥጋና ጠጅም በአፌ አልገባም» ዳን.10፥3 እንዳሉ ከጥሉላት እንከለከላለን።

ሆኖም ግን አንዳንድ ሰዎች የዓሣን ሥጋ እንደ ሥጋ ባለመቁጠር ይሁን ወይም ሌላ መበላት እንዳለበት ሲከራከሩ ይታያሉ። ቤተክርስቲያናችን በጾም ጊዜ ጥሉላት የሌሉበት ምግብም ቢሆን በመጠን ይበላ እያለች (ዳንኤል ማለፊያ እንጀራም አልበላሁም እንዳለ) የዓሣ አለመበላት እንደ ጥያቄ ሊነሳ አይገባውም። እንዲሁም በእነዚህ የተቀደሱ የጾም ጊዜያት ክርስቲያን ሁሉ ከሚያሰክር መጠጥ የመለየት ግዴታ አለበት። ነቢዩ ዳንኤል ‹ጠጅም በአፌ አልገባም› ያለው ይህንኑ ለማጠየቅ ነው። የራስን መንፈሳዊ ሕይወትም ለማሻሻል በሚደረገው ጥረት መካከል



©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

የምግብ ማካካሻ ማድረግ የማይገባ መሆኑን ሁሉም ሊገነዘብ ያስፈልገዋል።

## ሐ. ጾምን እንዴት እንቀበለው?

ጾም መጣብን ተብሎ የሚፈራና የሚማረር ሳይሆን በመጣልን ተብሎ በጉጉት የሚናፈቅ ዕድሜ የሚለመንለት የሥጋና የነፍስ አስታራቂ ሽማግሌ ነው።

የጾም ቀናት መንፈሳዊ ኃይል ማግኛና ስንቅ ማከማቻ ሲሆኑ ለሥጋ ፈቃድ ደግሞ የሞት ጊዜያት ናቸው። ጾምን የሚጾም ሰው የሚከተሉትን ቁም ነገሮች በሕሊናው ማስቀመጥም ያሻዋል።

2. ዕለት ተዕለት የማይቋረጥ ጾም – ያም የአንደበት፣ የዓይን፣ የእጅ፣ የእግር፣ የሕሊና ወዘተ...ጾም ነው።

• አንደበት – ከሃሜት፣ ከስድብ፣ ከሽሙጥ፣ ከሽንገላ፣ ምስጢር ከማባከን፤

• ዓይን:- ዓይቶ ለዝሙት፣ ለስርቆት፣ ከመመኘት፤

• እጅ:- ከመማታት፣ ከመግደል፣ ከመስረቅ፣ ሲጋራና ሀሺሽ ከመጨበጥ ጉቦ ከመቀበልና ከመስጠት፤

• እግር:- ወደ ዝሙት፣ ስካር፣ ዘፈን፣ ወዘተ...ቦታ ከመሄድ፤

• ኅሊና:- ከምቀኝነት፣ ከቅንዓት፣ መጾም ነው።

1. ዓላማና ይዘቱ መንፈሳዊ መሆኑን:- እንደ ግዴታ፣ ብዙ ሰው ስለ ጾመው ብቻ፣ ወይም ለመወደስ (ጿሚ ለመባል) የሚጾም መሆን የለበትም።

2. የጸጸትና የልብ ንጽሕና ጊዜ መሆኑን – ‹ወደኔ ተመለሱ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፣ እኔም ወደ እናንተ እመለሳለሁ› ዘካ.1፥3 እንዳለ እግዚአብሔር ደስ የሚሰኝበትን ሥራ መፈፀሚያ፣ በደልን አምኖ በኃጢአት የጐሰቆለች ነፍስንም በንስሐ፣ በቅዱስ ሥጋውና በክቡር ደሙ የሚያነጹበት ጊዜ ነው።

3. ለነፍስ ምግብ ማግኛ ጊዜ መሆኑን – ከሥጋዊ ይልቅ ለመንፈሳዊ ነገሮች ትኩረት የሚሰጥበት ጊዜ ነው። በጾም ወራት የዕለታቱን ቅድስና፣ ታሪክ እና ሊፈጸሙ የሚገባቸውን ሥርዓቶች በማወቅ የተውትን የምግብና የመጠጥ ዓይነቶች ከማሰላሰል ይልቅ ለነፍስ የሚሆነውን ምግብ ቃለ እግዚአብሔርን እያጣጣሙ መንፈሳዊ ሕይወትን ለማለምለም መዘጋጀት ያስፈልጋል።

እንዲህ ያለውን ጾም የጾሙት ከእህል ከውኃ በመከልከላቸው አማሩ ተዋቡ ፊታቸው አበራ እንጂ ለበሽታና ለሞት አልተዳረጉም። (ሙሴ፣ አስቴር፣ ሠለስቱ ደቂቅ) ዘፍ. 34፥24–35፣ አስቴ.2፥17 እና ዳን.1፥12–15።

## መ. ጾምና ንስሐ

ሰው በጾም፣ ሥጋውን ለኃጢአት ከሚያነሣሣ ከማንኛውም ምኞት ይከለከላል። በዚህም ጊዜ የራሱ ኃጢአት ከፊት ለፊቱ በመስተወት ውስጥ እንዳለ ምስል ቀርቦ ይታየዋል። ፈጥኖም ለንስሐ ይዘጋጃል። «በሃይማኖት ብትኖሩ ራሳችሁን መርምሩ» እንዳለ ሐዋርያው (2ኛ ቆሮ.13፥5) ማንነታችንን፣ ትናንትናና ዛሬ ምን ሠራን፣ የነገ መንገዳችንስ ምን መሆን አለበት? ብለን የምንጠይቅበት ወቅት ነው። እግዚአብሔር ጾማችንን እንዲቀበለው ራሳችንን እንመርምርና ካለፈው የኃጢአት ኑሮ እንላቀቅ። ያን ጊዜም ፈጥኖ ይምረናል።

«እነሆ የእግዚአብሔር እጅ ከማዳን አላጠረችም፣ ጆሮውም ከመስማት አልደነቆረችም፤» ነገር ግን በደላችሁ በእናንተና በአምላካችሁ መካከል ለይታለች፣ እንዳይሰማም ኃጢአታችሁ ፊቱን ከእናንተ ሰውሮታል።» ኢሳ.59፥1–2።

የጾምና የንስሐን ግንኙነት ስናነሳ የነነዌ ሰዎች ትዝ ይሉናል። እግዚአብሔር በመጀመሪያ ዮናስን እንዲህ ብሎት ነበር። «...ሰዎችም ሁሉ ከክፉ መንገዳቸውና በእጃቸው ካለው ግፍ ይመለሱ» ዮና.3፥8። ይህንን ቃል ካስተላለፈ በኋላም እንዳያጠፋቸው እግዚአብሔርን አንድ ነገር አሸንፎታል። ያንንም ነቢዩ እንዲህ ሲል ተናግሮታል «እግዚአብሔርም ከክፉ መንገዳቸው እንደተመለሱ ሥራቸውን አየ» ዮና.3፥10። እነዚህ ሰዎች ምሕረት ያገኙት ማቅ ስለለበሱ፣ አመድ ስለነሰነሱ ወይም ሦስት ቀንና ሌሊት ከንጉሡ እስከ ሌላው፣ ከሰው እስከ እንስሳው ከእህል ከውሃ ስለተከለከሉ ብቻ አይደለም። ከእነዚህ ሁሉ በፊት ይህንንም ለማድረግ ያስገደዳቸውን ከክፉ መንገዳቸው መመለሳቸውን (መጸጸታቸውን) ስላየ እንጂ። ከዚህ አባባል የጾም መጀመሪያው ንስሐ (ጸጸት) መሆኑን እንረዳለን።

ስለዚህ እኛም በጾማችን ወቅት ስለ ኃጢአታችን ንስሐ እየገባን ከእግዚአብሔር ጋር መታረቅ ይሻለናል። ‹ጌታ ሆይ፣ እስከ መቼ ትረሳኛለህ?› ከማለት ይልቅ ‹እስከመቼ ረሳሀለሁ?› እስከ መቼስ በተቀደደ መጋረጃ ፊቴን እሰውራለሁ? ማለት ይገባናል።

ነፍሳችንን ከአሁኑ በንስሐ እና በሥጋ ወደሙ አንጽተን ልባችንን የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እናድርጋት። ከተዘፈቅንበት የኃጢአት ባሕርም እንውጣ። በንስሐ ያለንም መንፈሳዊ ተጋድሎአችንን እንጨምር። ይህን ለመፈጸምስ ከአሁን (ከዛሬ) ሌላ ምን የተሻለ ጊዜ አለን? ከዕድሜያችን ላይ አንዲት ሴኮንድ ባለፈች ቁጥር ሞት ወደ እኛ፥ እኛም ወደ ሞት እየተጓዝን እንደሆነ ማስተዋል ያስፈልጋል። እንግዲህ በዋዛ ፈዛዛ የምናሳልፋቸው ጊዜያት ሊኖሩን አይገባም። መጽሐፍ «እነሆ የመዳን ቀን አሁን ነው» ይላልና። 2ኛ ቆሮ.6፥2። ✤

እግዚአብሔር ጾማችንን የድል ያድርግልን።



©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

# ትምህርተ ሃይማኖት

## ምሥጢረ ቁርባን

### በሚታይ አገልግሎት የማይታይ ጸጋ

በቅዱስ ቁርባን የሚገኘው መንፈሳዊ ጸጋ ብዙ ነው።

ሀ. በዕለተ ዓርብ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በጎልጐታ በመልዕልተ መስቀል ላይ የተቆረሰውን ቅዱስ ሥጋና ያፈሰሰውን ክቡር ደም እንቀበላለን።

ለ. በመንፈሳዊ ዕውቀት የምናድግበትንና በጸጋው የምንበለጽግበትን የሕይወት ምግብ እናገኛለን። መድኃኒታችን በመዋዕለ ሥጋዌው እንዳስገነዘበን «የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ ወደ እኔ የሚመጣ ከቶ አይራብም በእኔ የሚያምን ሁል ጊዜ ከቶ አይጠማም...ሥጋዬ እውነተኛ መብል ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነውና» ዮሐ.6፥35ና 55።

ሐ. ሥርየተ ኃጢአትን እናገኛለን። አበው «ሰው ሆኖ የማይበድል እንጨት ሆኖ የማይጤስ የለም» እንዲሉ ደካማ ባሕርያችን ወደ ስህተት ጐዳና በሚመራንና የኃጢአት ጭቃ አዳልጦን በምንወድቅበት ጊዜ በንስሐ ሳሙና ታጥበን የጌታችንን ሥጋና ደም በመቀበል ከኃጢአት እንነጻለን እንቀደሳለን። «ስለ ብዙዎች ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው» ማቴ.26፥27።

መ. ጌታችንና አምላካችን በሕይወታችን ውስጥ ይኖራል። እኛም በእርሱ እንኖራለን «ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል እኔም በእርሱ እኖራለሁ» ብሏልና። ዮሐ.6፥56።

ሠ. ከጌታችን ጋር ያለንን ተዋሕዶ እንዲሁም ከቅዱሳን ጋር ያለንን አንድነት እናረጋግጣለን። «ኅብስቱ አንድ እንደሆነ እንዲሁም እኛ ብዙዎች ስንሆን አንድ አካል ነን። ሁላችንም ከአንድ ኅብስት እንቀበላለንና። 1ቆሮ.10፥17።

ረ. ቅርንጫፍ ከግንዱ እስካልተለየ ድረስ ሕይወት እንዲኖረው ሁሉ ክርስቲያኖችም የወይን ግንድ ከሆነው ከአምላካችን ከኢየሱስ ክርስቶስ አለመለየታችንን፣ በሕይወት መኖራችንን፣ በኃጢአት አለመሞታችንን እናረጋግጣለን «እውነት እውነት እላችኋለሁ የሰውን ልጅ ሥጋውን ካልበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም» ዮሐ.6፥53።

ሰ. የዘላለም ሕይወትን እናገኛለን «ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ» ዮሐ.6፥54።

(The orthodox church Sacramentts p.32)

### የሚታይ አገልግሎት ለመሥዋዕት የሚሆነው ኅብስት አዘገጃጀት

ለመሥዋዕት የሚሆነው ኅብስት የሚዘጋጀው በወራቱ ከደረሰ ዋግ ካልመታው እንክርዳድ ከሌለበት (የተለቀመ) ንጹሕ ስንዴ ነው። ፍት.ነገ አንቀጽ 13 ረስጠጅ 3 ገጽ 138

በታቦቱ ላይ የሚሠዉትን መሥዋዕት ዕለቱን ያዘጋጁት ሊሆን ይገባል። ከተሠዋም በኋላ ለሚቀጥለው ቀን ማደር የለበትም። ኅብስቱም ነቅዕ የሌለበት ያላረረ ያልጠቆረ መሆን ይኖርበታል (ፍት.ነገ አንቀጽ 13 ገጽ 139 ረስጠጅ 30 ፍት. ነገ አንቀጽ 13 ገጽ 139 በስ 98)

ኅብስተ አኰቴቱ ገና ሲሠራ ሥርዓቱ አሥራ ሦስት መስቀል ባለው ማኅተም ታትሞ ይሠራል (ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ገጽ 54)

### ለመሥዋዕት የሚገባ ወይን

ወፍ ያልመጠጠው፣ አይጥ ያልቆረጠመው፣ መጀመሪያ የደረሰው ወይን ሊሆን ይገባል። ለመሥዋዕቱ የሚቀርበው ወይን በእሳት ከሚበስሉ ከጠጅ እና ከዐረቄ ወገን በማንኛውም አይሠራም (ፍት.ነገ አንቀጽ 13 ገጽ 138 ረስጠጅ 3)

ወይኑንም ሲሠሩ ጥሩ መሆኑን ተመልክቶ መሥራት ይገባል። ንጹሕ ጽሩይ ካልሆነ ለመሥዋዕት አይገባም፣ ጊዜ ያለፈውን ወይን መጨመር እንደማይገባ ታዝዟል። እንዲሁም ከሦስት እጅ የበለጠ ውኃ መጨመር



©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

አይገባም (ፍት. ነገ.አንቀጽ 13 በስ 995 102)

አግብአተ ግብር (ከቤተልሔም ወደ ቤተ መቅደስ)

ዲያቆኑ በቤተልሔም ኅብስቱንና ወይኑን ለመሥዋዕት ከሠራና ከአዘ ጋጀ በኋላ ንፍቀ ዲያቆን ኅብስቱን በመሶበ ወርቅ በራሱ ላይ አድርጐ፤ ወይኑን ሠራዊው ዲያቆን በጽዋዕ ይዞ ቃጭል እያቃጨለ በፊት በፊቱ፣ ንፍቁ ቄስ መስቀልና ማዕጠንት ይዞ እያጠነ በኋላ በኋላው ሆነው ከቤተ ልሔም ወደ ቤተ መቅደስ ይገባሉ (ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ገጽ 55)

ቅዳሴ አስቀድሶ ለሚያውቅ ሁሉ ይህ ክስተት እንግዳ አይደለም። ለሚያስቀድስ ምእመን የሁል ጊዜ ክንውን ነው። ምናልባት በአንዳንድ ክርስቲያኖች አእምሮ የምሥጢሩ ምንነት ግልጽ እንዲሆንላቸው የሚሹ ይኖራሉ። ኅብስቱና ወይኑ በቤተል ሔም መዘጋጀቱና ከዚያ መምጣቱ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቤተልሔም መወለዱን ያመለክታል። ከቤተልሔም ወደ ቤተ ክርስቲያን መወሰዱ ቤተ ክርስቲያን የቀራንዮ ምሳሌ ነች። ጌታ ሠላሳ ሦስት ዓመት ከሦስት ወር ዞሮ አስተ ምሮ በመጨረሻ በቀራንዮ ኮረብታ መሥዋዕት ሆኗልና ኅብስቱም የሚሠ ዋው የቀራንዮ አምሳል በሆነችው በቅ ድስት ቤተ ክርስቲያን የቃል ኪዳኑ መገለጫ በሆነው በታቦቱ ላይ ነው።

ሌላ ሊደረግ የሚገባ ጥንቃቄ ደሙ በምድር ላይ እንዳይፈስ ጽዋ ውን ከመጠን በላይ መሙላት አይገባም። ሲያቀብሉም በጥንቃቄ መሆን አለበት (ፍት.ነገ አንቀጽ 13 ገጽ 140 ረስጣ 45)

ከቁርባን በፊት ሊደረግ የሚገባ

ማንኛውም ክርስቲያን የጌታን ሥጋና ደም መቀበል ሃይማኖታዊ ግዴታው ነው። ዳሩ ግን ወደ ሥጋ ወደሙ ከመቅረቡ በፊት ሊያደርገው የሚገባ ቅድመ ዝግጅት አለ። እነዚህ ቅድመ ዝግጅቶች የሚከተሉት ናቸው።

ሀ. የሚቀድሱና የሚቆርቡ ሰዎች በጋብቻ ሥርዓት የሚኖሩ ከሆኑ ከመ ቀደሳቸውና ከመቁረባቸው በፊት ሦስት ቀን፣ ከቁርባን በኋላ ሁለት ቀን ከሩካቤ መከልከል ይገባቸዋል።

ለ. ሥጋ ወደሙን የሚቀበል ሰው አስቀድሞ ራሱን ለካህን ማስመርመር ይገባዋል። ይህም ማለት ንስሐ ገብቶ ከኃጢአቱ ነጽቶ በደሉን አስፍቶ መሆን ይኖርበታል ቅዱሳን አባቶች እንዳስተማሩን ከክርስቲያን ወገን ማንም ሰው የክርስቶስን ሥጋውን ደሙን ተቀብሎ ትንሣኤ ዘለሕይ ወትን ሊወርስ ቢወድ ልቡን ከቂም ከበቀል፣ ሰውነቱን ከበደል ንጹሕ አድርጐ መቀበል አለበት። ይህም ማለት ሰው ስለሚያውቀው ኃጢአት ተናዝዞ ስለማያውቀው ይቅር በለኝ እያለ በንጹሕ ልቡና ይቁረብ ማለት ነው። በንስሐ ከኃጢአት ሳይነጻ በድፍረት ቢቀበል ግን የጌታ ሥጋ እንደሆነ አላወቀምና እንደ ምድራዊ ምግብም አቃልሎታልና በኃጢአት ሳለ ያለ ኃፍረት ሥጋውን ደሙን በመቀበሉ ሥላሴ ይፈርዱበታል። 1ቆሮ.11፥23 ና 24

ሐ. ሥጋ ወደሙ ለመቀበል አሥራ ስምንት ሰዓት ያህል ከእህል ከውኃ ተከልክሎ መጾም ይገባል።

መ. ካህን በሚቀድስበት ቀን ዕንቅፋት ቢያገኘው ማለት ነስር፣ ትውኪያ፣ ብስና፣ ማንኛውም የአካል መድማት፣ መቁሰል፣ ወደ አፍ የሚገባ ተሐዋሲ ይህን የመሰለ ሁሉ ቢያጋጥመው በዚያው ዕለት መቀደስ እና መቁረብ አይችልም።

ከቁርባን በኋላ ከአለመጠንቀቅ የተነሣ እንዲህ ያለ ነገር ቢያጋጥመው ንስሐ ሊሰጠው ይገባል። ንስሐውን ሳይፈጽም እንደገና መቁረብ አይች ልም። ይህም ለካህን ብቻ ሳይሆን ምእመናንንም ሁሉ የሚመለከት ነው።

(ማስረጃ ያዕቆብ ዘእልበረዳኢ)

(በሊቀ ካህናት ክንፈ ገብርኤል አልታዬ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ገጽ 50–51)

ለመቁረብ የሚያበቃና የማያበቃ ሁኔታ

ሀ. ቅዳሴ ሲጀመር ያልነበረ ሰው አይቆርብም፣ ቅዳሴ ሲጀመር ያልነ በረ ካህንም እንደዚሁ ሥጋ ወደሙ ሊቀበል ሊያቀብል አልተፈቀደለትም ፍት.ነገ አንቀጽ 12 ገጽ 137 በስ 97

ለ. ከምእመናን በስተቀር (የሚቀ በሉት የጌታን አማናዊ ሥጋውንና ደሙን መሆኑን ከሚያምኑ በስተቀር) ያላመኑ ሰዎች ሥጋ ወደሙ ሊቀበሉ አይገባም። እንዳይቀበሉ መጠበቅና መቆጣጠር ያስፈልጋል። (ፍቅ. ነገ አንቀጽ 13 ገጽ 140 ረስጠብ 44)

ሐ. በንስሐ የተለየ ሰው የንስሐ ጊዜውን ሳይፈጽም ለሞት የሚያበቃ ደዌ ቢታመም ሥጋ ወደሙ ከመቀ በል አይከለከልም። ሥጋውን ደሙን ተቀብሎ ከዳነም ከምእመናን ጋር በጸሎት ይሳተፋል። በቀኖና ወደ ተለዩ ሰዎች አይመለስም (ፍት.ነገ አንቀጽ 13 ገጽ 139 ዕንቁራ 15)

መ. የሚጥል በሽታ ያለበት፣ ጋኔን ያደረበት (ሰውን የማይሳደብ ከጣለው በኋላ ዐረፋ የማያስደፍቀው



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ከሆነ) ሥጋ ወደሙ ከመቀበል አይከለከልም ሊቀበል ይችላል (ፍት.ነገ አንቀጽ 13 ጢሞ ገጽ 139)

## የአቀራረብ ሥርዓት

ሥጋውን ቄሱ በእጁ ሲያቀብል ደሙን ንፍቅ ቄሱ በዕርፈ መስቀል ለካህናት፤ እንዲሁም ዲያቆኑ ለምእመናን በዕርፈ መስቀል ይሰጣል እንጂ ንፍቅ ቄስና ዲያቆን ሥጋውን ደሙን በእጃቸው አይነኩም።

ያቀራረቡ ተራ እንደሚከተለው ይሆናል።

1. ሊቀ ጳጳሳት
2. ጳጳሳት
3. ኤጲስ ቆጶሳት
4. ቆሞሳት
5. ቀሳውስት
6. ዲያቆናት
7. ንፍቀ ዲያቆናት በየተራቸው ይቆርባሉ።


ከእነርሱም ቀጥሎ ሁሉም በየማዕረጉ ተራ ይቆርባል። ከካህናት ቀጥሎ በዕለቱ ክርስትና የተነሡ ይቀበላሉ። ከዚያም ሕፃናት ቀጥሎ ደናግል፤ ከዚያም ሕዝባውያን ምእመናን ሥርዓተ ቅዳሴው እንደሚያዝዘው በየማዕረጋቸው ይቆርባሉ።

ቁርባን ተቀብሎ ማየመቁረር ይሰጣል ይኸውም የቅዳሴ ጸበል በመባል የሚታወቀው ነው። (ፍት.ነገ አንቀጽ 13 ገጽ 242 እርስጣ 65)

## ከቁርባን በኋላ የሚደረግ ጥንቃቄ

ሀ. ከቆረቡ በኋላ በዚያው ዕለት ወደ ፍርድ ቤት መሄድና መሟገት ክልክል ነው። (ሥርዓተ ቤተክርስቲያን ገጽ 62)

ለ. በቆረቡበት ቀን ከሚስት ወይም ከባል መገናኘት፤ አብዝቶ



መብላት መጠጣት፤ ጥፍር መቆረጥ፤ ፀጉር መላጨት፤ በውኃ መታጠብ፤ ከልብስ መራቆት ክልክል ነው (ሥርኀተ ቅዳሴ 166)

### የሚቆርቡ እነማን ናቸው

በማዕከለ ምድረ በቀራንዮ ኮረብታ በመልዕለተ መስቀል የተሰቀለው የዓለም መድኃኒት ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ትምህርቱ በቀራንዮ የቆረሰው ሥጋና ያፈሰሰው ደም ለሚያምንበት ሁሉ የተሰጠ ዘላለማዊ ምግብ መሆኑን አስትምሯል። መላው የሰው ዘር በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝነትና የባሕርይ አምላክነት ካመነ ይቀበል ዘንድ ውዴታው ሳይሆን መንፈሳዊ ግዴታው ነው። ማንም ሰው መንግሥተ እግዚአብሔርን ይወርስ ዘንድ መጠመቅ ግዴታው እንደሆነ ሁሉ ሥጋ ወደሙን መቀበልም ለድኅነቱ አስፈላጊና ሃይማኖታዊ ግዴታው ነው።

በ40 ቀንና በ80 ቀን ሀብተወልድና ስመ ክርስትና ካገኙት ሕፃናት አንሥቶ እርጅና ከአልጋ ተጣብቀው እንዲኖሩ እስካደረጋቸው አረጋውያን ድረስ ሥጋ ወደሙን ይቀበሉ ዘንድ ቤተ ክርስቲያን የጥሪ ደውሏን ዘወትር ታስተጋባለች።

የቤተ ክርስቲያንን ቀኖና የማያውቁ ምናልባትም ራሳቸውን የሰየሙ አንዳንድ ካህናት ተብዬዎች «ሥጋ ወደሙን ሊቀበሉ የሚገባቸው ሕፃናት ወይንም ያገቡ ከዚያም በተረፈ መነኮሳት ብቻ እንጂ የሕይወታቸውን አቅጣጫ ለመወሰን ገና በዝግጅት ላይ ያሉና በንጽሕ ያልተጠበቁ ሰዎች ቢኖሩ በደል እንዳይሆንባቸው ሥጋ ወደሙን መቀበል እንዲቆጠቡ ያስፈልጋል» ይላሉ።

ነገር ግን ማንም ሰው (ምእመን) ሥጋ ወደሙን ለመቀበል ሊያደርገው የሚገባውን ቅድመ ሁኔታ ካጠናቀቀ ለመቀበል የሚያግደው ምንም ነገር የለም። ሥጋ ወደሙን እንዳይቀበሉ የሚከለከሉት ያላመኑ ወይም አምነው ተጠምቀው ራሳቸውን በሕገ ክርስቲያን ያላስጠበቁ ናቸው። እነዚህም ሥጋ ወደሙ አማናዊ የጌታ ሥጋና ደም መሆኑን የሚጠራጠሩና ትዕቢትን እንደ ሸማ ተጎናጽፈው ንስሐን የናቁ ሰዎች ናቸው።

ከዚህ ውጭ ግን ሕፃን ሆነ ጐልማሳ ያገባም ሆነ ያላገባ ሥጋ ወደሙን ይቀበል ዘንድ መፈቀድም ብቻ ሳይሆን ግዴታውም ነው። ✣


©ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

# የእግዚአብሔር ሕግ

(ካለፈው የቀጠለ)

ባለፈው እትም የእግዚአብሔር ሕግ በሚል ርዕስ በተከታታይ ለምናቀርበው ትምህርት መግቢያውን አስነብበን በቀጠሮ መለያየታችን ይታወሳል። እነሆም የቸሩ አምላካችን የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆኖ ዛሬ ደግሞ ተከታዩን ክፍል ይዘን ቀርበናል።

ከሁሉ አስቀድሞ እነዚህ የእግዚአብሔር ሕግ ድንጋጌዎች ስንት እንደሆኑና እነማን መሆናቸውን በማስታወቅ ወደ ዝርዝር ትንታኔውና ወደ ትምህርቱ እንገባለን። በዚሁ መሠረት የእግዚአብሔር ሕግ ድንጋጌዎች ለነቢየ እግዚአብሔር ሙሴ የተሰጡት አሠርቱ ትእዛዛት ሲሆኑ ዝርዝራቸውም የሚከተለው ነው።

1. እግዚአብሔር አምላክህ እኔ ነኝ ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ፤ ዘዳ.20፥2–3።
2. የእግዚአብሔርን የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ፤ ዘዳ.20፥7።
3. የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስብ አክብረው፤ ዘዳ.20፥10።
4. አባትህንና እናትህን አክብር፤ ዘዳ.20፥12።
5. አትግደል ዘዳ.20፥13።
6. አታመንዝር ዘዳ.20፥14።
7. አትስረቅ ዘዳ.20፥15።
8. በሐሰት አትመስክር ዘዳ 20፥16።
9. አትመኝ ዘዳ.20፥17
10. ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ ዘሌ.19፥18።

እዚህ ላይ ሊነሣ የሚገባው አንድ ነጥብ አለ። ይኸውም በቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ዘንድ ስለ አሠርቱ ትእዛዛት ዝርዝር ያለው ልዩነት ነው። አንዳንድ ሊቃውንት «የተቀረጸውን ምስል ለአንተ አታድርግ» የሚለውን (በዘዳ.20፥5) እንደ ሁለተኛ ትእዛዝ በመቁጠር እስከ «አትመኝ» ድረስ ብቻ ያለውን አሥር በማድረግ «ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ» የሚለውን በዘሌ.19፥16 የተጻፈውን ከአሠርቱ ትእዛዛት ቁጥር ያስወጡታል። ሌሎቹ ሊቃውንት ደግሞ «የተቀረጸውን ምስል ለአንተ አታድርግ» የሚለው ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ ከሚለው ውስጥ የሚጠቃለልና አምልኮን የሚመለከት በመሆኑ እንደተለየ ትእዛዝ ለብቻው ሊመዘገብ አይገባውም። ከዚህም በላይ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሚያስተምርበት ጊዜ ስለ ትእዛዛት የቀረበለትን ጥያቄ ሲመልስ «ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህም በፍጹም አሳብህም ውደድ (ፈጽመህ አምልከው) ታላቂቱና ፊተኛይቱ ትእዛዝ ይህች ናት። ሁለተኛይቱም ይህችን ትመስላለች እርሷም ባልንጀራህን እንደ ነፍስህ ውደድ የምትለው ናት» ማቴ.22፥35–40። በማለት መናገሩ ፍቅረ ቢጽን እንደ አንድ ዋነኛ ትእዛዝ በመቁጠሩ ነው። ስለዚህ አሥረኛው ትእዛዝ በዘሌዋውያን 19፥18 የተጻፈው «ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ» የሚለው መሆን አለበት በማለት በማስረጃ የተደገፈ ምክንያት ያቀርባሉ።

እኛም በመጽሐፋዊ ማስረጃ የተደገፈውን ሁለተኛውን አስተያየት በመቀበል ከፍ ብሎ በተዘረዘረው ቅደም ተከተል መሠረት ትምህርቱን እናቀርባለን።

## የመጀመሪያው ትእዛዝ

«ከግብፅ ምድር ከባርነት ቤት ያወጣሁህ እግዚአብሔር አምላክህ እኔ ነኝ ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ። በላይ በሰማይ ካለው በታች በምድር ካለው ከምድርም በታች በውኃ ካለው ነገር የማናቸውንም ምሳሌ የተቀረጸውንም ምስል ለአንተ አታድርግ አትስገድላቸው፤ አታምልካቸውም። በሚጠሉኝ እስከ ሦስተኛ አራተኛ ትውልድ ድረስ የአባቶችን ኃጢአት በልጆች ላይ የማመጣ፤ ለሚወዱኝ ትእዛዜንም ለሚጠብቁ እስከ ሺህ ትውልድ ድረስ ምሕረትን የማደርግ እኔ እግዚአብሔር አምላክህ ቀናተኛ አምላክ ነኝና።» ዘዳ.20፥2–5።

ይህን የመጀመሪያ ትእዛዝ በሚከተሉት ንዑሳን አርእስት በመከፋፈል እንመረምረዋለን። «እግዚአብሔር አምላክህ እኔ ነኝ»

አምላካችንና ፈጣሪአችን እግዚአብሔር በፍጹም ቸርነቱ የሚወደን መሆኑንና ማንነቱንም ጭምር «አምላካችሁ እግዚአብሔር እኔ ነኝ» በማለት ገልጦልናል። ብዙ ጊዜም ራሱን በተለያየ መንገድ ለሰው ልጆች ገልጧል። ለምሳሌም ለነቢዩ ሙሴ «እኔ የአባትህ አምላክ የአብርሃም አምላክ የይስሐቅም አምላክ የያዕቆብም አምላክ ነኝ።» ብሎታል። ዘዳ.3፥6። በዚህም በሙሴ አማካኝ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ነት አምላክ መሆኑን ለሕዝቡ ሁሉ ገልጧል። ያደረገላቸውንም ቸርነት አስታውሶ ያንን የቸርነት ሥራ የሠራሁላችሁ አምላካችሁ እኔ ነኝ በማለት በፍቅር ቋንቋ ማን መሆኑን ገለጠላቸው እንጂ «እኔ ሰማይንና ምድርን በውስጧም ያለውን ሁሉ የፈጠርኩ እግዚአብሔር ነኝ» ወይም «እኔ ምንም ምን የማይወስነኝ ልዑልና ኃያል አምላክ ነኝ» በማለት በማስፈራራት ራሱን የገለጠ አይደለም። ይልቅስ የሚረዳ የሚያድን ሰውን ወዳጅ ሰውንም ከማፍቀሩ የተነሣ ከግብፅ ባርነት እሥራኤልን ያወጣ መሆኑን በመጥቀስ በቸርነቱ እንዲያውቁት ከፍቅሩም የተነሣ እንዲያፈቅሩት ራሱን በዚህ መልክ ገለጠ።

እግዚአብሔር እርሱ ለሰው ልጆች ያለውን ፍቅርና መልካም ሃሳብ እንዳይዘነጉ ሰዎችን ያስታውሳቸዋል። የእርሱን ፍቅር ምሕረቱንና ቸርነቱን ባስታወሱ ጊዜ ደግሞ ይወዱታል። ስለ ፍቅሩም ያፈቅሩታልና ስለዚህ አስቀድሞ ያደረገላቸውን ቸርነት በመንገር ራሱን ለሰዎች ገልጧል። እግዚአብሔር ከሚያስፈራና ከሚያስደነግጥ ቃል ይልቅ ዘወትር በጆሮአችን የሚነግረን «እኔ ይህንና ይህን ከመሰለ ደዌህ የፈወስኩህ፣ በዚህ ዓመት ያቀድከውን እንድታከናውን የረዳሁህ፣ ከዚህ ወይም ከዚያ ችግር ያወጣሁህ፣ ከመከራም የከለልኩህ፣ መልካሙን ሁሉ ያደረግሁልህ እግዚአብሔር አምላክህ እኔ ነኝ» በማለት ነው። በዚህም ሁሉ ምክንያት አስፈሪ ስለሆነ ሳይሆን ቸርና መሐሪ ስለመሆኑና ስለ አደረገልን የተቀደሰ ይቅርታው እንዳንረሳው ስለሚፈልግ ስለምን ፈራው ሳይሆን ስለምንወደው እንድናስታውሰው ስለሚፈልግ ነው አምላክነቱን ባደረገልን ቸርነት የሚገልጠው።

እኛ በልማድ ዝንጉዎች ስለሆንን እግዚአብሔር ፍቅሩንና ቸርነቱን ያስታውሰናል። በአብዛኛውም እግዚአብሔርን የምናስታውሰው የምንሻውን ነገር በምንጠይቅበት ጊዜና የጠየቅነውን ከማግኘታችን አስቀድሞ ነው። የለመንነው ከተሰጠንና የምንሻው ከተደረገልን በኋላ ግን የእግዚአብሔርን ቸርነት እንዘነጋዋለን። ይህን ደካማ ጠባያችንን ስለሚያውቅ ነው እግዚአብሔር «እኔ ከባርነት ቤት ያወጣኋችሁ እግዚአብሔር አምላካችሁ ነኝ» በማለት ባደረገልን ቸርነት ራሱን የሚገልጥልን። በዚህም «የተዋረዳችሁበትን፣ በባርነት የተገዛችሁበትን፣ ምርኮኞች የነበራችሁበትን ዘመንና በዚያ ያደረግሁላችሁን እያስባችሁ አምልኩኝ» ማለቱ እንደሆነ ግልጽ ነው። ፍቅሩንም እያሰብን ከፍቅር በመነጨ አምልኮ እንድናመልከውም ጭምር እየነገረን ነው። በመሆኑም እግዚአብሔር ዘወትር የሚያደርግልንን በጎ ነገር ባለመዘንጋት የሚገባውን ሁሉ ልናቀርብለት ይገባል።

ከዚህ አንፃርም በእግዚአብሔር ፊት ተንበርክኮ «አቤቱ ጌታዬ እግዚአብሔር ሆይ አንተ ይህን ሁሉ ቸርነት ያደረግህልኝ አምላኬ ነህ። እኔም በሕይወት እስትንፋሴ ሕያው ሆኜ በምኖርበት ዘመኔ ሁሉ ተናግሬ ስለማልፈጽመው ቸርነትህ ለአንተ እገዛልኻለሁ» ማለት ምንኛ ያማረ ነው። ስለዚህም ልቡናችንን ሰብስበን እግዚአብሔር ያደረገልንን ቸርነቱን ምሕረቱንና ፍቅሩን በማሰብና በማስታወስ ከፊቱ እንንበርከክ። ትእዛዛቱንም እንፈጽም። እርሱንም አቤቱ ያደረግህልኝን ቸርነት አልረሳም፣ ፍቅርህና ምሕረትህን በረሳሁ ጊዜ በኃጢአት እወድቃለሁና። የሚያስታውስ ልቡናን ስጠኝ እንበለው።

እግዚአብሔር ትእዛዛቱን ለእኛ ማስታወቁ ለመልካም ነው። ከእኛ ጋራ ሆኖ በእኛ የሚያደርገው ነገር ሁሉ ደግሞ ድንቅ ነው። ከፍ ብለን እንደተመለከትነው እግዚአብሔር ትእዛዛቱን ከመስጠቱ በፊት ፍቅሩንና ቸርነቱን እንድናስብ ያደርገናል። ምክንያቱም ትእዛዛቱን ከቸር አባት እንደተሰጠ ትእዛዝ እንጂ ከበላይ አለቃ እንደተሰጠ መመሪያ እንዳን ቆጥረውና ከፍቅሩም የተነሣ እንድንፈጽመው ስለሚፈልግ። እግዚአብሔር በፍቅር አምላክነቱን ዐውቀንና አምነን እንጂ ከፍርሀት የተነሣ እንድናመልከው የሚሻ አምላክ አይደለም።

ከዚህም ሌላ እግዚአብሔር ምንም እንኳ ኃጢአተኞች ብንሆን ሳይተወን የቸርነቱን ሥራ የሠራልንና እየሠራልንም ያለ መሆኑን እያሰብን እንድናመልከው ያሻል። ለዚህ ነው «ከግብፅ ምድር ከባርነት ቤት ያወጣሁህ እግዚአብሔር አምላክህ እኔ ነኝ» በማለት በትእዛዙ መግቢያ የተናገረው።

«እግዚአብሔር አምላክህ እኔ ነኝ» የሚለው ሐረግም የሚያመለክተው አምልኮን ነው። አምላካችን እግዚአብሔር ነው ማለትን ያስከትላልና። በወንጌል «ለጌታ ለአምላክህ ስገድ እርሱንም ብቻ አምልክ ተብሎ ተጽፏልና» እንደተባለ ማቴ.4፥10።



©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

ኢያሱም ደግሞ «እኔና ቤቴ ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን» እን ዳለ። ኢያ.24፥15። አምልኮ ሲባ ልም ዘወትር በእግዚአብሔር ቤት እየተገኙ መጸለይን፣ መጾምን፣ ቅዱ ሳት መጻሕፍትን ማንበብና መመርመ ርን ወዘተ...የሚያጠቃልል ነው። እነዚህን የአምልኮ መግለጫ የሆኑ የተቀደሱ ምግባራት የማያደርግ ማንም ሰው «እግዚአብሔር አምላክህ እኔ ነኝ» በሚለው ኃይለ ቃል ይወቀሳል። ምክንያቱም አምላኩ የሆነ እግዚአብሔር ሊቆጣጠረው ይገባልና ለእርሱ የሚገባውን አምልኮ ለባለቤቱ መስጠት ይጠበቅበታልና እነዚህ ቃላት ይወቅሱታል።

ማንም ቢሆን ሥርዓተ አምልኮ ውን የሚፈጽመው ተገድዶ አይደ ለም። ስለራሱ ጥቅም ብሎ ነው እንጂ። ይህም በጥሩ ሁኔታ በቅዳሴ ጎርጎርዮስ ተገልጧል። «አቤቱ የእኔ አገልግሎት ለአንተ የሚያስፈልግህ አይደለም የአንተ አምላክነት ለእኔ ያስፈልገኛል እንጂ»

«እግዚአብሔር አምላክህ እኔ ነኝ» የሚለው ሐረግ የፍቅር መግለጫ ነው። እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ያለውን ፍቅር ያመለክታል። እግዚአ ብሔር «ከእንግዲህ ወዲህ ባሮች አልላችሁም...ወዳጆች ግን ብያች ኋለሁ» እንዳለ ወዳጆች እንጂ ባሮች ብሎ አልጠራንም። ዮሐ.15፥15። ከዚህም የተነሣ በጸሎታችን አባታችን ሆይ እንለዋለን። እርሱ አስቀድሞ ወዶናልና እኛም እንወደዋለን። 1ዮሐ.4፥19። እግዚአብሔር ይህን ፍቅር ከቀድሞ ጀምሮ ይሻው ነበረ። ይህንንም በነቢዩ ሙሴ «እሥራኤል ሆይ ስማ አምላካችን እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው። አንተም አምላክህን እግዚአብሔርን በፍጹም ልብህ በፍጹምም ነፍስህ በፍጹምም ኃይልህ ውደድ» ሲል በተናገረው ቃሉ ገልጦታል። ዘዳ.6፥4–6።

እግዚአብሔር በልባዊ ፍቅር ላይ የተመሠረተውን እንጂ የታይታ አም ልኮን አይሻም። እሥራኤላውያንን ስለ ኃጢአታቸው «ይህ ሕዝብ በአፉ ወደ እኔ ይቀርባልና በከንፈሮቹም ያከብረኛልና ልቡ ግን ከእኔ የራቀ ነውና» ኢሳ.29፥13። እንዲሁም ደግሞ በወንጌል «በከንፈሩ ያከብ ረኛል። ልቡ ግን ከእኔ በጣም የራቀ ነው የሰውም ሥርዓት የሆነ ትምህርት እያስተማሩ በከንቱ ያመልኩኛል።» ማቴ.15፥10 በማለት የወቀሳቸውም ለዚህ ነው። እንዴት ልናመልከው እንደሚገባ ሲናገርም ‹ልጄ ሆይ ልብህን ስጠኝ ዓይኖችህም መንገዴን ይወድዱ› ሲል ገልጦታል። ምሳ.23፥26።

በመሆኑም «እግዚአብሔር አምላ ክህ እኔ ነኝ» የሚለው ሐረግ ሰዎች ለእግዚአብሔር እንዲታዘዙና ለእር ሱም እንዲገዙ እንዲያምኑትና እንዲ ያመልኩትም የሚያደርግና የሚያበ ረታታ ሕይወታቸውንም ለእርሱ እንዲሰጡ የሚያስገነዝብ ነው። በዚህ ሁኔታ አምላክነቱን ለሰው ከገለጠ በኋላ ነው ትእዛዙን የሰጠው። ከፍቅር የተነሣ ያደረግሁላችሁን ቸርነት እያሰባችሁ የምታመልኩኝ አምላካ ችሁ እኔ ነኝና «ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ» ሲል አዝ ዟል። «ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ...» ✣

(ይቀጥላል)

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

## ዛሬን ትቶ ነገን መኖር

በዚህች የመከራ ዓለም፣ ዙሪያው ገደል ሆኖ ሰማያት መክራን ቢያንጠበጥቡ፣ ምድርም ችግርን ብቻ የምታበቅል ብትመስል ዛሬን ትተህ ነገን አስበው፤ ወደ አንተ የተዘረጋውን የእግዚአብሔር የምሕረት እጅም ትመለከታለህና። ቅዱሳን አባቶቻችን በሙሉ የኖሩት በዚህ የሕይወት መመሪያ በመመራት ነበረ። የዛሬን ተድላና ደስታ በመተው ነገ የሚያገኙትን የዘላለም ሕይወት ተስፋ አደረጉ። በዚህም ሀብታቸውንና ንብረታቸውን በመተው ከምድረ በዳ ተቅበዘበዙ ዕብ.11፥38። የነገውን ደስታም በማሰብ ለመጋዝ በመሰንጠቅ በእሳት ለመቃጠልና ለአውሬዎች ለመሰጠት ተነዱ።

ልበ አምላክ ዳዊት ነገን በማሰብ ያለምንም ማንገራገር ከሳዖል ፊት ሸሸ፣ ዮሴፍ ከእስር ቤት ነገን በተስፋ ዓይን እየተመለከተ ሲታገስ አባቱ ያዕቆብም ከወንድሙ ከዔሳው ፊት በኮበለለ ጊዜ የጎዘኑ መሸፈኛና የድካሙ ማበረታቻው ነገ እንጂ ሌላ ምንም አልነበረም።

«ዛሬ» ችግርና መከራ የበዛበት፣ መልሶች የጠፉበት የጥያቄ ሣጥን ቢሆንም «ነገ» መልስን ይዞ እንደሚመጣ ተስፋ አድርጎ የወቅቱን ችግር በእምነት ማለፍ መንፈሳዊነት ነው። ምክንያቱም ክርስቲያን ማለት ዛሬን ስለነገ ብሎ የሚኖር፣ ነገን ደግሞ በእምነት መነጽር የሚመለከት የሁለት ዘመን ሰው ነውና። ስለዚህ «ዛሬን» ትተን «ነገን» እንኑር።



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ኪነ ጥበብ

## ሶልያና

በኅሊናዋ ጓዳ እየተመላለሰ እረፍት የሚነሳትን ሃሳብ ለማስወጣት እንዳሰበች ሁሉ በረጅሙ ተነፈሰች። የውስጥ ጭንቀት እምቀት በትኩስ ትንፋሽ ሲወገድ፣ ውስጧን ቀለል ሲለው ተሰማት።

እኩለ ለሊት ማለፉን የሚያበስሩት የመንደሩ አውራ ዶሮዎች ጩኸት መሰማት ሲጀምር ሶልያናም መቀነቷን ማጠባበቅ ገባች። መንገደኛው ልቧ ርቆ ከሄደ ወራት ቢያልፉትም አካሏ ግን ከታፈረው ከተከበረው የአባቷ ግቢ አልወጣም። እናም ተነሳች መስኮቱን በቀስታ ከፍታ ውጪውን ተመለከተችው። ጨለማው ከዛፎቹ ጥላ ጋር ተደምሮ የግቢውን ግርማ አንሮታል። ሰማዩ ላይ የተፈነጣጠቁት ከዋክብት ባትሪ ላይ የተዘረጉ የአልማዝ እንክብሎች መስለዋል። በደመናው የተደበቀችው ጨረቃ አኩኩሉ የምትጫወት ሕፃን ትመስላለች።

ሶልያና ድሃ፣ ሮጣ፣ ወድቃ፣ ተነስታ ያደገችበትን ቤት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ትታ ለመሄድ ስትነሳ ሆዷን ባር...ባር አላት። ልቧ ሲሸፍትባት ታወቃት። አማተበችና «አምላኬ ሆይ አድነኝ» ብላ በመስኮቱ ተንጠላጥላ ወደ መሬት ዱብ አለች። በዚያ በምታውቀው የግቢው የኋላ በር ሾልካ ወጣችና ጤፍ በሚያስለቅመው ጨረቃ ሩጫዋን ተያያዘችው። መጥፋቷ በቤተሰቡ ዘንድ እንደተሰማ የሚፈጠረው ነገር ሲታሰባት የደም ዝውውሯ ፍጥነት፣ የልቧ ምት ሲጨምር ይታወቃታል። ትንሿ ሶልያና የአባቷ ውድ ልጅ...የነገዋ ሙሽራ...የዛሬዋ ኮብላይ...። ለሠርጓ የተደገሰው ድግስ መና ሲቀር፣ እርሷን አግብቶ ለመደሰትና ምንም ማድረግ ለማይችላቸው ጣዖታት ለመገበር የተዘጋጀው እጮኛዋ በንዴት ጠጉሩን ሲነጭ ሁሉም በኅሊናዋ እንደፊልም ክር ተመላለሰባት። እግሯ ግን ጉዞውን አላቋረጠም— ወደ ገዳሙ።

የሶልያና መጥፋት ወሬ እንደተሰማ በቤተሰቡ ዘንድ ታላቅ መደናገጥን ፈጠረ። የፈገግታ ፊቶች በሙሉ የኀዘን ድባብ አጥልቶባቸው ሲታይ ደስታ ግቢውን ረግጦት የማያውቅ አስመሰለው።

የሶልያና አባት ከልጃቸው መጥፋት ባሻገር የሚመጣውን ነገር በሙሉ እያሰቡ ይቆዝማሉ። በእዳ መከበባቸው፣ ውርደት በራቸው ደፍ ላይ ቆሞ ልግባ አልግባ እያለ ሲያመነታ ታያቸው። ንዴትና እልህ ወጥሮ ይዟቸው ሲንጐራደዱ ላያቸው የቆሰለ አንበሳ ነበረ የሚመስሉት። መጠቃትን የማይወደው ልቡናቸው ዛሬ በልጃቸው ሲወጋ ሕመሙ ሁለት ወገን ሆነባቸው። «ምነው ልጄ፣ ምን በደልኩሽ?» አሉ ፊታቸው እንደተቀመጠች ሁሉ በልምምጥ ቃና። እርሷ ግን ርቃለች፣ ላትመለስ ሄዳለች፣ እናም የርሳቸው ሶልያና የሌላ ሆናለች።

አንዳች መግነጢሳዊ ኃይል እንደጐተታቸው ሁሉ ተስፈንጥረው በመነሳት ወደ መኝታ ክፍላቸው ገቡ። ጐራዴያቸውን ከተሰቀለበት አውርደው ከጐናቸው ሻጡት። ንዴት የሚይዙትንና የሚጨብጡትን እያሳጣቸው ወደ ፈረሶች ጋጣ ከሩጫ ባላነሰ አረማመድ ገሰገሱ። የችግር ጊዜ ፈረሳቸውን ጭነው ሶልያንን ለመፈለግ።

ዓይኗን ስትገልጥ በቀጭኑ የሚወጋ ብርሃን ጠቅ ሲያደርጋት ተሰማት። መልሳ ከደነቻቸው። የዓይኗ ሽፋል ላይ አንዳች ነገር እንደተጫነ ሁሉ ከበዳት። ጉሮሮዋ ደርቆ በመሰንጣጠቁ ምላሷን ማንቃነቁ የማይሞከር ሆነ። ያለችበትን ቦታ አለማወቁ ደግሞ ሌላ ችግር ነው።

እንደምንም ብላ ዓይኗን ገለጠችና አካባቢዋን ማጥናት ተያያዘች። በመጀመሪያ ጭል ጭል ከምትል መብራት በስተቀር ምንም አይታያትም ነበረ። ኋላ ግን ዙሪያዋ በግማሽ ወገግታ ሲታጠር አንዲት ጠባብ ክፍል ላይ ዓይኗ አረፈ። ቤቷ ዙሪያዋን በቅዱሳንና በሰማዕታት፣ በእመቤታችንና በጌታችንም ሥዕሎች የተዋበች ናት። ከሥዕሎቹ አካባቢ በቀጭኑ ወደ ላይ የሚወጣው ዕጣን መዓዛ በቤቷ ነግሷል። የመገረም ስሜት ውስጧን አሸንፏት ከድካሟ በረታች። የሰውነቷ ዝለት፣ የጉሮሮዋ ድርቀት ብን ብሎ እንደጠፋ ሁሉ ብድግ ብላ ቁጭ አለች። ወዲያው ከሌላው ማዕዘን የተቀመጠ ሰው እንዳለ አስተዋለች። ግማሽ ፍርሃት ግማሽ ደስታ በሰውነቷ ውስጥ ሲሯሯጥባት፣ ዓይኗ ከመቸውም በላይ ተከፍቶ ያንን ፍጡር መመልከት ያዘች። «ተነሣህ ልጄ» አላት ጉርነን ያለና አንዳች አረጋጊ መንፈስ በውስጡ ያዘለ ድምፅ። «በጣም ደክሞህ ስለነበረ ለረዥም ሰዓታት ራስህን ሳታውቅ ተኛህ።»

ከሴትነት ወደ ወንድነት የመቀየሯ ምሥጢር ግር አላት። የደረሰች ኮረዳ፣ ውበቷ ዓይንን ከሩቅ የሚስብ መሆኗን ራሷም ታውቀዋለች። አሁን ግን «አንተ» መባሏ ድንግር እያላት የሚመጣውን በመጠበቅ ዝም አለች። ከወደ ጨለማው ቀጭን ረዛም ጥቁር ቀሚስ የለበሱ መነኩሴ ብቅ አሉ። በእጃቸው የያዟትን መስቀልም አሳለሟትና ከፊት ለፊቷ ቁጭ አሉ። ✣



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ልናስተዋውቃችሁ

## አንድራቻ መድኃኔዓለም ገዳም

በዚህ እትም ከአዲስ አበባ በስተደቡብ 445 ኪ.ሜ ርቃ ወደምትገኘው በደቡብ ኢትዮጵያ የከፋና ሸኪቾ ዞን ርዕሰ ከተማ ወደሆነችው ወደ ቦንጋ ባደረግነው ጉዞ ከጎበኘናቸው አብያተ ክርስቲያናት ታሪካዊውን አንድራቻ መድኃኔዓለም ገዳም ይዘንላችሁ ቀርበናል።

ቦንጋ በቀድሞ ጊዜ የከፋ ነገሥታት መናገሻ ነበረች። ከተማዋ ዲንቻና ግቻ በሚባሉ ሁለት ታላላቅ ወንዞች የተከበበችና ፈጣሪ በለገሳት ደን የተዋበች ናት። የቦንጋ አናት በሆነው በስተምሥራቅ በኩል ከፍ ብሎ የሚታየው የስብራ ተራራ ግርማ ሞገስዋን የሚያጎላው ከመሆኑም በላይ፣ ከዚሁ ተራራ ተያይዞ ከወደ ሰሜን ምሥራቅ ከከፍተኛ ቦታ ቁልቁል የሚፈሰው የበርታ ፏፏቴ ተፈጥሮዋን ግሩም አድርጎታል።

ይህች ጥንታዊት ከተማ ተዋሕዶ ሃይማኖት ከቀድሞ ጀምሮ የተስፋፋባት ለመሆኑዋ በአካባቢዋ የሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት በቂ ምስክሮች ናቸው። ለዐብነትም ያህል በ1932 ዓ.ም ገዳመ የተመሠረቱት የበሃ ቅዱስ ጊዮርጊስ፣ የእኩት (ኩቲ) ቅዱስ ሚካኤል የጊዱ ቅዱስ ጊዮርጊስ፣ የሻፓ ቅዱስ ገብርኤል፣ የጭሪ ቅዱስ ሚካኤል፣ የዋሻ (ጠሎ) ቅዱስ ሚካኤል አድባራት የሚጠቀሱ ናቸው።

በአንድራቻ መድኃኔዓለም ገዳም ያገኘናቸው አቶ ተፈራ መኩንን የተባሉት አባት ባደረጉልን ገለፃ መሠረት ለመግቢያ እንዲሆን በቤተ ክርስቲያኑ ታሪክ እንጀምራለን።

አካባቢው አንድራቻ ስለሚባል ቤተክርስቲያኑም አንድራቻ መድኃኔ ዓለም ገዳም ተብሎ ይጠራል። ይህ ስም በከፈኛ «ምሥራቾ አንድ ዳቾ» ከተባለለት የወጣ ሲሆን ትርጉሙም ‹የምሥራች አሁን ተገኘ› ማለት ነው። ስያሜው ሊሰጥ የቻለው ቀደም ሲል የከፋ ገዥ ከተማ ለመከተም ፈልገው በአካባቢው ከሚገኙት አሥር ወረዳዎች ቦታ ሲያስመርጡ ይሄ ቦታ ከሁሉ ቅርብና ተስማሚ ሆኖ ስለተገኘ ነው።

አቶ ተፈራ እንደገለፁልን አባ ኃይሉ የሚባሉ መነኩሴ ቤተክርስቲያኑ በታነጸበት በዚህ ቦታ ብቻቸውን በጸሎት ይተጉ ነበር። እኚህ መነኩሴ ራእይ ታይቷቸው ‹ይህ ቦታ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ነው፣ የዘለዓለም የብርሃን ምሰሶ ተተክሎ አይቻለሁ› በማለት የተናገሩና የራእዩን ፍች ሲያስረዱ በአካባቢው ለሚኖሩ ምእመናን የሚሆን ቤተ ክርስቲያን ይሰራበታል የሚል ተስፋ ሰጥተው የነበር በመሆኑ ነው።

ራስ ወልደ ጊዮርጊስ ከአጼ ምኒልክ ተልከው ከሸዋ ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ ሲመጡ ሦስት ጽላት ይዘው ነበር። የቅድስት ሥላሴ፣ የመድኃኔ ዓለምንና የእመቤታችን የቅድስት ማርያምን ጽላት ። ሁለቱ ወደ ሌላ ቦታ ሲወሰዱ የመድኃኔዓለም ጽላት ግን እዚሁ ተቀምጧል። የሕንፃው ሥራ የተጀመረው በ1875 ዓ.ም ሲሆን ሰባት ዓመታት የፈጀው ሥራ ተጠናቆ ታቦተ ሕጉ ወደ መንበሩ የገባውና በደብሩ አገልግሎት መስጠት የተጀመረው በየካቲት 1882 ዓ.ም ነው። የመድኃኔዓለም ጽላት የመጣውም ከጎንደር እንደነበር ይተረካል። ይህንን የገለፁልን አቶ አዋራሽ ዓለሙ አጦን በጎንደር ግንድ አንሣው መድኃኔዓለም በመባል ይታወቅ እንደነበር አስረድተዋል።

ራስ ወልደ ጊዮርጊስ የቤተ ክርስቲያኑን ሕንፃ ከገነቡ በኋላ በአካባቢው የሚኖሩ ካህናትና መነኮሳትን፣ ሌሎች አቅመ ደካማ የሆኑ ክርስቲያኖችን እንዲኖሩበት በማሰብ ከአጼ ምኒልክ ጋር ተነጋግረው አስገደሙት (ገዳም አደረጉት)። ቤተ ክርስቲያኑን ለመሥራት የተጠቀሙበት እንጨት በተለይ ለግድግዳና ለጣሪያ የዋለው ጥርብ (ሣንቃ) የመጣው ከሊሙ ቦተር ልቼ (ጊቤ አካባቢ) ነበር። ቦታው ሩቅ ስለሆነና በዘመኑ ዕቃውን ማጓጓዝ ከባድና አስቸጋሪ የነበረ በመሆኑ የቦተር ሕዝብ ለጅማ የጅማ ሕዝብ ለከፋ በነፍስ ወከፍ በሸክም በማቀባበል ቤተ ክርስቲያኑ ድረስ በማጓጓዝ የአካባቢው ምእመናን ትልቅ አስተዋጽዖ እንዳደረጉ አቶ ተፈራ ተርከውልናል።

በአንድራቻ መድኃኔዓለም ቅጥር ግቢ ውስጥ ከአጸዱ ሥር አረፍ ብለን ታሪኩን ስናዳምጥ ቆየንና ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ለመዝለቅ ከአስጎብኛችን ጋር ተነሳን። አስጎብኛችን አቶ ተፈራ መኩንን የ62 ዓመት አዛውንት ናቸው። በደብሩ ከ1939 ዓ.ም ጀምሮ ቀደም ሲል በዲቁና አሁን ደግሞ በመዘምርነት በማገልገል ላይ መሆናቸውን ገልጸውልናል።

ቤተ ክርስቲያኑ እንደ አብዛኞቹ የሀገራችን ጥንታውያን አድባራት በክብ ቅርፅ የተሠራ ነው። ከውጭ ግርማ ሞገሱን የሚያጎላው ጉልላቱ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

በቀራንዮ አደባባይ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበትን መስቀል ያስታውሰናል። ደብሩ እንደ ሐመረ ኖኅ ሦስት ክፍሎች አሉት። ወደ ውስጥ ስንገባ መጀመሪያ ያየነው የቅኔ ማኅሌቱ መቆሚያ ቦታ እጅግ ማራኪ ነው። የግድግዳው ምርጊት ጠንካራ ከመሆኑ የተነሣ እስካሁን ውበቱን እንደጠበቀ ይገኛል። አቶ ተፈራ እንደገለፁት ግድግዳው የተሰራው በጭቃ ብቻ ሳይሆን ሰወቅቱ በርካታ የከብቶች ቆዳ ተሰብስቦ ለሦስት ዓመታት ያህል በመሬት ውስጥ ተቀብሮ ከተብላላና ከበሰበሰ በኋላ ተቦክቶ የተመረገ ስለሆነ ለዘመናት ሳይረግፍ እንዲቆይ አድርጎታል። የመቅደሱ ዙሪያ ልዩ መንፈሳዊ መስህብ ባላቸው የቅዱሳን ሥዕሎች የተዋበ መሆኑን ያየነው ወደ ቅድስቱ ስንዘልቅ ነው። የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሥነ ስቅለት፣ እመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ልጇን ወዳጇን አማኑኤልን ታቅፋ የተሣለው ሥዕል፣ የቅዱሳን፣ የሰማዕታት፣ የመላእክት፣ የሐዋርያት...የመሣሰሉትን ሥዕሎች በአራቱም ማዕዘናት ኀበኘን፣ በሰዐሊው ዕፁብ ድንቅ ጥበብ ተማርከን ለረጅም ሰዓት ፈዘን ቀረን። እነዚህ ሥዕሎች የተሰሩት በሕንፃው ግንባታ ወቅት ነበር። ሰዓሊው አለቃ ያምሮት ይባላሉ። ሥዕሉ ያረፈበት ሰሌዳ የቡሉኮ ጨርቅ ሲሆን፣ ሥዕሎቹ ያሸበረቁበት ቀለማት የተዘጋጁት ባካባቢው ከሚገኙ ዕፅዋትና ልዩ ልዩ ነገሮች ተቀምመው መሆኑን አስጎብኛችን አስረድተውናል።

ሥዕሎቹ እጅግ በርካታ በመሆናቸው እያንዳንዱን በቃላት ለመግለፅና በዓይነ ኅሊና ለመቅረፅ ይከብዳል። በብሉይ ኪዳን ከተፈፀሙት ዐበይት ተዓምራት አንዱ የሆነው ልዑል እግዚአብሔር ሕዝበ እስራኤልን ከፈርኦን ግዛት ነጻ አውጥቶአቸው፣ ሙሴ እየመራቸው ባሕረ ኤርትራ ሲደርሱ በመልአከ እግዚአብሔር ቅዱስ ሚካኤል አማካኝነት ባሕሩ ሲከፈልና ሲሻገሩ፣ የፈርኦን ሠራዊት በባህር ሲሰጥም የሚያሳየው ሥዕል ግሩም ድንቅ ነው። በሌላ በኩል የሥዕሎቹ ጨርቅ እያረጀ በመምጣቱ በተለይም ወደ ወለሉ አካባቢ ያሉት ሥዕሎች በዕድሜ ብዛት ጨርቁ እየተበታተከ በመሆኑ በሙያተኛ ዕገዛ ጥገና ካልተደረገለት እነዚህ የእምነት መሠረት የሆኑት መንፈሣዊ ሀብቶች በቀላሉ ሊበላሹ ይችላሉ። በዚህ ረገድ የሚመለከተው ክፍል ወይም እገዛ ለማድረግ የሚችሉ ሁሉ አስፈላጊውን ትብብር ካላደረገ ይህ ሃይማኖታዊና ታሪካዊ ሀብት የመበላሸቱ ጉዳይ ይበልጥ የሚያሳስብ ነው።

በአሁኑ ወቅት የቤተ ክርስቲያኑ ሕንፃ በመታደስ ላይ ነው። የእድሳቱ ሥራ በምን ደረጃ እንዳለ አቶ ተፈራን ጠይቀናቸው ሲመልሱ «ቀድሞውኑ በዚህ ቤተ ክርስቲያን ሥራ ላይ በከፋ የሚገኘው ሕዝበ ክርስቲያን ያደረገው ጥረት ከፍተኛ ነው። አሁንም የዕድሳቱ ሥራ በአካባቢው ሕዝብ ርዳታ የሚካሄድ ሲሆን ወጭው ከሕዝቡ አቅም በላይ እየሆነ ስለመጣ የከፋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ዮሴፍ ባደረጉልን ማስተባበር ብር 12000 (አሥራ ሁለት ሺ ብር) ያህል ተሰብስቧል። ጥንትም ከመሰረቱ ጀምሮ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረገው የጅማ ሕዝብ ኮሚቴ አቋቁሞ የእድሳቱን ሥራ ለማስፈፀም ከፍተኛ ትብብር እያደረገ ነው» በማለት ያለውን ሁኔታ አስረድተዋል።

በአንድራቻ መድኃኔዓለም ገዳም ከጥንት ጀምሮ ብዙ ተዐምራት እንደ ተሰሩ ይነገራል። ስለነዚህ ተዐምራት ገለፃ ያደረጉልን አስጎብኛችን እንዲህ ይላሉ።

«ከጣልያን ወረራ ጀምሮ የታዩ ብዙ ተዓምራት አሉ፣ ኰሎኔል ማልታ የሚባል ጣሊያናዊ ጦር አዛዥ ቤተ መቅደሱ ውስጥ ካህናቱ የጦር መሣሪያ ደብቀው ለአርበኞች ሊያቀብሉ ነው የሚል ወሬ ሰምቶ ወደ ገዳሙ ይመጣል። ከዚያም ካህናቱን ሰብስቦ ቤተ መቅደሱን ክፈቱልኝ የደበቃችሁት መሣሪያ ስላለ ገብቼ አወጣለሁ ብሎ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ሲገባ ገና ከአጥሩ መግቢያ ያልታሰበ የጉንዳን ሠራዊት ወጥቶ አባርሮታል። በሌላ ቀን እንዲህ ለመግባት መጥቶ ከአጸዱ ሥር በርካታ የእባብ ሠራዊት ወጥቶ ያባርረዋል፣ ከዚህ በኋላ አንዳንድ ባንዳዎች ካህናቱን አስፈራርተህ እነሱን አስቀድመህ መግባት ትችላለህ ብለው ስለመከሩት፣ ካህናቱን ይዞ እስከ ቅኔ ማኅሌቱ ገብቶ የንጉስ ዘውድና መሣሪያ ያለውን ሁሉ አውጡ ብሎ ያዛል። ካህናቱም ምንም ዓይነት መሣሪያና ዘውድ እንደሌለ ገልፀው፣ ልጅ ኢያሱ የሰጡት ምንጣፍ ብቻ በቤተ መቅደሱ እንደሚገኝ ይነግሩታል። እሱም ምንጣፉን ይወስድና ወደ ቦንጋ ይመለሳል። እጅግ የሚገርመው ሰውዬው ከዚያች ዕለት አለማለፉ ነው። ይኸውም ምንጣፉን በመኝታ ቤቱ አንጥፎ እንደተኛበት ጠዋት የተገኘው ሬሣው ነበር። ከዚህ ሌላ ለብዙ ጊዜ የሚታየው ተአምር ቤተክርስቲያኑ ከመታነጹ በፊት እንደሆነው ከሰማይ እስከ ምድር የተተከለ የብርሃን ምሶሶ ተደጋግሞ ታይቷል። በቅርቡ መስከረም 16 ቀን 1987 ዓ.ም በቤተ ክርስቲያኑ ይህን የብርሃን ምሶሶ ያዩ ሰዎች ከሩቅ ከተለያዩ አቅጣጫ እየሮጡ ይመጣሉ። ዕለቱ የመስቀል ደመራ ዋዜማ ስለነበር በሁኔታው ተገርመው የሆነውን ለማየት ነበር የመጡት። ቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ሲገቡ ግን ብርሃኑ ተሰወረባቸው።»

የገዳሙን ጉብኝት ያጠናቀቅነው ንዋየ ቅድሳቱን ከተመለከትን በኋላ ነበር ጥንታዊ የብራና መጻሕፍት ሆኑ ሌሎቹም ንዋየ ቅድሳት የሚቀመጡት በቄሰ ገበዙ ቤት ነው። ምክኒያቱም በዘመኑ የስርቆት ተግባር እየበዛ በመሄዱ፣ ለጥበቃ እንዲያመች መሆኑ ተነግሮናል። አስጎብኛችንም ኀብስት ባርከው ከመገቡን በኋላ መርቀው ሸኝተውናል። ✥

ወስብሐት ለእግዚአብሔር...



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# የአቡነ ይምዓታ ቤተ ክርስቲያን

አቡነ ይምዓታ ቁጥራቸው በ6ኛው መ/ክ/ዘመን ወደ ኢትዮጵያ ከመጡትና ወንጌልን በመላው ሀገሪቱ ዞረው ካስተማሩት ከ፱ቱ ቅዱሳን ነው። አቡነ ይምዓታ በተለይ ብዙ የቆዩበት በትግራይ ውስጥ ገረዓልታ በሚገኘው ልዩ ስሙ ጉሕ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ነው። የአካባቢውም አሰያየም ከእኚህ ጻድቅ አባት ታሪክ ጋር የተገናኘ መሆኑ ይነገራል። ታሪኩም እንዲህ ነው።

አቡነ ይምዓታ ከአኩሱም ተነስተው «አብ ጐሕ፣ ወልድ ጐሕ፣ መንፈስ ቅዱስ ጐሕ» የሚለውን የቅዳሴ ማርያም ክፍል እያዜሙ ከዛሬው የጉሕ መንደር ነጋባቸው። በዚህም የተነሣ የመንደሯን ስም ‹ይኩን ስምኪ መካነ ጐሕ...› ብለው ሰየሟት።

በዘመን ብዛት ጐሕ በጉሕ ተተክቶ ዛሬ ጉሕ ትባላለች።

የአቡነ ይምዓታ ቤተክርስቲያን ከሐውዜን 13 ኪ.ሜ በመኪና ከተጓዙ በኋላ የግማሽ ሰዓት የእግር መንገድ ተጉዞ የሚገኝ ነው። ቤተክርስቲያኑ ሰማይን እንደ ምሠሦ ደግፈው የቆሙ ከሚመስሉት ረጃጅም የገርዓልታ ተራሮች ውስጥ የሚገኝ ሲሆን አጠገቡ ካልደረሱ የማይታይ የቀደሙት አበው ድንቅ የመንፈሳዊነትና የብርቱነት ውጤት ነው።

ይህ ከባሕር ወለል በላይ 2200 ሜትር ከፍታ ላይ የሚገኘውን የዓለት ተራራ መውጣት በጣም አስቸጋሪ ነው። ምክንያቱም ለመወጣጫ የሚሆኑ ለእጅ መቧጠጫ ለእግር መቆናጠጫ የሚያገለግሉ ጉድጓዶች ብቻ ናቸው ያሉት። ከ240–300 ሜትር ርዝመት ያለው ገደል ቁልቁል ሲመለከቱት እጅግ የሚያስደነግጥና የሚያስፈራ ነው። እ.ኤ.አ በ1960ዎቹ የትግራይ ውቅር አብያተ ክርስቲያናትን እየተዘዋወረች ያጠናችው አይ.ቪ.ፐርስ ስለ ገጠመኟ እንዲህ ትተርካለች። «ጓደኞቿ ቄሰ ገበዙ የቤተ ክርስቲያኑን ቁልፍ ይዘው እስኪመጡ ይጠብቁ ነበር። እኔ እረፍት እየወሰድኩ ቀስ በቀስ ተራራውን ወጣሁ። የምችለውን ያህል እንደወጣሁኝ ከዓለታማው ተራራ ጋር ተፋጠጥሁ። መቀጠል ግን አልቻልኩም።...ዓለቱ በእጅና በእግር የሚያዙ ጉድጓዶች ብቻ ናቸው ያሉት። እጆቼ አጫጭር በመሆናቸው አንዱን ይዤ ከሌላው ለመድረስና እግሮቼም እንዲከተሉ ለማድረግ አላስቻለኝም። መድፈር ስላልቻልኩም መውጣቱን ተውኩና ጥጌን ይዤ ተቀመጥሁ።» በአካባቢው ያሉ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ግን እንዴት እንደሚወጡትም ስትመሰክር «ጓደኞቼ በአርባ ደቂቃ የፈፀሙትን ጠና ያሉት ቄስና ዲያቆናቱ ግን እንደ ሽረሪት እየተንፏቀቁ በሃያ ደቂቃ ውስጥ አጠናቀቁት» ብላለች።

ይህ ቤተ ክርስቲያን በተራራዎች ጉያ የተሸጐጠ በመሆኑ ከግራኝ እና ከጉዲት ጦር ጉዳት ሊያመልጥ ችሏል። አብያተ ክርስቲያናት በሙሉ በተዋሕዶ ጠላቶች ሲቃጠሉና ሲፈርሱ ግማሾቹም በተደጋጋሚ ዝርፊያዎች ሲቸገሩ የአቡነ ይምዓታ ቤተክርስቲያን ግን ይህ ችግር ብዙም የጐዳው አይመስልም።

ይህንን ቤተክርስቲያን ልዩ ከሚያደርጉት መለያዎች አንዱ የሆነው ደግሞ የበርካታ ሰዎች አጽም የተቀበረበት ከዐለት ተፈልፍሎ የተሠራ የመቃብር ሥፍራ መኖሩ ነው። አስደናቂው የመቃብር ሥፍራው ብቻ አይደለም ቀባሪዎቹም እንጂ። ቀባሪዎቹ በመቶዎች የሚቆጠሩ ኪሎሜትሮችን አቋርጠው በመምጣት ተራራ እንደ ዝንጀሮ ተንጠላጥለው በቅዱሱ አባት በአቡነ ይምዐታ ስም በተሰየመው ሥፍራ መቅበር ምእመናኑ ለቦታው ያላቸውን ትልቅ ክብር፣ የእምነታቸውንም ጽናት ያሳያል። ለምሳሌ ያህል አስከሬን ተሸክመው ኩዋጅራት (ደቡብ ምሥራቅ ትግራይ) ተሸክመው 200 ኪ.ሜ አቋርጠው ይቀብሩ ነበር።

ቤተ ክርስቲያኑ ከዓለት ተፈልፍሎ የተሠራ ሲሆን ከውስጥ ራሳቸውን ችለው የቆሙ አራት ዓምዶች አሉት። ጠቅላላስፋቱም 6( )9 ሜትር፣ ከወለል ወደ ጣሪያ ያለው ከፍታ ደግሞ 3 ሜትር ነው።

ቤተ ክርስቲያኑ ድንቅና ልዩ እንዲሆን ያደረገው ከድንጋይ ተፈልፍሎ መሠራቱ ብቻ ሳይሆን በውስጡ ያሉት ቅዱሳት ሥዕሎችም ናቸው። በቅኔ ማኅሌቱ ጣሪያና ግድግዳ የሚታዩት ደማቅ ሥዕሎች ተከታታይ ታሪኮች የያዙ ናቸው።

የአቤል፣ የኖኅ፣ የአብርሃም፣ የይስሐቅና የያዕቆብ ሥዕሎች ደምቀው ይታያሉ። ከዚህም በተጨማሪ በቅኔ ማኅሌቱ ጣሪያ ላይ የ፱ቱ ቅዱሳን ሥዕል ይታያል። ሦስቱ መስቀል፣ አምስቱ ደግሞ መጻሕፍት እንደያዙ ሲሆን አንደኛው ግን ባዶ እጃቸውን ናቸው። አቡነ ይምዓታ በፈረሳቸው ላይ ተቀምጠው፣ እና የአቡነ አሮን፣ የአቡነ ማትያስ፣ የአቡነ ቢንያምና የአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ሥዕሎች የቤተ ክርስቲያኑ የዘመናት ጌጦች ናቸው።

ሥዕሎቹ በጣም ደማቅ በመሆናቸው ብዙ ክፍለ ዘመናትን አልፈው የመጡ ድንቅ ቅርሶች አይመስሉም። በብዙ ጥንታውያን የቤተ ክርስቲያናችን ግድግዳዎች ላይ እንዳሉት ወይም በዕቃ ቤት ተዘግቶባቸው በዝናብና በጥንታቄ ጉድለት እንደተበላሹት ሥዕሎች ያልተበላሹ ደማቆች፣ ውበታቸው ያልጠገገ መኩሪያዎች ናቸው። አንዳንድ የሥነ ሥዕል ሊቃውንት በ15ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ተስለዋል ብለው የሚገምቷቸው እነዚህ ሥዕሎች ውብና ማራኪ ናቸው።

የአቡነ ይምዓታ ቤተ ክርስቲያን ሀገራችንን በዓለም ደረጃ ካሳወቋት የውቅር ዓለት አብያተ ክርስቲያናት አንዱ ነው።

ይህ ትውልድም ታሪኩንና ማንነቱን ለማወቅ ዘወር ብሎ ያለፈ የአባቶቹን ሥራ መመርመር ይጠበቅበታል።

ኋላውን ያጠና፣ የፊቱን መገንዘብ ይችላልና። የአባታችን የአቡነ ይምዓታ ጸሎትና አማላጅነት አይለየን፣ አሜን። ✣

(ምንጭ – ክልል አንድ ቱሪዝም ቢሮ)



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# አፌን በምሳሌ እከፍታለሁ!

መዝ.77፥2

● «ዕንቁአችሁን በእሪያዎች ፊት አታኑሩ በእግራቸው እንዳይረግጡት ተመልሰውም እንዳይነክሱአችሁ» ማቴ.7፥6።

እሪያ መልከ ጥፉ ነው። ዕንቁ በፊቱ ቢያኖሩ ዕንቁው እንደመስተዋት መልክን ስለሚያሳይ የራሱን መልክ ዓይቶ በራሱ መልክ ጥፉነት ደንግጦ ሲሄድ ይሰብረዋል።

እንደዚሁም ሁሉ ዕንቁ ባሕርይ የሆነው ጌታ በአይሁድ ፊት ቆሞ እናንተ ጸሐፍት ፈሪሳውያን ወዮላችሁ እያለ በገዛ ኃጢአታቸው ቢዘልፋቸው ውስጣዊ ኃጢአታቸውን ግልጽ አድርጐ ስላሳያቸው ጠልተው ተመቅኝተው ሰቅለው ገድለውታልና።

ዛሬም በእምነት ለማይመስሉአችሁ መናፍቃን ዕንቁ ሃይማኖታችሁን አትንገሩ እንዳይነቅፉት።

✥ ✥ ✥

● «የበግ ለምድ ለብሰው ከሚመጡባችሁ በውስጣቸው ግን ነጣቂዎች ተኩላዎች ከሆኑ ከሐሰተኞች ነቢያት ተጠንቀቁ።» ማቴ.7፥15።

እውነተኞች መስለው ከሚመጡ ከሐሰተኞች፣ ሃይማኖታውያን መስለው ከሚመጡ መናፍቃን፤ መንፈሳውያን መስለው ከሚመጡ ከሥጋውያን መምህራን (ሰዎች) ተጠበቁ። ቢመረምሯቸው ሰውን እየነጠቁ ወደ ገሃነም የሚያወርዱ ናቸውና።

ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ ለሰብአ ቆሮንቶስ በላካት በሁለተኛው ክታቡ የጌታን ምሳሌያዊ አነጋገር እንዲህ ተርጉሞታል። «እንደዚህ ያሉ ሰዎች የክርስቶስን ሐዋርያት እንዲመስሉ ራሳቸውን እየለወጡ ውሸተኞች ሐዋርያትና ተንኮለኞች ወረተኞች ናቸውና። ይህም ድንቅ አይደለም ሰይጣን ራሱ የብርሃንን መልአክ እንዲመስል ራሱን ይለውጣልና። እንግዲህ አገልጋዮቹ ደግሞ የጽድቅን አገልጋዮች እንዲመስሉ ራሳቸውን ቢለውጡ ታላቅ ነገር አይደለም። ፍጻሜያቸው እንደ ሥራቸው ይሆናል።» 2ቆሮ.11፥13–15።

✥ ✥ ✥

● «በአረጀ ልብስ አዲስ እራፊ የሚያኖር የለም። መጣፊያው ልብሱን ይበጥቀዋልና።

መቀደዱም የባሰ ይሆናል። በአረጀ አቁማዳ አዲስ የወይን ጠጅ የሚያኖር የለም። ቢደረግ ግን አቁማዳው ይፈነዳል። የወይን ጠጁም ይፈሳል አቁማዳውም ይጠፋል፣ ነገር ግን አዲሱን የወይን ጠጅ በአዲስ አቁማዳ ያኖረዋል። ሁለቱም ይጠባበቃሉ።» ማቴ.9፥16–17።

ጌታ ይህን የተናገረው «ደቀ መዛሙርትህ ለምን አይጦሙም» ብለው ለጠየቁት ጥያቄ መልስ ሲሰጥ ነው። በአረጀ ልብስና በአረጀ አቁማዳ የመሰለው ገና በልጅነት ያልታደሰ ሰውን የሐዋርያት ሰውነት ነበር። በአዲስ ሕይወት ባልታደሰ ሰውነታቸው ሕግ ጠብቁ ቢሏቸው ሕጉም ይፈርሳል ሰውነታቸውም ይጐዳል ገና በሃይማኖት አልጠነከሩምና።

✥ ✥ ✥

● «እንደ እባብ ልባሞች እንደ ርግብም የዋሆች ሁኑ» ማቴ.10፥16።

የእባብ ብልሃቱ ምንድነው?

እባብ:-

ሀ. ከመንገድ ዳር ሲተኛ ራሱን ቀብሮ ይተኛል። እናንተም ራሳችሁን እኔን («የሰው ሁሉ ራስ ክርስቶስ ነውና። 1ቆሮ.11፥3)። አትካዱኝና ለተለያየ ጥቅም አሳልፋችሁ አትስጡኝ ሲል ነው።

ለ. ውኃ ሲጠጣ በምላሱ ላይ ያለውን መርዝ በየብስ አኑሮ ነው። ያለበለዚያ ከውኃው የገባ እንደሆነ መርዙ በሰውነቱ ተሰራጭቶ ያጠፋዋል።

ክርስቲያንም ተንኮል፣ ቂም፣ በቀል በልቡ ይዞ ሕይወትን የሚያረካውን የእግዚአብሔር ቃል ቢሰማ ወይም የጌታን ሥጋና ደም ቢቀበል ልቦናውን ከቂም ከበቀል ሳያጠራ ተቀብሏልና የገዛ ኃጢአቱ ሕይወቱን መርዞ የዘላለም ሞት ያስከትልበታል።

ሐ. በጥፋት ውኃ ጊዜ ኖኅ እንስሳትን ለዘር በመርከብ ውስጥ ሲያስገባ እርሱንም አስገብቶት ነበር። አፉን ከፍቶ ሳለ ርግብ ዋሻ መስሏት ገብታ ዕንቁላሏን ጣለች እሷን የበላኋት እንደሆን ኖኅ አስወጥቶ በፈላ ውኃ ውስጥ ይጥለኛል ብሎ ርግቧ እስክትወጣ አፉን እንደከፈተ ቆይቷል።

እናንተም ከፊታችሁ ያለውን የሚባለውን ብቻ ዓይታችሁ የሚያመጣባችሁን መጥፎ ነገር ሳትመረምሩ ለጊዜያዊ ደስታና እርካታ ብላችሁ ራሳችሁን የሚያጠፋ ሥራ አትሥሩ ሲል ነው።

መ. ጥግ ሳይዝ አይጣላም – የክርስቲያን መሸሸጊያው መከታው (ጥጉ) ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። የክርስቶስን ኃይል መከታ ያላደረገ ክርስቲያን ለድል አይበቃም። ሐዋርያው «ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ» እንዳለ ፊል.4፥13። ኃያል አምላክ ክርስቶስን መጠጊያ አድርገን ባለጋራችን ዲያቢሎስን ልንዋጋ ይገባናል።

ሠ. ዕፀ ዘዌ የሚባል አለ። እባብ ፍሬውን ይወደዋል። ጥላው ሲያርፍበት ግን ያደክመዋል። ለጠላቶቹም ያጋልጠዋል። ብልህ ስለሆነ ጥላው እንዳያርፍበት ጧት በምሥራቅ፣ ማታ በምዕራብ ሆኖ ፍሬውን ይመገበዋል።

እኛም ልናገኘው የምንመኘውን ነገር ለማግኘት ብለን ለጠላታችን ለዲያብሎስ ተጋልጠን መሰጠት የለብንም እንደ እባቡ የምንሻውን በብልሃት ከሃይማኖታችን ሳንናወጥ የምናገኝበትን ዘዴ መዘየድ ያሻል ሲል ነው። ✥



©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

ንስሐ በነቢያትም በሐዋርያትም የተሰበከ የክርስቲያኖች የሕይወት ዋስትና የሆነ ድንቅ ምሥጢር ነው። አዳም ከበደለ በኋላ በሠራው ሥራ ተጸጽቶ ንስሐ ቢገባ ከልጅ ልጁ ተወልዶ፣ ሰው ሆኖ እንደሚያድነው ቃል ተገባለት። ሕዝበ እስራኤል የእግዚአብሔርን ቸርነትና አባትነት በመዘንጋት ድንጋይ አለዝበው

## ንስሐ ለምን እና እንዴት?

ተሾመ አይቼው (ከባሕር ዳር)

እንጨት ጠርበው ሰግደው ከእምነታቸው ሲለዩ ዳግም ቃል ኪዳናቸውን ያደሱት በንስሐ ነው።

ነቢየ እግዚአብሔር ኢሳይያስ ‹ንስሐ ግቡ፥ ልባችሁንም መልሱ... የቀድሞውን የጥንቱን ነገር አስቡ...› ብሏል። ኢሳ.46፥9። ሕዝቅኤልም ‹ንስሐ ግቡ ኃጢአትም እንቅፋት እንዳይሆንባችሁ ከኃጢአታችሁ ሁሉ ተመለሱ› በማለት ሰዎች ከአምላካቸው ተለይተው እንዳይቀሩ የንስሐን መንገድ አሳይቷል። ሕዝ. 18፥30 ጌታችንም የትምህርቱ መጀመሪያ ያደረገው ንስሐን ነው። ማቴ.4፥17።

ወደ ዘመናችን የክርስትና ሕይወት ስንመለስም ብዙ ሰዎች የንስሐ አባት አላቸው እንጂ ንስሐ አይገቡም። ይህንንም ትምህርት እንደ ጦር የሚፈሩ ቀላል አይደሉም። ስለዚህም የንስሐን ምሥጢር እንድንረዳው ምንነቱን በዝርዝር እንመለከተዋለን።

### ንስሐ ማለት

1. ወደ እግዚአብሔር መመለስ ነው። ሰውን በአርአያው በአምሳሉ ፈጥሮ የመጀመሪያውን ግንኙነት የጀመረው ሰው ሳይሆን እግዚአብሔር ነው። ነገር ግን በኋላ የመጣ ኃጢአት ሰውንና እግዚአብሔርን ለያየው። ዛሬም ኃጢአት የሚሠራ በሙሉ ከእግዚአብሔር የተለየ ሲሆን ንስሐ የገባ ደግሞ ወደ አምላኩ ተመልሷል ማለት ነው። ከግንዱ የተለየች ቅርንጫፍ እንደቀድሞው አብባና ለምልማ እንድትኖር ከግንዱ ጋር በአንድነት መኖር እንዳለባት ሁሉ ክርስቲያንም በመንፈሳዊ ሕይወቱ ሕያው እንዲሆን ንስሐ መግባት አለበት። ዮሐ.15፥1።

እግዚአብሔር አምላክም አስቀድሞ በነቢዩ አንደበት «ወደ እኔ ተመለሱ፣ እኔም ወደ እናንተ እመለሳለሁ» ሚልክ.3፥7 ብሎ ንስሐ የሰው ወደ እግዚአብሔር መመለስ፣ እግዚአብሔርም በምሕረትና በቸርነት ሰውን መጐብኘት መሆኑን አስተምሮናል።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ትምህርቱ እንዳስተማረው «የጠፋው ልጅ» ሀብት ንብረቱን ከተካፈለ በኋላ በመጀመሪያ የተለየው ከአባቱ መሆኑን ማስተዋል ያስፈልጋል። ልጅ፥ የሰዎች፣ አባት– የእግዚአብሔር ምሳሌ። ሉቃ. 15፥11–24።

ስለዚህ ወደ እግዚአብሔር መመለሳችን እውነተኛና ትክክለኛ ይሆን ዘንድ ንስሐ እንግባ።

2. ወደ እውነተኛው የክርስትና ሕይወት መግባት ነው። ክርስትና በጥምቀት የጸጋ ልጅነትን በማግኘት የሚጀመር፣ ሥጋውንና ደሙን በመቀበል የሚጸና፣ በጾምና በጸሎት የሚጠበቅ በንስሐ የሚታደስ ሕይወት ነው። ዘወትር በኃጢአቱ በመፀፀት ንስሐ የሚገባ ክርስቲያን ወደ እውነተኛው የክርስትና ሕይወት የገባ ራሱንም ሙሉ በሙሉ ለአምላኩ የሰጠ ነው። አንዳንድ ሰዎች ግን ንስሐ ላለመግባት አሻፈረኝ የሚሉት በልቡናቸው ያልተፈጸመ የኃጢአት ፍቅር፣ የሚያስተናግዱት ብዙ እንግዳ ስላለባቸው ነው። እንደዚህ ዓይነት ሰዎች መንፈሳዊ (ዊት) መስለው ቢመላለሱም መንፈሳዊነትን ግን አልጀመሩትም። ለአብነትም የሲሞን መሠሪይን ታሪክ መጥቀስ ይቻላል። የሐዋ.8፥14–25።

አምኖ የተጠመቀ፣ ወደ ክርስትናም ሕይወት የገባው ሰው ለሐዋርያት ገንዘብ በማሳየት፣ እጄን የምጭንበት ሁሉ መንፈስ ቅዱስን ይቀበል ዘንድ ለእኔ ደግሞ ይህን ሥልጣን ስጡኝ አላቸው። ይህ ሰው መመለሱ ውስጣዊና እውነተኛ ሳይሆን አፍአዊና ለታይታ መሆኑን ግብሩ ገለጸበት። መመለሳችን እንዲህ ዓይነት እንዳይሆን ንስሐ እንግባ።



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

3. ከሞት ወደ ሕይወት መሸጋገር ማለት ነው። ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ የኃጢአት ደሞዝ ሞት ነው ብሎ እንዳስተማረው ሁሉ በኃጢአት የነበረ ሰውም ንስሐ ገብቶ ወደ አምላኩ ሲመለስ ከሞት ወደ ሕይወት ተሸጋገረ ማለት ነው። ዛሬም በክርስትና የሌሉ፣ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አምነው ያልተጠመቁ፣ በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ትምህርት የማይመሩ፣ በቃለ ወንጌል ያልታነፁ በሙሉ በሞት እንደሚመላለሱት ሁሉ ትእዛዘ እግዚአብሔርን የጣሱ ከንስሐ የተለዩም በሙሉ መንገዳቸው የሞት ጐዳና ነው።

የአባቱን ሀብት ንብረት ይዞ የኮበለለው ልጅ (ወደ አባቱ) በተመለሰ



የጠፋው ልጅ (ሉቃ.15፥24)

ጊዜ አባቱ የተናገረው ቃል ለርእሳችን ማረጋገጫ ይሆነናል። «ይህ ልጄ ሞቶ ነበርና ደግሞም ሕያው ሆኖአል» ቁ.23።

ከእግዚአብሔር መለየት ሞት፣ ወደ እርሱም በንስሐ መመለስ ሕያውነት ነውና።

4. ከኃጢአት ባርነት ነጻ መውጣት ነው። በኃጢአት መመላለስ፣ ንስሐ ላለመግባትም አሻፈረኝ ማለት የኃጢአትን ሕይወት መቀበል፣ በሰይጣንም ባርነት መያዝን መፍቀድ ማለት ነው። መጽሐፍ... «ልጁ አርነት ያወጣችኋል...» (ዮሐ.8፥37)። እንዳለ ክርስቲያን ከባርነት አርነት የወጣ፣ እግዚአብሔርን አባቴ ሆይ ብሎ የሚጠራ እንጂ የሰይጣን ባሪያ አይደለም። ስለዚህም ንስሐ የሚገባ ሰው ከሰይጣን ባርነት የእግዚአብሔርን ልጅነት፣ ከሲዖልም ገነትን የመረጠ ነው።

ንስሐ ስንገባ ከእግዚአብሔር የሚለየን ሱስና የሥጋችን ፍላጐት ላይ አምፀን «ከእንግዲህ እኔ የእግዚአብሔር ነኝ» ብለናል ማለት ነው። ስለዚህም ንስሐ እንግባ።

5. ስለ ፍቅረ እግዚአብሔር ብሎ ኃጢአትን መተው ነው። የክርስትና ሕይወት በፍቅር የተሞላ ነው። አምላካችንን ከመንበሩ ስቦ ለመስቀል ሞት ያበቃውና ሰውንም ደግሞ ከኃጢአት ዓለም፣ ከሥጋዊ ምቾትና ድሎት ጐትቶ ለመከራ ሥጋ ለሰማዕትነት የሚያበቃው (የሚያደርሰው) ይኸው ፍቅር ነው።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ብትወዱኝስ ትዕዛዜን ጠብቁ» (ዮሐ.14፥15)፣ በተጨማሪም «ትእዛዜን ብትጠብቁ በፍቅሬ ትኖራላችሁ» እንዳለ (ዮሐ.15፥10)። ምእመናንም በመስቀል የሞተውን አምላክ በማሰብ ሕይወታቸውን በፍቅር ይመራሉ። የእግዚአብሔርንም ፍቅር በማሰብ ንስሐ ይገባሉ። ይህንንም ግልጽ ለማድረግ ንስሐ የሚመስሉ ነገር ግን ያልሆኑ ምሳሌዎችን እንጥቀስ።

ሀ. ለኢኮኖሚ ቁጠባ ብቻ ብሎ ኃጢአትን መተው ንስሐ አይደለም፣ ስካር የቤቱን ኑሮ ያናጋበት፣ ሲጋራ ማጤስና ጫት መቃም የደሞዙን ዋልታ ያነቃነቀበት በዚሁ ተመርሮ እርግፍ አድርጐ ቢተው ንስሐ ገባ አይባልም። ነገር ግን የተቀደሰውን ሰውነቴን በኃጢአት አበላሸሁት ብሎ ተጸጽቶ ለመምህረ ንስሐው ቢናዘዝ ግን ንስሐ ይሆናል።

ለ. በፍርሐት ምክንያት ኃጢአትን መተው።

ሰማይንና ምድርን የፈጠረውን እግዚአብሔርን ሳይሆን ምድራዊ ፍጡርን ወይም በሽታን ፈርቶ ኃጢአትን መተው ንስሐ አይደለም። ለምሳሌ መድኃኒት ያልተገኘለትን የኤድስ በሽታ በመፍራት ከዝሙት ብቻ መራቅ በራሱ ንስሐ አይባልም። ምክንያቱም መድኃኒት ተገኘለት ቢባል ወደ ኃጢአት መመለስ ሊመጣ ይችላልና። ስለዚህ መፍራት የሚገባው ሁሉን የፈጠረ እግዚአብሔርን ነው። ምሳ.1፥7።



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ሐ. በጊዜ እጥረት ምክንያት ኃጢአትን መተው።

ብዙ ሰዎች ለዕለት ጉርስ ለዓመት ልብስ በሚያደርጉት ሩጫ ጊዜ አጥተው ሊውሉ ሊያድሩ በዚህም ምክንያት ኃጢአትን ሊተዉ ይችላሉ። በእስር ቤት ያለ እስረኛ፣ በደዌ ዳኛ፣ በአልጋ ቁራኛ የተያዘ በሽተኛ ከገጠመው ፈተና አልፎ ተርፎ ሌላ ኃጢአት ባይሠራ ያ ብቻውን እንደ ንስሐ ተቆጥሮለት መንፈሳዊ ሰው አያሰኘውም።

አንድ ሰው መንፈሳዊ የሚሆነው «ኃጢአትን ስለ እግዚአብሔር ፍቅር ብሎ» ሲተው ዕድሜውንም በሙሉ በፈሪሃ እግዚአብሔር ታንፆ የኖረ እንደሆነ ብቻ ነው።

6. ንስሐ ኃጢአትን ላይመለሱበት መተው ነው።

ጥበበ እግዚአብሔር የተገለጠለት ሰሎሞን «ጻድቅ ሰባት ጊዜ ይወድቃልና፣ ይነሣል...»(ምሳሌ 24፥16) እንዳለ በክርስትና መመላለስ በመከራ መኖር፣ መነሣት መውደቅም ስለሆነ መበደል ይኖራል። ነገር ግን ነገ ንስሐ እገባለሁ ብሎ ዛሬ ኃጢአትን መሥራት በእግዚአብሔር ላይ መቀለድ ይመስላል። ሐዋርያውም «አትሳቱ እግዚአብሔር አይዘበትበትም» ማለቱን ማስታወስ ያስፈልጋል።

ስለዚህ ወደ ንስሐ የሚቀርብ ሰው ዛሬ የተፀፀተበትን ኃጢአት ላለመድገም በመቁረጥ ንስሐ መግባት ይገባዋል። ይህ ማለት ደግሞ ንስሐ አይደገምም ማለት አለመሆኑን ማስተዋል ያስፈልጋል። በአጠቃላይ ወደ መምህር ንስሐ ሲቀረብ ዳግም ላለመበደል ለራስ ቃል በመግባት፣ ኃይል የሚሰጠውን አምላክ በመማጸን፣ የቅዱሳን አማላጅነትና ተራዳኢነትም በመተማመን መሆን ይገባዋል።

7. ንስሐ ዘላቂ የሆነ የባሕርይ ለውጥ ማምጣት እንጂ ጊዜያዊ ቁጥብነት አይደለም። ክርስትና ለአንድ ሰሞን በወረት ብቻ የምንመላለስበት ወራቱም ሲያልቅ እርግፍ አድርገን የምንተወው የኮንትራት ጓደኝነት አይደለም። በጥምቀት የሚጀመር፣ በተጋድሎ የሚጸና በክብር የሚፈጸም የሕይወት መንገድ ነው። አንዳንድ ሰዎች ግን ለአንድ ሰሞን ብቻ በስሜታዊነት በመገፋፋት ፍጹማን መስለው ይታዩና ከአፍታ በኋላ ግን ቀድሞ ከነበሩበት የኃጢአት ሕይወት የባሰ አዘቅት ውስጥ ተዘፍቀው ይገኛሉ።

ንስሐ ማለት ግን ያለፈ የኃጢአትና የጨለማ ሕይወትን ሙሉ በሙሉ ፍቆ በመጣል የጽድቅና የብርሃን ሕይወትን መጀመር ያንንም አጽንቶ መጠበቅ ነው። ንስሐ የገቡ ሰሞን ከኃጢአት መራቅ፣ በቤተ ክርስቲያን ንጹሕ መስሎ መታየት፣ ጊዜ ሲረዝም እንዲሁም ከቅጽረ ቤተ ክርስቲያን ስንርቅ ግን የሥጋን ፈቃድ መፈጸም፣ በሰይጣን መንገድ መመላለስ አይገባም። ስለዚህ ንስሐ የምንገባው ዘላቂ የሆነ ለውጥ ለማምጣት አስበን መሆኑን መገንዘብ ይገባናል። ከንስሐ በኋላ አነጋገራችን፣ አኗኗራችን፣ አካሄዳችን በሙሉ ይስተካከላል። ጸባዩ ነው ወይም ተፈጥሮዬ ነው ብለን የምንተወው ምንም ባዕድ ጠባይ አይኖረንም።

## ማጠቃለያ

ዓይን ያላያትን፣ ጆሮ ያልሰማትን፣ እግዚአብሔር ለወዳጆቹ ያዘጋጃትን ቅድስት ሀገር ለመውረስ በምናደርገው መንፈሳዊ ጉዞ ንስሐ ቁልፍ መሆኑን በመገንዘብ ሕይወታችንን እንመሥርትበት። በመስቀል ሞት ያዳነን አምላካችን ፍቅሩ ወሰን የለውምና ዳግም ብንበድል እንኳን ጠፍተን እንዳንቀር የንስሐን በር ከፍቶልናልና እንዳንበት። በዚሁም ከዚህ ክፉ ዓለም ራሳችንን እናድን። የሐዋ.2፥40። በተጨማሪም

- ንስሐ ለመግባት ምን ማድረግ አለብን?
- ንስሐችንንስ እንዴት እንናዘዝ?
- ከንስሐ በኋላ ያለ ሕይወትስ ምን መምሰል አለበት?
- የንስሐ ፍሬስ ምንድነው? ❖

ይቆየን!

ወለእግዚአብሔር ስብሐት

(ይቀጥላል)

## ብሂለ አበው

በሀገረ ሮማ በዘመነ ዑልያኖስ የነበሩት ወንድማማቾቹ ቅዱሳን አበው ባስልዮስና ጎርጎርዮስ (ዘኑሲስ) በክርስትናቸው ምክንያት ወደ ወኅኒ ተጥለው፣ በሮችም ተዘግተውባቸው ነበረ። መምለኬ ጣዖት ዑልያኖስም ወደ ጦርነት ከመሄዱ በፊት ቅዱስ ባስልዮስን አስጠርቶ ለጣዖቱ እንዲሰግዱ አለበለዚያ ግን መከራ እንደሚያጸናባቸው ሲያስጠነቅቀው «አንተ ባለፍየል ጢም (ሽማግሌ) የጠራቢውን ልጅ አምላክህን የት ተውከው?» አለው። ቅዱስ ባስልዮስም በትሕትና «ሰማእታት የሚቀበሩበትን ሣጥን ሲጠርብ ሳለ ተውኩት» ሲል መለሰለት።

(ስንክሳር – ኅዳር 25 ቀን።)



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# በጸጋው መዳን እንዴት ነው?

ዲ. ደጀኔ ሺፈራው (ካለፈው የቀጠለ)

2. ልጅነትን ጸጋ ይላታል ሀ.«ወደዚህ ጸጋ በእምነት መግባት አግኝተናል። በእግዚአብሔር ክብርም እንመካለን።» ሮሜ.5፥2። ይላል። በእርሱ የባሕርይ አምላክነት አምነን፥ ወደ ልጅነት ተመርተን የሄድንበት፥ ያገኘናት፥ ወድቀን የተነሣንባት፥ ደክመን የበረታንባት፥ ልጅነት መመኪያችን ናት በልጅነትም እግዚአብሔር የሚያወርሰንን ርስት ተስፋ እናደርጋለን ማለት ነው።

ለ. «እንደተሰጠንም ጸጋ ልዩ ልዩ ስጦታ አለን።» ሮሜ.12፥6። እንደ ዚህም ከሆነ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተሰጠን ልጅነት አለን፥ ሀብቱም ልዩ ልዩ ነው፥ ማለት ነው።

3. ሐዋርያነትን ጸጋ ይለዋል። «እንግዲህ ልጄ ሆይ አንተ በክርስቶስ ኢየሱስ ባለው ጸጋ በርታ።» 2ጢሞ. 1፥5። ቅዱስ ጳውሎስ ጢሞቴዎስን፥ ኢየሱስ ክርስቶስ በሾመህ ሐዋርያነት ጸንተህ ኑር ሲለው ነው።

4. ባለሟልነትን ጸጋ ይለዋል። በእግዚአብሔር ፊት ሞገስ ያገኘ ሁሉ የእግዚአብሔር ባለሟል ይባላል። «ፍለጋ የሌለውን የክርስቶስን ባለጠግነት ለአሕዛብ እሰብክ ዘንድ... ከዘላለም የተሰወረው የምሥጢር ሥርዓት ምን እንደሆነ ለሁሉ እገልጥ ዘንድ ይህ ጸጋ ከቅዱሳን ሁሉ ይልቅ ለማንስ ለእኔ ተሰጠ።» ኤፌ.3፥8። ይህ ባለሟልነት ለእኔ ተሰጠ ማለቱ ነው። በዚያውም «ከቅዱሳን እናንሳለን።» ማለትንም አስተምሮናል።

5. ቸርነቱን ጸጋ ይላታል። ሀ. «ያዳነን በቅዱስም አጠራር የጠራን እግዚአብሔር ነውና፥ ይህም እንደ ራሱ አሳብና ጸጋ መጠን ነው እንጂ፥ እንደ ሥራችን መጠን አይደለም።» 2ጢሞ.1፥8። ከፍርሃት፣ ከድካም ያዳነን፥ በልዩ አጠራር የጠራን፥ እግዚአብሔር ነው፥ የጠራንም በቸርነቱ ነው እንጂ በሙያችን በጉልበታችን ወይም በጥበባችን አይደለም ማለት ነው። በመሆኑም እኔ ዐዋቂ፥ ባለሙያ፥ ጥሩ ተናጋሪ፥ ጉልበታም፥ የምግባር ሰው፥ ንጹሕ፥ ቅዱስ ስለሆንኩ ነው፥ ለአገልግሎት የተጠራሁት አንበል።

ለ. «ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጐድሎአቸዋል። በኢየሱስ ክርስቶስም በሆነው ቤዛነት እንዲያው በጸጋው ይጸድቃሉ።» ሮሜ.3፥23። ሐዋርያው በዚህ መልእክቱ፥ አይሁዳዊ በአሪቱ፥ አረማዊ በጣዖቱ ብሎ አልለየም። ነቢዩ ዳዊት «ሁሉ ዐመፁ፥ በአንድነትም ረከሱ።» መዝ.13፥3። እንዳለው ሁሉ በድለዋልና አለ እንጂ። ሁሉ የተባሉት አይሁዳዊውም አረማዊውም ናቸው። ምክንያቱም አይሁድም ሆኑ አሕዛብ ከኃጢአት ነፃ አልነበሩምና። እግዚአብሔርንም ማገልገል በመተዋቸው እግዚአብሔር ሊሰጣቸው ያለውን ክብር አጥተው ነበርና። ስለዚህ ሁላችሁም በኢየሱስ ክርስቶስ ካሣ ድኅነትን አገኛችሁ፥ በቸርነቱ ዳናችሁ ሲል ጻፈላቸው።

ቅዱስ ጳውሎስ ይህን የጻፈበት ምክንያት ነበረው። አይሁድ አሕዛብን፥ ጣዖትን በማምለክ የሠሩትን ኃጢአት፥ እግዚአብሔርን ባለማወቅ የበደሉትን በደል እየቆጠሩ ይወቅሷቸው ነበር። ይህም በጥምቀት ከአሕዛብ ጋር አንድ የመሆናቸው ምሥጢር ስላልተዋጠላቸው ነው። አግዚአብሔርም የእነርሱ ብቻ አምላክ እንደሆነም ያምኑ ስለነበረ ነው። ከዚህ በማከታተልም «ትምክህት እንግዲህ ወዴት ነው? እርሱ ቀርቶአል። በየትኛው ሕግ ነው? በሥራ ሕግ ነውን? አይደለም። በእምነት ሕግ ነው እንጂ። ሰው ያለ ሕግ ሥራ በእምነት እንዲጸድቅ እንቆጥራለንና። ወይስ እግዚአብሔር የአይሁድ ብቻ አምላክ ነውን? የአሕዛብስ አምላክ አይደለምን? አዎን የተገረዘን ስለ እምነት፥ ያልተገረዘንም በእምነት የሚያጸድቅ አምላክ አንድ ስለሆነ የአሕዛብ ደግሞ አምላክ ነው። አንግዲህ ሕግን በእምነት እንሽራለን? አይደለም፥ ሕግን እናጸናለን እንጂ።» ሮሜ.3፥27–31። ብሎ ጻፈላቸው። በዚህም ሕግ ስንፈጽም ኖረናል፥ ብለው ሕግ ባልተሰጣቸው አሕዛብ ላይ እንዳይመኩ አስተማራቸው። ሕጉን ሳይሆን በሕጉ እየተመኩ በሕጉ ተከልለው ግብረ አሕዛብን ከመፈጸም ያልታቀቡትን አይሁድ ነቀፋቸው። የቃሉ ምሥጢር ሳይገባቸው አይሁድም ሆኑ አሕዛብ ሕጉን ወደ መሻር እንደማይጠቅምም አድርጎ ወደ መናገር እንዳያዘነብሉ ደግሞ ሕግን በእምነት እናጸናለን እንጂ አንሽርም አላቸው። ምክንያቱም «ሕጉ ቅዱስ ነው፥ ትእዛዙም ቅድስትና ጻድቅት በጎም ናትና።» ሮሜ.7፥12። ጌታም በወንጌል ወጣቱን ባለጸጋ፥ የዘላለምን ሕይወት እንድታገኝ ትእዛዛትን ጠብቅ ብሎ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ታልና። ማቴ.19፥17፤ ዘጸ. 20፥12።

ይህ እንዲህ ከሆነ «በሕግ ልትጸድቁ የምትፈልጉ ከክርስቶስ ተለይታችሁ ከጸጋው ወድቃችኋል።» ገላ.5፥4። የሚለው አነጋገር ምን ማለት ነው? ሕግ አያስፈልግም ማለት ይሆን? ካልሆነስ ለምን ተነገረ? የሚለውን እስቲ እንመልከት።

ከላይ እንደተመለከትነው ወንጌል በኦሪት በምሥጢር መሰበኳን፥ ኦሪት ለወንጌል አምሳልና መርገፍ መሆኗን ያልተረዱ አይሁድ ከአሕዛብ የምታስበልጠንን ኦሪት እንጂ የምታስተካክለንን ወንጌል አንፈልግም በማለታቸው የተነገረ ነው። እገሌ ከእገሌ እኩል ለምን ሆነ ማለት ደግሞ ምቀኝነት የእግዚአብሔርንም ቸርነት ማቃለል ነው። በጥቅሱ ጸጋ የተባለው በጥምቀት የምትገኘውን ልጅነት እና ለሁሉ ለአይሁድም ለአሕዛብም የተገለጠችውን ወንጌልን ነው። በመሆኑም አመፀኞቹን አይሁድ በጥምቀት ከምትገኘው ልጅነት በወንጌል ከምትወረሰው ርስት ወጥታችኋል ሲላቸው ከጸጋው ወድቃችኋል አላቸው። ስለዚህ «እነሆ ውኃ፤ እንዳልጠመቅ የሚከለክለኝ ማን ነው?» ብለን ለተጠመቅን፥ «ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ አምናለሁ።» የሐዋ.8፥36። ብለን ወንጌልን ለተቀበልን ለእኛ ለኢትዮጵያውያን ለኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ልጆች ይህ ጥቅስ የሚያስደነብረን አይደለም። ምክንያቱም ማንነታችንን እናውቃለንና። «እንግዲህ ምን እንላለን? ጸጋ እንዲበዛ (በጸጋ እንድናለን፥ እንጸድቃለን እያልን) በኃጢአት ጸንተን እንኑርን? አይደለም፥ ለኃጢአት የሞትን እኛ እንዴት አድርገን በእርሱ እንኖራለን?» ሮሜ.6፥1።

የተወደዳችሁ አንባብያን ከጽሑፉ እንደተረዳነው እውነትን በመያዝ ሳይሆን ለተቃውሞ እንዲረዳ በማለት ብቻ ጸጋ የሚለውን ቃል የበግ ለምድ አድርጐ ሥራ፥ ሕግ፥ ጥምቀት፥ ቁርባን (ሥጋውና ደሙ)፥ የቅዱሳን አማላጅነት አያድንም እያሉ ምዕመናንን ግራ ማጋባት አይገባም። ይህም ሁሉ የእግዚአብሔር ጸጋ ነውና።

ሀ. አምናችሁ ብትጠመቁ ትድናላችሁ፥ መንግሥተ ሰማያት ትገባላችሁ ብሎ ጥምቀትን የሰጠን፥ ለአብነት ተጠምቆ ያሳየንም እርሱ ነው። ማቴ.3፥13፤ ማር.16፥16፤ ዮሐ.3፥5።

ለ. የዘላለም ሕይወት ይሆናችኋል ብሎ ሥጋውን ደሙን የሰጠን እርሱ ነው። ዮሐ.6፥53-59።

ሐ. የድንግል ማርያም አማላጅነት እና እናትነት ጸጋ ነው። «ጸጋን የተመላሽ ሆይ...በእግዚአብሔር ፊት ባለሟልነትን አግኝተሻልና» ሉቃ. 1፥28፤30። «እናትህ እነኋት» ዮሐ.19፥27። የሚለው ይኸንኑ የሚያረጋግጥ ነው። ይህ ጸጋ ከእግዚአብሔር የተገኘ ነውና።

መ. የቅዱሳን መላእክት ተራዳኢነትና አማላጅነት የእግዚአብሔር ጸጋ ነው። ልመናቸውንና ምልጃቸውን ተቀብሎ እንዲረዱን የሚልካቸው እርሱ ነውና። መዝ.33፥7፤ ዘካ. 1፥12፤ የሐዋ.10፥3፤ 12፥6፤ ዕብ.1፥14።

ሠ. የቅዱሳን ሁሉ አማላጅነት፥ ቃል ኪዳናቸውን በማመን መታሰቢያቸውን በማድረግ የሚገኝ በረከት ጸጋ ነው። መዝ.111፥6፤ ምሳ. 10፥7፤ ኢሳ.56፥4-7፤ ማቴ. 10፥41፤ ያዕ.5፥16። በአጠቃላይ ኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክ እንደሆነ በማመን በመስቀል ላይ የተፈጸመውንም ቸርነት በማሰብ በቅዱሳን አማላጅነት የምናገኘው ምሕረት፥ በጾምና በጸሎት፥ በስግደትና በምጽዋት የጸጋው ሁሉ ተሳታፊዎች እንድንሆን የእግዚአብሔር ቸርነት የድንግል ማርያም አማላጅነት አይለየን አሜን። ❖

## ወንድሜ ሆይ

- ሰውን ሁሉ መውደድ፤ መልካም ነው፤ ቃል የምትገባውን ሁሉ ፈጽም። እገኛለሁ ባልክበት ሁሉ በተቻለህ መጠን በሰዓቱ ተገኝ። ንዝህላልና ዝንጉ አትሁን።
- ሰውን ልምሰል አትበል፤ ራስህን መስለህ ኑር። ሰዎችን እንደ ባሕርያቸው ያዝ። ስለምታደርገው ሁሉ ከሰው በጎ አትጠብቅ፤ ውለታ መላሽ– አምላክ ነውና።
- መጥፎ ነገሮችን ዝም ብለህ አትለፍ፤ ወንድምህንም በአግባቡ ገስፅ።
- ስሕተትህን እመን፤ ሰው ነህና እንደምትሳሳት አስብ። የግትርነት ጸባይ አይኑርህ። ይህ ያስታብያልና። ስሕተቱን የሚያምን ግን ዕውቀትን ይጨምራል። ከመሞገስ፤ ከመወደስ ይልቅ መታረምን፤ መገሰፅን ምረጥ።

ወለተ ሩፋኤል

❖ ❖ ❖

- «አንዳንድ ሰዎች ቤተ ክርስቲያን በትምህርቷና በሥርዓቷ ጉድለት ያለባት የሚመስላቸው ጉድለታቸውን ስለምታሳያቸው ነው።

ወ/ሮ ፀ. መ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ደካማ ጎንን እንዴት ማሸነፍ ይቻላል?

(ካለፈው የቀጠለ)

በሁለት ተከታታይ ክፍሎች ደካማ ጎንን ለማሸነፍ የሚረዱንን ሦስት ነጥቦች አንሥተን በዝርዝር ተመልክተናል። የተቀሩትን ሁለቱን ደግሞ በዚህ እትማችን እናጠናቅ ቃለን። ደካማ ጎንን ለማሸነፍ:-

4. ስማዕትነትን ለመቀበል ዝግጁ መሆን:-

አንድ ደካማ ጎኑ ምን እንደሆነ ያወቀና ለማሸነፍ የሚጥር ሰው በቀላሉ ማሸነፍ ሊክብደው ይች ላል?! ለምሳሌ በጫት ወይም በሲ ጋራ ሱሰኝነት የተጠመደ ሰው ሊያ ቆም ሲሞክር ምን አልባት ለጊዜው ሊታመም፣ አካባቢውን ሊቀይር ወይም ከቀድሞ ጓደኞቹ ጋር መለ ያየት ይኖርበት ይሆናል። በዚህ ጊዜ ‹እንዴት አድርጌ እችለዋለሁ?› እያለ ራሱን ማዳከም ሳይሆን በቆራጥነት የሚገጥመውን ችግር ለጊዜው ብቻ እንደሆነ ተረድቶ የሚበጀውን ሊመ ርጥ ይገባዋል። ያውም በክርስትና ሕይወት እስከ መጨረሻው ጸንቶ ለሰማያዊ ክብር የተሰጣቸው በመከራ ውስጥ ማለፍ ይጠበቅበታል። ጻድቁ አባታችን አቡነ ተክለሃይማኖት ክንፍ ያበቀሉት እግር አጥተው መሆኑን መዘንጋት የለብንም። ወደ እግዚአ ብሔር መንግሥት በብዙ መከራ እንገባ ዘንድ ያስፈልገናልና። የሐዋ.14፥22።

የብዙዎቻችን ችግር ግን አንድ በጣም የምንፈልገውን ያውም የሰማያ ዊውን ሀብት ለማግኘት በዚህች ምድር ላይ ትንሽ እንኳን መጎዳት ወይም መቸገር አንፈልግም። ከዚህም የተነሣ ወደፊት ምናልባት ሊገጥመን የሚችለውን ፈተና ለመቋቋም ድፍ ረቱ ጠፍቶን ደካማ ጎናችንን ተሸ ክመን መሰቃየትንና ከእግዚአብሔር ቤት ተለይቶ መኖርን እንመርጣለን።

ስለዚህ ደካማ ጎናችንን ለማሸነፍ ገና ለገና ብታመምስ? ችግር ቢገጥ መኝስ? ወዘተ. እያሉ በቅድሚያ ምክንያቶችን እየደረደሩ ተስፋ ከመቁ ረጥ በቆራጥነትና በእምነት መታገስ ያስፈልጋል። ይህ ነው ተፈላጊውም ሰማዕትነት። የሚደርስበትን መከራ በጸጋ ተቀብሎ ደካማ ጎንን አሸንፎ ለክብር መብቃት።

5. መጽናት

መጽናትን በሁለት መልኩ መመልከት ይቻላል።

ሀ. በጽናት መታገል

ደካማ ጎንን ለማሸነፍ እስከ መጨረሻው በጽናት መታገል ያስፈ ልጋል። የብዙ ሰዎች ችግር አለመጽ ናት ነው። አንድ ሁለት ጊዜ ይሞክሩና በቃኝ፣ አልቻልኩም፣ ተሸንፌአ ለሁ! ብለው እጃቸውን ይሰጣሉ። ለምሳሌ በምኞት ጾር የሚፈተን ወጣት ብዙ ጊዜ ሊሰቃይ ስለሚችል ቶሎ ተስፋ መቁረጥ የለበትም። በጽናት እስከ መጨረሻው መታገል እንጂ። ክርስቲያን በተጋድሎ እግዚአብሔር ለእርሱ የሚያደርግለትን ሲጠብቅ ትዕግስትን ይማራል። በትዕግስትም ለሰማያዊ ርስት ይበቃልና ሉቃ.21፥19።

እንዲሁም በጽናት እስከ መጨ ረሻው ከታገልን በኃይለ እግዚአብ ሔር የማናሸንፈው ደካማ ጎን አይኖርም። በእግዚአብሔር ቤት ጸንቶ ደካማ ጎንን ለማሸነፍ በመታገል ቅዱሳን ለታላቅ ክብር በቅተዋል። ደካማ የነበሩት ብርቱዎች፣ ፈሪ የነበሩት ደፋሮች፣ በእምነታቸው ተጠራጣሪዎች የነበሩት ጽኑዓንና ጠንካሮች ሆነዋልና። ለምሳሌ — ሐዋርያትን ጌታ ብዙ ጊዜ በእምነታ ቸው ደካማነት የተነሣ ይወቅሳቸው ነበር። ማር.16፥1—ፍ.ም። ነገር ግን ተስፋ ሳይቆርጡ እስከ መጨረሻው ከእርሱ ጋር በመሆናቸው ይወቀሱበት የነበረውን ደካማ ጎናቸውን ለማሸነፍ በቁ። ሉቃ.17፥3። የሐዋ.3፥1—10።

ለ. አንድ ጊዜ ካሸነፉ በዚያው መጽናት

በዘመናችን ብዙ ወጣቶች ደካማ ጎናቸውን ለማሸነፍ በሚያደርጉት ጥረት ኃይለ እግዚአብሔር ታክሎበት ያሸንፋሉ። አሸንፈው ያንን ሲጠቁ በት የነበረውን ነገር ለአንዴና ለመጨ ረሻ ጊዜ የሚያጠፉት ግን በጣም ጥቂቶች ናቸው። የተቀሩት ተመል ሰው ለዚያ በአንድ ወቅት ሲያወግዙት ለነበረው ደካማ ጎናቸው ተንበርክከው በእግዚአብሔር ቤት እንደፈቃዱ ለመኖዝ ይቸገራሉ።

ሁሉም ሰው ትንሽም ብትሆን ደካማ ጎን ሊኖረው ይችላል። በኃይለ እግዚአብሔርም ያሸንፋል። ለአሸናፊ ነቱ መጽናት ደግሞ የበለጠ ለታላቅ ክብር ይበቃል። ስለዚህ ደካማ ጎኑን ያሸነፈ ክርስቲያን ማሸነፉ ለጊዜው ሳይሆን እስከ መጨረሻው ሊሆን ይገባል። ❖

ወለእግዚአብሔር ስብሐት



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ክርስትና በማኅበራዊ ኑሮ

«አትስረቅ» የሚለው ትዕዛዝ በጽሑፍ ለሰው ልጆች ከመሰጠቱ ቀደም ብሎ በሕገ ልቡና ሳይቀር ታውቆ ይኖር የነበረ አምላካዊ ሕግ ነው። ሰው ሰውን መስረቁ የተለመደ ክስተት እየሆነ በመምጣቱ አድራጎቱ የሚያስደምም ላይሆን ይችላል።

ሰው እግዚአብሔርን ሰረቀ ሲባል ግን ያስገርማል፣ ያስደንቃል። ልዑለ ባሕርይ አምላክ በአገልጋዩ በሚልክያስ አድሮ የሰረቁትን ሰዎች እንዲህ ሲል ገስጿቸዋል። ሰው እግዚአብሔርን ይሰርቃልን? እናንተ ግን እኔን ሰርቃችኋል። እናንተም የሰረቅንህ በምንድር ነው? ብላችኋል። በአሥራትና በበኩራት ነው። እናንተ፣ ይህ ሕዝብ ሁሉ እኔን ሰርቃችኋልና በእርግማን ርጉሞች ናችሁ» ሚል.3፥7–9።

ሰዎች እግዚአብሔርን የሚሰርቁት «ከሰጠኸኝ ሁሉ ለአንተ ከአሥር እጅ አንዱን እሰጥሃለሁ» ዘፍ. 28፥22 በማለት ቅዱስ ያዕቆብ ከሚያገኙት ሁሉ ለእግዚአብሔር አሥራት በኩራት ማውጣት እንደሚገባቸው ያስተማረውን ትምህርት ዘንግተው የእግዚአብሔርን ፈንታ ለግል ጥቅማቸው ሲያውሉም ነው።

የአሥራት በኩራትን አስተዋጽኦ መከፈል በቅዱሳት መጻሕፍት ተደንግጎ የምናገኘው ሃይማኖታዊ ግዴታ ሲሆን ዳሩ ግን እንደ ምድራዊ መንግሥት ግብር አሰባሰብ በኃይል ሳይሆን በፍቅርና በውዴታ ግዴታ ላይ የተመሠረተ ነው።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በገላትያ ለሚኖሩ ምእመናን በላከው ክታቡ እንዲህ ብሏል «ቢቻልስ ዓይኖቻችሁን አውጥታችሁ በሰጣችሁኝ ብዩ እመሰክርላችኋለሁ» ገላ.4፥15። ይህ ጥቅስ የሚያስገነዝበን ክርስቲያኖች ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ሲባል እንኳን ገንዘባቸውን ሕይወታቸውን ሳይቀር ከመስጠት ወደ ኋላ እንደማይሉ ነው።

## ሰው እግዚአብሔርን ይሰርቃልን?

አሥራት በኩራት ማውጣት ከቀድሞ ጀምሮ የነበረ ሕግ ነው። የእምነት አባት እየተባለ የሚጠራው አብርሃም ለልዑል እግዚአብሔር አገልጋይ ለካህኑ መልከ ጼዴቅ ከሀብቱ ሁሉ አሥራትን እንደሰጠ በቅዱስ መጽሐፍ ተመዝግቦ ይገኛል። ዘፍ.14፥18–21።

አባታችን ያዕቆብ በፍኖተ ሎዛ ለአምላኩ ለእግዚአብሔር የገባው ቃል ኪዳን እኛንም የሚመለከተን መሆኑን መዘንጋት የለብንም። ከእንስሳት እንኳ ሳይቀር መጀመሪያ የሚወለደውን ለእግዚአብሔር መስጠት እንደሚገባ ታዟል። «የምድርም አሥራት ወይም የምድር ዘር ወይም የዛፍ ፍሬ ቢሆን የእግዚአብሔር ነው። ለእግዚአብሔር የተቀደሰ ነው። ከበሬም ሁሉ ከአሥር አንድ ከእረኛውም በትር በታች ከሚያልፍ በግና ፍየል ሁሉ ከአሥር አንድ ለእግዚአብሔር የተቀደሰ ይሆናል» ዘሌ.27፥26–32።

በሌላም ሥፍራ እንዲህ የሚል ተጽፏል። «ከእርሻህ በየዓመቱ ከምታገኘው ከዘርህ ፍሬ ሁሉ አሥራት ታወጣለህ። ሁል ጊዜ አምላክህን እግዚአብሔርን መፍራት ትማር ዘንድ ስሙ እንዲጠራበት በመረጠው ስፍራ በአምላክህ በእግዚአብሔር ፊት የእህልህን የወይን ጠጅህንም የዘይትህንም አሥራት የላምህንና የበግህንም በኩራት ብላ።› ዘዳ.14፥22–24።

ልዑለ ባሕርይ አምላክ አገልጋዮቹ እንዲሆኑ ከእስራኤል ነገድ ሁሉ ለይቶ ለመረጣቸው ሌዋውያን ደመወዛቸው የእሥራኤል ልጆች የሚያወጡት አሥራትና በኩራት እንደሆነ ካህኑ አሮንን እንዲህ ሲል አዞታል «ለሌዊም ልጆች እነሆ በመገናኛው ድንኳን አገልግሎት ስለሚያገለግሉ፣ የእሥራኤል ልጆች አሥራት ርስት አድርጌ ሰጥቼአለሁ» ዘኁ.18፥21–28።

በእግዚአብሔር መንፈስ የተጠራና የተመረጠ ቅዱስ ጳውሎስ ለምእመናን ቆሮንቶስ በላከው ቀዳማይ ክታቡ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ይውል ዘንድ አሥራት በኩራት ማውጣት እንደሚገባ እንዲህ ሲል



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ጽፏል። «ለቅዱሳንም ገንዘብን ስለማውጣት፣ ለገላትያ አብያተ ክርስቲያናት እንደ ደነገግሁት እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉ። እኔ ስመጣ ይህ የገንዘብ ማዋጣት ያን ጊዜ እንዳይሆን፣ ከእናንተ እያንዳንዱ በየሳምንቱ በፊተኛው ቀን እንደ ቀናው መጠን እያስቀረ በቤቱ ያስቀምጥ» 1ቆሮ.16፥1–3።

ዛሬም ቢሆን ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ያስተማራቸውን ትምህርት እኛም ልንጠቀምበት ያስፈልጋል። የተጻፈው ለሁላችንም ትምህርት ይሆነን ዘንድ ነውና። ይኸው የእግዚአብሔር ምርጥ ዕቃ ቅዱስ ጳውሎስ በሁለተኛ መልእክቱ እያንዳንዱ ምእመን የእግዚአብሔርን ገንዘብ ለእግዚአብሔር መልሶ ሲሰጥ በሙሉ ፈቃደኛነትና በደስታ መሆን እንዳለበት እንዲህ ሲል አስገንዝቧል «እግዚአብሔር በደስታ የሚሰጠውን ይወዳልና እያንዳንዱ በልቡ እንዳሰበ ይስጥ። በኀዘን ወይም በግድ አይደለም» 2ቆሮ.9፥6።

ሳይቆጭና ሳይሳሳ በደስታ ለሚሰጥ ሰው የእግዚአብሔር እጅ በምሕረት እንደሚዘረጋም ሲያስተምር «በተለይም ለምስኪኖች ለሰጠ ጽድቁ ለዘላለም ይኖራል ተብሎ እንደ ተጻፈ እግዚአብሔር ሁል ጊዜ በነገር ሁሉ አግኝታችሁ ለበጎ ሥራ ሁሉ ትበዙ ዘንድ ጸጋን ሁሉ ሊያበዛላችሁ ይችላል። ለዘሪ ዘርን፣ ለመብላትም እንጀራን በብዙ የሚሰጥ እርሱም የምትዘሩትን ዘር ይሰጣችኋል ያበረክትላችሁማል። የጽድቃችሁንም ፍሬ ያሳድጋል። በእኛ በኩል ለእግዚአብሔር የምስጋና ምክንያት የሚሆነውን ልግስና ሁሉ እንድታሳዩ በሁሉ ነገር ባለጠጎች ትሆናላችሁ» 2ቆሮ.9፥8–12።

በመጽሐፈ ሲራክም እንዲህ ተብሎ ተጽፏል «ፊትህን ደስ እያለህ እግዚአብሔርን አመስግነው። ከመጀመሪያ አዝመራህም አሥራት ማግባትን አትተው። የሰጠህን ገንዘብ ሁሉ ፊትህን ደስ እያለህ ስጠው። ደስ እያለህም ያዝመራህን አሥራት አግባ። እንደ ክብሩ ብዛት መጠን ለእግዚአብሔር መባህን አግባ። በእጅህ ካገኘኸው ገንዘብም ፊትህን ደስ እያለው አግባለት። እግዚአብሔር ዋጋህን ይመልስልሃልና። ሰባት እጥፍ አድርጎ ይሰጥሃልና። ፊትህን ደስ እያለህ አግባለት» መጽ.ሲራክ. 32፥10–13።

ፈጣሪያችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ትምህርቱ «የቄሣርን ለቄሣር የእግዚአብሔርንም ለእግዚአብሔር ብሏል።» ማቴ.22፥21።

እንግዲህ ምን እንላለን «የሰረቅነውን የእግዚአብሔርን ገንዘብ ልንመልስ አይገባንምን? ለእግዚአብሔር የሰጠንን መልሰን ካልሰጠን የተሰጠን ይወሰድብናል» ስለሆነም ከአሥር አንድ የእግዚአብሔር ድርሻ ነውና አሥራት በኩራትን ማውጣትን እንልመድ፣ የእግዚአብሔርንም በረከት እንቀበል። ለዚህም እግዚአብሔር ይርዳን። ✣

መስብሐት ለእግዚአብሔር

> **የአሥራት በኩራትን አስተዋጽኦ መክፈል በቅዱሳት መጻሕፍት ተደንግጐ የምናገኘው ሃይማኖታዊ ግዴታ ሲሆን ዳሩ ግን እንደ ምድራዊ መንግሥት ግብር አሰባሰብ በኃይል ሳይሆን በፍቅርና በውዴታ ግዴታ ላይ የተመሠረተ ነው።**

# አዲስ ኪዳን በብሉይ ኪዳን

(ከዲ/ደጀኔ ሺፈራው)

መፍቀሬ ሰብእ እግዚአብሔር በአርአያውና በአምሳሉ የፈጠረውን የሰው ልጅ ሁል ጊዜ ይጐበኘዋል፣ ለድኅነትም ይጠራዋል። ለዚሁም ነው በነቢያት ሲያረጋጋው የነበረ እርሱን በአንድ ልጁ መገለጥ ያዳነው። ሰውም ይህንን የድኅነት መንገድ እንዲረዳ ብሉይን ከአዲስ አስተባብሮ ሰጥቶታል። አንዳንድ መጻሕፍትን ያልጠነቀቁ ሰዎች ግን አንዱን ተቀብለው ሌላውን ሲያጣጥሉ ይገኛሉ። ይህም ቅዱሳት መጻሕፍትንና የክርስትናን ምሥጢር ካለመረዳት የመጣ ስህተት ስለሆነ የብሉይንና የአዲስ ኪዳንን ግንኙነት እንደሚከተለው ለማቅረብ እንሞክራለን።

መጽሐፍ ቅዱስ በሁለት ታላላቅ ክፍሎች ይከፈላል። ይኸውም ብሉይ ኪዳን እና አዲስ ኪዳን በመባል ይታወቃል። መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል በመሆኑ ለዘላለም ይኖራል። ምክንያቱም ሰማይና ምድር ያልፋሉ እንጂ ቃሉ አያልፍምና። ማቴ.5፥17 በተጨማሪም መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር እስትንፋስ ነው። 2ጴጥ.1፥21፣ 2ጢሞ.3፥17። እስትንፋስ እግዚአብሔር መባሉም ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተቀኝተው በመናገራቸው ነው።

የመጽሐፍ ቅዱስ የመጀመሪያው ክፍል የሆነው ብሉይ ኪዳን የቃሉ ትርጉም የቆየ የጥንት፣ በሰውና በእግዚአብሔርብ መካከል ያለውን የማይለወጥ ጽኑ መሐላ ቃልኪዳን የሚናገር ውል ወይም ስምምነት ማለት ነው። በአጠቃላይ ከክርስቶስ በፊት የነበሩት ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ይባላሉ።

የመጽሐፍ ቅዱስ ሁለተኛው ክፍል የሆነው አዲስ ኪዳን የቃሉ ትርጉም አዲስ ውል አዲስ ስምምነት

ወደ ገጽ 32 ዞሯል



©ማኅበረ ቅዱሳን                www.eotcmk.org

# ጥያቄዎቻችሁ

ለክርስትና በማኅበራዊ ኑሮ አዘጋጆች

ጥያቄ 1. ተባዕትና አንስት ጾታ ያላቸው ወጣቶች ማኅበርተኛ (የእርዳታ ወይም የመንፈሳዊ ጉዞ) መሆን ይችላሉ? ከሆኑስ ጋብቻ ሊፈጽሙ ይችላሉ ወይ?

(ዘውዱ አስፋው– ከድሬዳዋ)

መልስ – ሌሎች አራት የመጽሔታችን አንባቢዎችም ተመሳሳይ ጥያቄ ጠይቀውናል። መልሱንም አጠቃልለን ለማቅረብ እንሞክራለን።

በቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓት መሠረት ከሥጋና የጋብቻ ዝምድና ሌላ በሁለት ሰዎች መካከል ጋብቻ እንዳይፈጸም የሚከለክል መንፈሳዊ ዝምድና አለ። ይኸውም በጥምቀቱ ክርስትና ያለው ዝምድና (አበልጅ የሚባለው) ነው። (ፍ.ነገሥ.24 ቁ.847)። በዚህም መሠረት ወደ ላይ የክርስትና ልጅ፣ የክርስትና አባቱን ሚስት፣ ልጁን፣ የልጅ ልጁን፣ አጎቱን አያገባም። ወደ ታች ደግሞ የክርስትና አባት የክርስትና ልጁን እናት፣ አኅት፣ የእኅቱንና የወንድሙን ልጅ አያገባም። ከዚህም ሌላ በሃይማኖት የማይመሳሰሉ ሰዎች ልዩነቶቻቸውን እንደያዙ መጋባት አይችሉም። አንደኛው የተቀረውን ወደ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት መልሶ ማግባት ግን ይችላል።

በተረፈ የአንድ ሰንበት ት/ቤት ተማሪዎች ወይም የአንድ የእርዳታ ወይም የመንፈሳዊ ጉዞ ማኅበር ወዘተ አባላትን ከመጋባት የሚከለክላቸው ሕግ የለም።

አንዳንድ ሰዎች የአንድ ማኅበር አባላት የሆኑ ወጣቶች ሲጋቡ ተመልክተው እንደኃጢአት ቆጥረውት ሲናገሩ ይሰማሉ። በዚህም ብዙ ወጣቶችን አስደንግጠው ከቤተ ክርስቲያን እንዲርቁ አድርገዋል። ይህ ግን ትክክል አይደለም። እግዚአብሔር ከፈቀደና ከተስማሙ ራሳቸውን በንጽሕና በቅድስና ጠብቀው ለቅዱስ ጋብቻ መብቃት ይችላሉ። ይህ ሲባል ደግሞ መንፈሳውያን ማኅበራት የተሰበሰቡበትን መሠረታዊ ዓላማ እንዳይስቱ ሊጠነቀቁ ያስፈልጋል።

ጥያቄ 2. በአዲስ አበባ የአንድ ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ትምህርት ቤት ተማሪና አገልጋይም ነበርኩ። በዚህ ዓመት ግን 12ኛ ክፍል ስለሆንኩ ቤተሰቦቼ የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ተፈታኝ ነሽ ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን መሄድ የለብሽም ብለው በአጠቃላይ ከቤተ ክርስቲያን እንድርቅ አደረጉኝ። በሳምንት አንድ ቀን እሑድ እንኳን ቅዳሴ ማስቀደስ አልቻልኩም። ከዚህ የተነሣ መንፈሳዊ ሕይወቴ እየደከመ ሄደ። መዝሙር መስማትም ስለተከለከልኩና እቤት ውስጥም ዘወትር ዘፈን ብቻ ስለማደ ምጥ እኔም መዘመሬን አቆምኩ፣ መጸለይም ተውኩ። እንዲያውም ከቤት እንዳልወጣ በተከለከልኩ መጠን ከዚህ በፊት አስቤ የማላውቃቸውን መጥፎ ነገሮች እመኝ ጀመር። ሁል ጊዜ ስለምጨነቅ እንደታሰበው ማጥናት አልቻልኩም። ምን እንደማደርግ ግራ ገብቶኛልና እባካችሁ ምክራችሁን ለግሱኝ።

(ሶስና– ከአዲስ አበባ)

ወለተ መድኅን (ከጅማ) እና ሐና (ከአዲስ አበባ) በወላጆች ተጽዕኖ ቤተ ክርስቲያን መሄድ መከልከላችሁንና በዚህም ምክንያት በክርስቲያናዊው ሕይወታችሁ ላይ የደረሰባችሁን ፈተና በመግለጽ ጠይቃችሁናል። አስፈላጊውን መልስ በግል አድራሻችሁ መመለሳችንን እያስታወስን ከሦስታችሁ ጥያቄ በመነሣት ጠቅለል አድርገን ወላጆችና ልጆች እንዴት መኖር እንደሚገባቸው ለመመልከት እንሞክራለን።

ወላጆች ልጆቻቸውን የሚቆጣጠሩት ከፍም ሲል የሚጫኗቸውና የሚጨቁኗቸው ልጆቻቸውን ለመጉዳት በማሰብ ሳይሆን ለእነርሱ ይጠቅማል፣ ተጠብቀው ቢያድጉ ትልቅ ደረጃ ይደርሳሉ በማለት የወደፊቱን እያሰቡ ነው። የሰንበት ትምህርት ቤት ወጣቶችንም (በእኅቶቻችን እንደደረሰው ዓይነት) ከቤተ ክርስቲያን እስከ ማስቀረት ሊደርሱ ይችላሉ። ይህ የሚሆነው አንድም ልጆች ቤተ ክርስቲያን እየሄዱም ሕይወታቸው ሳይለወጥ ሥርዓት አልባ፣ ለትምህርታቸውና ለኑሮአቸው ሁሉ ደንታ ቢሶች ሲሆኑባቸው ተስፋ በመቁረጥ ሲሆን፤ በሌላ በኩል ደግሞ ወላጆች የሰንበት ትምህርት ቤት ጥቅም ሳይገባቸው ቀርቶ ልጆቻቸው ወደ ሌላ ተግባር እንጂ ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲሄዱ አለመፈለጋቸው ነው። አንዳንዶቹ ደግሞ የልጆቻቸው ቤተ ክርስቲያን ሄደው መንፈሳዊ ሕይወት ይዘው መገኘትና ታዛዥ ወይም ትሁት መሆን፣ ሥርዓትን የጠበቀ አለባበስ መከተል፣ ከመጠን በላይ አለመኳኳል (አለመሽቀርቀር) ወዘተ...በወጣትነት ጊዜ መሆን የሌለበትና ወጣት ቢያደርገው እንኳን በሽተኛ የሆነ ስለሚመስላቸው ቤተ ክርስቲያን መሄድን እንደመጎዳት ይቆጥሩታል። ወላጆች ልጆቻቸውን የመቆጣጠር ኃላፊነት ያለባቸው መሆኑ ባያጠያይቅም ግን ለልጆቻቸው የሚበጀው ምን እንደሆነ ማጤን ይኖርባቸዋል። በጣም የሚገርመው ለአቅመ ሔዋን የደረሰች ልጁን ሰውነት የሚያጋልጥ ልብስ ካልለበስሽ፣ ፊትሽ በመኳኳያ (በቀለማት) ብዛት ካልተኾ‍ጉረጎረ እያለ የሚያስቸግር ወላጅ እንዳለ ተመልክተናል። በፋንታው ነጠላ በላይዋ ላይ ጣል አድርጋ መውጣትን ከመረጠች እሟት ይሆናል በማለት ወደ ሥነ አእምሮ ሐኪም (psychiatrist) እስከ መውሰድ የደረሱም አጋጥመውናል። እንዲህ ዓይነት ብዙ ወላጆችን መጥቀስ ይቻላል። በዚያም ሆነ በዚህ አንድ ወላጅ በዕውቀት ደረጃው ለልጁ የሚያደርገው ሁሉ ይጠቅመዋል ብሎ በማሰብ እንጂ ልጁ እንዲጠፋበት ወይም ባለጌ እንዲሆንበት አይደለም። እያንዳንዱ ወላጅ ልጁ ከትልቅ ማዕረግ ደርሶ ስሙን እንዲያስጠራለት ይመኛል። ነገር ግን ካለማወቅ ወይም ከፍቅሩ ጽናት የተነሣ ለልጁ የሚበጀውን አደርጋለሁ ብሎ እያሰበ ሊጎዳው ይችላል። በእኅታችንና በተቀሩት ላይ የደረሰውም ይኸው ይመስለናል።



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

በአንጻሩም አንዳንድ ወጣቶች ቤተ ክርስቲያን መሄድ በጀመሩ ማግስት ለሥጋቸው የሚጠቅመውን ሥራ ሁሉ (ትምህርቱን፣ ንግዱን፣ ወዘተ) ኃጢአት አድርገው በማሰብ እርግፍ አድርገው ይተውታል። ይህ ሁኔታ ገና በወላጆቻቸው አስተዳደር ሥር ባሉ ወጣቶች ብቻ ሳይሆን በዕድሜ ከፍ ባሉትና ትዳር በመሠረቱት ላይም ይስተዋላል። ታዲያ በዚህ ሁኔታ ከወላጆች ወይም ከትዳር ጓደኛ ጋር መስማማት ይጠፋል። በፈንታው ጥላቻና መናናቅ ይተካል። ስለዚህ ወጣቶች በስሜት ብቻ ከመመራት በክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር ታንጸው ያለነቀፉ መኳዝ ይጠበቅባቸዋል።

ሌላው ደግሞ ወላጆች በሚገባ ማወቅ ያለባቸው ልጆቻቸው በትክክል ቤተ ክርስቲያን ቢሄዱ በሚሠሩት ሥራ የበለጠ ታታሪ ዎች፣ ለወላጆቻቸው ታዛዦችና ትሑቶች መሆን እንደሚችሉ ነው። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን እንዳይሄዱ ከመከልከል ይልቅ የሚሄዱበት ቦታ በርግጥም ቤተ ክርስቲያን መሆኑን መከታተል እንዲሁም በትምህር ታቸውም ማበረታታት ይኖርባቸዋል።

ወላጆች ለልጆች አርአያ በመሆን እየመ ከሩና እየገሰጹ እንጂ በግድ እየቀጠቀጡ ወይም በተቃራኒው እንደፈለጉ ይሁኑ በማለት መረን ለቅቆ ማሳደግ አያስፈልግም። በሁለቱም መንገድ ልጅን ለማሳደግ መሞከር ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናልና። ከእህታችን ደብዳቤ እንኳን መረዳት እንደሚቻለው በግድ አጥኚ ተባለች፣ ማጥናትን ጠላች፣ እንዲያውም ጭንቀትና መጥፎ ሃሳብ በኅሊናዋ አሳደረባት። ለዚህ ነው በአንድ ወቅት ከግቢ መውጣት ሲከለከሉ የምናያቸው ወጣቶች ሲለቀቁ በአጉል ሱሰኝነት ተጠምደው፣ በአመንዝራነትና ከሕብረተሰብም ሆነ ከእግዚአብሔር በሚለይ ልቅ ሕይወት ተበክለው የምንመለከተው።

## ማሳሰቢያ

«ተማሪ እገሌ» እያልክ ሁለት ደብዳቤዎችን የጻፍከው ወንድማችን ጥያቄህ በግል የሚመለስ ሆኖ አንተ ግን ስምህን በመደበቅህ ልንረዳህ አልቻልንም። ሌሎቻችሁም ትክክለኛ አድራሻችሁንና ስማችሁን ባትደብቁ ቶሎ ይመለስላችኋል። ✣

# ቤተ ክርስቲያንህን ለወቅ

## የንዋየ ቅድሳት ዝርፊያ ከትናንት እስከ ዛሬ

(ክፍል አንድ)

በዓለም የድንቅ ታሪኮች መዝገብ ከሰፈሩት የኢትዮጵያ ታሪካዊ ቅርሦች አብዛኛዎቹ የቤተ ክርስቲያን ሀብት ናቸው። የላሊበላ፣ የጎንደርንና የትግራይ አብያተ ክርስቲያናትን፣ እንዲሁም የሸዋውን አዳዲ ማርያም ለምሳሌ ያህል መጥቀስ ይቻላል። ከዚህ በተጨማሪ የእንግሊዝን፣ የፈረንሣይንና የኢጣሊያንንና የሌሎችንም የአውሮፓ አብያተ መጻሕፍት (Libraries) እንዲሁም ቤተ መዘክሮች (Museams) ያጣበቡት በሺዎች የሚቆጠሩ መጻሕፍት፣ ሥዕሎች ንዋየ ቅዱሳት ከኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የተዘረፉ የቀደምት አበው የመንፈሳዊነት ውጤቶች ናቸው። ይህ ሁሉ መቼ እንዴትና ለምን ሆነ? ዛሬስ ያለው ሁኔታ ምን ይመስላል? ለነገስ ምን መደረግ አለበት? የሚሉት ጥያቄዎች በብዙ የሚያነጋግሩና ውሳኔም የሚያስፈልጋቸው ናቸው።

ኢትዮጵያ ሀገራችን የክርስትናን እምነት በቀዳሚነት የተቀበለች፣ በራሷ ትምህርትና መንበረ ጵጵስና ለመተደደር ከእስክንድርያ ቤተክርስቲያን ጋር፣ በብዙ ተጋድሎና መከራ የጸናች፣ በፃድቃ ቅዱሳን፣ ኋላም በተነሱ አበው ብርሃንነት የወንጌልን ትምህርት ከዳር ዳር ያስፋፋች፣ ለሕዝቧም ባሕልንና ቅርስን ያወረሰች ዛሬም በሐዋርያት ትምህርት የጸናች ናት። የታሪክ ባለቤት፣ በኢ–አማንያን የተከበበች የክርስትና ደሴት መሆኗ ያላስደሰታቸው ሰዎች ለዘመናት ሊያጠፏት ብዙ ሙከራ አድርገዋል። በእነዚህ ጠላቶቿ በቀጥታና በተዘዋዋሪ መንገድ የተፈጸሙት ብዙበደሎች መልካቸውን ቢቀያይሩም እስከ ዛሬም ድረስ አልጠፉም። ይህንንም ለመረዳት ትናንት ምን ነበረ? ዛሬስ ምን አለ? የሚለውን ለመመልከት እንሞክራለን።

### 1. ከ642 ዓ.ም እስከ 682 ዓ.ም

በአቡነ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን ስብከት፣ በፃድቃ ቅዱሳን ተጋድሎ የጸናው የክርስትና ትምህርት በመላው ሀገሪቱ ተዳርሶ የምንኩስና ሕይወትና ገዳማዊ ሥርዓት ተመሥርቶ፣ አብያተ ክርስቲያናትም ታንፀው ስለነበረ ይህ ጊዜ ክርስትና ያበበበት ጊዜ ነበረ።

በ642 ዓ.ም በአክሱም የንጉሡ የድግ ናዡን ልጅ ሕፃኑ አንበሳ ውድም በነገሠበት ዘመን አይሁዳዊቷ ዮዲት (ጉዲት) ጦሯን አስከትታ ለጦርነት ተነሣች። ከላስታ፣ ሰሜንና ወልቃይት የተሰበሰቡትን ፈላሾች፣ ሌሎችንም ቀስቅሳና አስፈራርታ በማስነሣት ወደ አክሱም ዘመተች። እግረ መንገዷንም ያገኘቻቸውን አብያተ ክርስቲያናት አፈራረሰች። የታሪክ ቅርሶችንም በእሳት አቃጠለች። በዚህ ወቅት ነበረ በአብርሃና በአጽብሃ የተሠራችው የመጀመሪያይቱ የድንግል ማርያም ቤተ ክርስቲያን የተቃጠለችው። ከዚህም በተጨማሪ ከክርስትና በፊትም ሆነ በዘመነ ክርስትና የተሠሩ ሀውልቶችን አፈራረሰች። መጻሕፍትና አያሌ የቤተ ክርስቲያን ንዋያተ ቅድሳትን ደመሰሰች፣ ምእመናንና ካህናትም ከድንግል ማርያም ቤተ ክርስቲያን ጋር አብረው ተቃጠሉ። ምድራዊ ሀብት የማይገዛቸው፣ የዘመን ብዛትም የማይመልሳቸው ቅርሶች ዐመድ ትቢያ ሆኑ።

በአክሱም የሚገኙ ካህናትም ታቦተ ጽዮንንና ቅዱሳት መጻሕፍትን ለማትረፍ ብዙ መቶ ኪሎ ሜትሮች አቋርጠው ወደ ዝዋይ ሐይቅ ደሴቶች ተሰድደዋል። ይህም 40 የመከራ ዘመን ታሪካዊ ቅርሦች የጠፉበት፣ ክርስቲያኖች የተጨፈጨፉበት በመሆኑ የሚዘነጋ አይደለም።



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

## 2. ከ912 ዓ.ም እስከ 1542 ዓ.ም

መንበረ መንግሥታቸውን በላስታ ያደረጉት የላስታ ነገሥታት በዘመናቸው ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን ሲያሳንፁ፣ መንፈሳዊ ተጋድሎም ሲጋደሉ ኖረዋል። ለምሳሌ ንጉሥ ላሊበላ ከእግዚአብሔር በተሰጠው ጥበብ ከውቅር ዐለት የተሠሩ አብያተ ክርስቲያናትን ያነፀው በዚሁ ዘመን ነበር። እነዚህን የማይጠፉ ማኅተሞች በተመለከትን ጊዜ ያለፈ ታሪካችንን፣ የአባቶቻችን ተጋድሎ፣ መንፈሳዊነታቸውን በመገንዘብም ራሳችንን እንመር ምርበታለን። ነገር ግን ቤተ ክርስቲያን ያላትን እንድታጣ፣ ልጆችዋም ከብርሃን ጨለማን እንዲመርጡ ከማድረግ የማይቦዝን ጠላት ግራኝን አስነሥቶ ከሰሜን እስከ ደቡብ፣ ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ የታነፁ አብያተ ክርስቲያናት ፈረሱ፣ የቀሩትም በእሳት ተቃጠሉ። መጻሕፍትና ንዋያተ ቅዱሳት ተሰብስበው ወደ እቶኑ ተጣሉ። ካህናትና መነኮሳት በእምነታቸውም የጸኑ ምእመናን ተሠዉ። ገሚሱም ቤተ ክርስቲያናቸው ሲቃጠል መታገስ እያቃታቸው ወደ እሳት እየገቡ፣ የእሳት እራት ሆኑ። የተቀሩት ምእመናንም በኃይል ክራቸውን በጠሱ። ይህ ክፉ ዘመን እስኪያልፍም አበው የተረፉትን መጻሕፍትና ንዋያተ ቅዱሳት በመያዝ በየዋሻውና በየገደሉ ተንከራተቱ። በዚህም ታሪክን ለትውልድ አተረፉ፤ እነርሱ ሞተው ታሪክን ሕያው አደረጉ። «ጉንጬ ይሙላ ደረቴ ይቅላ» ሳይሉ የቤተ ክርስቲያን ነገር እያንገበገባቸው ሕይወታቸውን አሳለፉ።

## 3. ከ1607 ዓ.ም እስከ 1632 ዓ.ም

በግራኝ የጭካኔ ጭፍጨፋ የተጐዳችው ቤተ ክርስቲያን ከጉዳቷ አገግማ ምእመናንን ከማበርታቷ የተበተኑትንም በወጉ አሰባስባ ሳታበቃ የሮማ ካቶሊካውያን የተንኮል ድራቸውን ማድራታቸው በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ ሆነባት። አፄ ሱስንዮስን በእርዳታ ሰበብ እምነታቸውን በማስቀየር የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ታሪክና ቅርስ ለማጥፋት ቆርጠው በመነሣታቸው ይህንን ሐሳብ አልቀበል ያሉ ምእመናን በሰይፍ ተቀሉ። ከእናት ቤተ ክርስቲያናቸውም እንዲለዩና የሮማን እምነት እንዲቀበሉ ብዙ ተንኮል ተፈጸመ። አብያተ ክርስቲያናት እንደገና በሮማውያን እንዲባረኩ፣ ምእመናንም እንደገና እንዲጠመቁ፣ ካህናትም ሁለተኛ እንዲካኑ፣ በምሥራቃውያን ሥርዓት የተሣለው የቀለም ሥዕል ቀርቶ በሮማውያን ሥርዓት ከደንጊያ የተጠረበ (የተቀረጸ ምሥል) እንዲቆም ተወሰነ። በዚህም ምክንያት በተነሣው ጦርነት ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ፈረሱ፣ ሥዕሎችም ከየግድግዳው እየተገነጠሉና እየተላጡ ተቃጠሉ።

በዘመናትም ብዛት ምእመኑ የራሱ የሆነውን ታሪኩን ባሕሉንና ሥርዓቱን እንዲረሳ ለማድረግ ሚሲዮናውያኑ ኢየሱሳውያን (Jesuits) ብዙ ሞከሩ። ይሁን እንጂ ቸር ጠባቂዋ ኢየሱስ ክርስቶስ ነውና ቤተ ክርስቲያኒቱ አልጠፋችም። ዛሬም ይህ የሚሲዮናውያን ቅሰጣ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍል ሲፈጸም እንመለከታለን። «አንድ ነን» በሚል የሽንገላ ንግግር በተለያዩ የኢኮኖሚ እርዳታዎች ሰበብ ኦርቶዶክሳውያንን ለማሳሳት በጦርነት ጭምር አልሳካ ያላቸውን ዓላማቸውን ግብ ለመምታት ላይ ታች ሲሉም ይታያሉ። ከዚህ በተጨማሪም ቤተ ክርስቲያኒቱ ሰላም እንዳታገኝ፣ ምእመናን በፍቅርና በአንድነት እንዳይኖሩ የተከሉት እሾህ ለብዙ ዘመናት በምእመናን መካከል ልዩነት እየፈጠረ ሲያወዛግባቸው፣ እስከደም መፋሰስም ሲያደርስ ቆይቷል።

ስለዚህ ታሪካችንንና ቅርሳችንን ለመጠበቅ ዛሬም የተንኮል ጥበባቸውን መረዳትና መገንዘብ ያስፈልጋል።

## 4. 1769 ዓ.ም እስከ 1855 (ዘመነ መሳፍንት)

ይህ ዘመን ኢትዮጵያ በመሳፍንት አገዛዝ እንደ ቅርጫ ሥጋ የተከፋፈለችበት፣ መሳፍንት–ነገሥታቱን ለይምሰል ብቻ አንግሠው እያስቀመጡ አገሪቱን ግን የሚመሩት ራሳቸው መሳፍንቱና መኳንንቱ ስለነበሩ ዘመነ መሳፍንት ተብሏል። እርስ በርሳቸውም ስለማይስማሙም ከውጭ ሀገር መሣሪያ ለማስገባትና ሌላውን ለመጣል በሚሲዮኖች አማካኝነት ወደየመንግሥታቱ ይላላኩ ነበረ። ይህም ትርምስ ለሚሲዮኖቹ ሃይማኖታቸውን ለማስፋፋት ጥሩ አጋጣሚ ሆነላቸው። በየመኳንንቱ ቤትም እየተቀመጡ አማካሪዎች ሆኑ። ለምሳሌ በኤርትራ ቆላማ ክፍል የሚገኙ ክርስቲያኖች ወደ እስልምና የሄዱት በዚሁ ዘመን ነው። ቆለኞቹ ክርስቲያኖች ለብዙ ዓመታት ካህናትና የሃይማኖት መምህራን አይተው ስለማያውቁ የእስላም ወራሪ በመጣባቸው ጊዜ የቤተ ክርስቲያናቸውን ንዋያተ ቅድሳት በመያዝ በረሃ ለበረሃ በመንከራተት ሃይማኖታቸውን ጠብቀው ነበረ። ነገር ግን ትውልድ አልፎ ትውልድ ሲተካ የሃይማኖታቸው ምልክቶች የሆኑት ንዋያተ ቅድሳትም በየዋሻው በምስጥ እየተበሉ ተበጣጥሰው በማለቃቸው ምእመኑ ሳይወድ በግድ ወደ እስልምና ሃይማኖት ተሳበ።

በደቡብና በምዕራብ ኢትዮጵያም የነበረው ታሪክ ከዚህ የሚለይ አይደለም። ጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት በ13ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ሐዋርያዊ ጉዞ አድርገው የሠሯቸው አብያተ ክርስቲያናትና የገደሟቸው ገዳማት የጠፉት በዚህ ዘመን ነው። ምእመኑም እስከ አራት ትውልድ ድረስ ካህን ባለማግኘቱ ወደ እስልምናና አረማዊነት ተቀየረ፣ የጸናውም እምነት እንጂ ጥምቀት አልነበረውም። በዚህም ምክንያት በሱዳን በኩል የገቡ እስላሞች ወደ እምነታቸው አስገቡት።

ቤተ ክርስቲያን በሀገር ውስጥ ብቻ ሳይሆን በኢየሩሳሌም ከነበሩት አያሌ ቦታዎች ብዙዎቹን የተነጠቀችው በዚሁ ዘመን ነው። በየዓመቱ ይደረግ የነበረው ጉዞ በመቋረጡና በዚያ የነበሩት መነኮሳትም በበሽታና በችግር በማለቃቸው ገዳማቱ ባለቤት የሌላቸው ሆኑ። ጠባቂ ያልነበራቸውን ቅርሶችና ቦታዎች አርመኖችና ግሪኮች ወሰዱአቸው።

በዚህም ሳያበቃ መሣፍንቱ እርስ በርስ በሚያደርጓቸው ጦርነቶች አያሌ አብያተ ክርስቲያናት ተደምስሰዋል። ሚስዮናውያኑም ይህንን አጋጣሚ በመጠቀም ሀብታችንን እየዘረፉ ወደ ባሕር ማዶ አሻግረውታል።❖

ይቀጥላል



©ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

# የቤተ ክርስቲያን ታሪክ

ከብርሃኑ ጐበና

‹ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬ
እስከ ዘላለምም ያው ነው›
ዕብ.13፥7

ቅዱስ መጽሐፍ እንዲህ ቢልም በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እናምናለን የሚሉ፣ ያንኑ አንዱን ወንጌል የሚይዙ፣ በክርስትና ስም የሚጠሩ ድርጅቶች እየበረከቱ መጥተዋል። የእኔ ይበልጥ፥ የእኔ ይበልጥ ምእመናንን ግራ ሲያጋቡ፣ ገሚሱንም በተንኮል ወጥመዳቸው ሲይዙ ይስተዋላል። ለመሆኑ ቤተ ክርስቲያንና ክርስትና ከትናንት እስከ ዛሬ ታሪካቸው ምን ይመስላል። በዚህ ጽሑፍ የዚህን መልስ በተከታታይ ያገኛሉ።

ሃይማኖት እንደ እንግዳ ደራሽ እንደ ውኃ ፈሳሽ በሰው ልጅ ታሪክ ድንገት የተከሰተ የሰው አእምሮ ውጤት ሳይሆን ከጥንት ጀምሮ ያለና የነበረ ነው። ሃይማኖት ሥርወ ቃሉ ግዕዝ ሲሆን የሱርስትም ፍቺው በተመሳሳይ ሁኔታ ማመን መታመን ማለት ነው።[1] ሃይማኖት ወደ እግዚአብሔር የሚያደርስ መንገድና የሰውና የእግዚአብሔር ግንኙነት ነው። ይህም ግንኙነት በእግዚአብሔር የተጀመረው አስቀድሞ በመፍጠር፣ እንደዚሁም የሰው ልጅ አጥፍቶ በተደበቀ ጊዜ የጥሪ ድምፅ በማሰማት ነው። በመሆኑም ሃይማኖት ፍኖተ እግዚአብሔር (ዴሬክ ያህዌ) ይኸውም የእግዚአብሔር መንገድ ይባላል። በተለይም የክርስትና ሃይማኖት የአምላክ በሰው ሥጋ መገለጥ፣ የአምላክ ወደ ሰው መምጣት፣ የጠፋውን መፈለግ ነውና የመጀመሪያውን ሰው ለመፈለግ የተደረገው አምላካዊ ጉዞ የተፈጸመበት የታተመበት ስለሆነ ሃይማኖት ፍኖተ እግዚአብሔር መባሉ ትክክለኛ ነው።[2]

ሃይማኖት አቻና አኳያ የሌላት አንዲት ናት። ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ፈጽሞ የተሰጠች ናት እንጂ በየጊዜው የምትሻሻልና የምትለወጥ አይደለችም።[3]

ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ እንደሰበከው የሃይማኖታችን ምሥጢር ያለምንም ጥርጥር ታላቅ ነው። 1ጢሞ.3፥17። ከላይ እንደተገለጸው ሃይማኖት ፍኖተ እግዚአብሔር ነው። በመሆኑም እግዚአብሔር የሰው ልጅን ከወደቀበት የኃጢአት አዘቅት ለማውጣት ያደረገው አምላካዊ ጉዞ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ነው። የቤተ ክርስቲያን መሠረቷና ጉልላቷ ክርስቶስ ነውና የሃይማኖታችንም ጀማሪና ፈጻሚውም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ቤተ ክርስቲያንን በደሙ መሥርቷታልና። እንደ ሊቃውንቱ አመስጥሮ ቤተ ክርስቲያን ማለት እግዚአብሔር ግዕዛን ካላቸው ፍጥረታት ጋር ያለው ግንኙነት ነው። ከዚህ ምሥጢራዊ አፈታት በመነሣት የቤተ ክርስቲያን ዕድሜ በሦስት ይከፈላል። የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን ሰው ከመፈጠሩ በፊት በዓለመ መላእክት የነበረችው የመላእክት አንድነት ናት። ሁለተኛው የቤተ ክርስቲያን ዕድሜ ከአቤል ጀምሮ እስከ ሐዲስ ኪዳን መግቢያ ድረስ የነበሩ ደጋግ ሰዎች አንድነት ነው። ሦስተኛይቱና የመጨረሻይቱ ግን በክርስቶስ ደም የተመሠረተችው የክርስቲያኖች አንድነት (ማኅበረ ምእመናን) ናት እሷም የጸጋና የጽድቅ ምንጭ ናት።[4]

የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ረዥምና ምሥጢሩም የረቀቀ ሲሆን እንደ ሰማይ የመጠቀውን፣ እንደ ባሕር አሸዋ የበዛውን ይህንን የቤተክርስቲያን ታሪክ በዚህ መጣጥፍ ዘርዝረን ባንዘልቅም ከረዥሙ ባጭሩ ከሙሉ በከፊሉ ለማቅረብ እንሞክራለን።

## ቅድመ ልደተ ክርስቶስ

ቀዳማዊው አዳም ትዕዛዘ እግዚአብሔርን ከጣሰ ወዲህ በሰው እና በእግዚአብሔር መካከል የጸብ መጋረጃ ተጋረደ። ሰውና እግዚአብሔር ተለያይተው ነበር። የሰው ልጅ የአምላኩ ገጽታ ከዓይኑ ኀሊናው ጠፍቶ የተለያዩ ጣዖታት በልቦናው ሰሌዳ ላይ ተቀርጸው መፍቀሬ ጣዖት ሆኖ ለብዙ ዘመናት ኖሯል።

በዚህ የጨለማ ዘመን አምላካቸውን ፈልገው በማግኘት ከልዑለ ባሕርይ አምላክ ጋር ግንኙነት የነበራቸው ውሉደ አዳም መኖራቸው አይዘነጋም። ፈጣሪው ንጹሐ ባሕርይ አምላክ መሆኑን ዐውቆ ለቅን መንፈስ ንጹሕ መስዋዕት ለአምላኪ ያቀረበው አቤል ደግ ሥራው ቢያስገድለውም የአቤል ሃይማኖት ሳትሞት በእሱ ምትክ ወደተወለደው ሴት ተዘዋውራለች። የሴት ልጆችም ከሴት ርቀው ንጽሕ ጠብቀው በጾም በጸሎት ተጠምደው በደብር ቅዱስ ይኖሩ ነበር። በዚህም የእግዚአብሔር ልጆች ተብለው ተጠርተዋል።[5]

መላው የሰው ዘር ተካክሎ እግዚአብሔርን በበደለበት ወቅት ኖኅ በሕገ እግዚአብሔር ጸንቶ በመገኘቱ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ስምንት ራሱን በመርከብ ውስጥ ገብቶ ሲተርፍ መላው ዓለም ጠፋ።

መምለክያነ ጣዖት እንደ ዝናም ጠብታ በበዙበት ወቅት ከከለዳውያን አገር ከዑር ከተማ የታራ ልጅ አብርሃም አባቱም እርሱም ያመልኩበት የነበረውን ጣዖት አፈራረሰ። አምላኩን ፈልጎ አገኘ። ገባሬ ኩሉ አምላክ እግዚአብሔር አብርሃምን ከዘመዶቹ ተለይቶ እርሱ ወደሚያሳየው ሀገር እንዲሄድ አዘዘው። አብርሃምም ከዘመዶቹ ተለየ። እግዚአብሔርም ባረከው ዘሩንም እንደ ምድር አሸዋ እንደ ሰማይ ከዋክብት አበዛለት።

**ያንኑ አንዱን ወንጌል የሚይዙ፣ በክርስትና ስም የሚጠሩ ድርጅቶች እየበረከቱ መጥተዋል። የእኔ ይበልጥ፥ የእኔ ይበልጥ ምእመናንን ግራ ሲያጋቡ፣ ገሚሱንም በተንኮል ወጥመዳቸው ሲይዙ ይስተዋላል።**

ልጁ ይስሐቅም የአባቱን መንገድ ተከተል፣ ይስሐቅ ለያዕቆብ ያዕቆብ ለልጆቹ አስተላለፈ፤ ነቢያት የአብርሃምን መንገድ ይዘው ስለ መሲሑ መምጣት ትንቢት እየተናገሩ ሕዝቡም ከክፋት መንገድ እንዲርቅ እያስተማሩ የተስፋውን ቀን በጉጉት ይጠባበቁ ነበር።

በሌላ በኩል ደግሞ አያሌው የዓለም ሕዝብ ፈጣሬ ኩሉ ዓለም አምላክን ዘንግቶ በተለያየ የጣዖት አምልኮ ተይዞ ነበር። በብዙ አማልክት ማምለክ (ፖሊተይዝም) የዘመኑ ፋሽን ነበር። በተለይ በስፋት ተንሰራፍተው ይመለኩ የነበሩት በጥንታዊ አጠራርዋ ፋርስ የአሁኗ ኢራን የተመሠረተው የዞራስተር እምነት ኦሎምፒስ ተብሎ በሚጠራው ትልቅ ተራራ ላይ ይኖሩ የነበሩ የግሪክ አማልክት እነ ጁፒተር (የአማልክት ንጉሥ) ጁኖ (የሰማይ ንግሥት)፣ አፖሎ (የፀሐይ የመድኃኒት፣ የሙዚቃና የግጥም አምላክ)። ቬኑስ (የቁንጅና፣ የሳቅ የፍቅር አምላክ)፣ ኒፕቱን (የውኃዎች አምላክ)፣ ፕላቶ (የሲኦል አምላክ) የግሪካውያንና የሌሎችንም ስሜት በአድናቆት አውታር ወጥረው ይዘው ነበር። በተለይ ዞራስተር ለዚህ ዓለም ሁለት ፈጣሪዎች አሉት «አሁራ ማዝዳ» (የጥበብ አምላክ ከሁሉ በላይ የሆነ የዓሉም ገዥ) በዓለም ውስጥ ደግ የሆነውን ነገር ሁሉ የፈጠረ። የሰውም ፈጣሪ፣ «አንግራ ማንዩ» (ክፉ መንፈስ በዓለም ውስጥ ያለውን ክፉ ነገር ሁሉ የፈጠረ) በማለት ስለ ሁለት አማልክት ያስተምረው የነበረው የሁለት አማልክት ትምህርት በመካከለኛው ምሥራቅ የብዙ ሰዎችን ኅሊና ገዝቶ እንደነበር በታሪክ ተዘግቧል።

ግሪኮች እንደ ሰው ለመሆን ምንም ያህል ከማይቀራቸው (ሙዚቃ ከሚወዱ ፍቅር ከሚይዛቸው ሥነ ጽሑፍ ከሚያፈቅሩ) አማልክት በተጨማሪ ሔርኩለስን የመሳሰሉ ግማሽ የሆኑ አማልክቶች ነበሩአቸው። ከነዚህም ሌላ ተራ ሰዎች ከሆኑት ውስጥ እንደ አማልክት ቆጥረው የሚሰግዱላቸው ነበሩ። የኤፌሰንዋ አርጢምስና ልጅዋ ዜዋስ ለዚህ ዓይነተኛ ምስክር ናቸው።

በጥንታዊ ግብፅም አብያተ ጣዖት በብዛት ተሠርተው እንደ ነበር ታሪክ ያዘክረናል። ራስ ቅሉ የሰው አምሳል ሆኖ መላ ሰውነቱ ግን የእንሰሳ አምሳል የሆነው «ከፊኒክስ» ከብዙዎቹ መካከል ለምሳሌነት የሚጠቀስ ነው።[6]

ዓለማችን ቅድመ ልደተ ክርስቶስ የለማኝ እህል ይመስል በተለያዩ አምልኮት ውጥንቅጧ የወጣ ነበረ። በዚህ ሁሉ ውዥንብር ውስጥ ግን ፈጣሪ እውነተኛዋን መንገድ ለጥቂቶቹ ገልጾላቸው በዚህች መንገድ ይጓዙባት ነበር። እነዚህም ሕዝበ እግዚአብሔር ተብለው ይጠሩ የነበሩ የእስራኤል ልጆች ናቸው።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ከምድረ ፍልስጤምም ውጭ የነበረው የሮማ መንግሥት ፖለቲካ ደግሞ ከቅኝ ግዛቱ የተነሣ ያነገንግ ነበር።

በዚህ ወቅት ነበር በተነገረው ትንቢት፣ ባስቆጠረው ሱባዔ መሠረት ጊዜው ሲደርስ የቤተ ክርስቲያን መሠረት፣ የአሕዛብ ብርሃን የእሥራኤል ዘነፍስ ክብር መድኃኔዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ በቤተልሔም የተወለደው።

ሥርዓተ ኦሪትን ትንቢተ ነቢያትን በሚገባ እንከታተላለን ይሉ የነበረው ፈሪሳውያን በእነርሱ ኅሊና ስላልመጣ ጀርባቸውን ሰጡት፤ መሲሑ ነው ብለው ሊቀበሉትም ፈቃደኞች አልነበሩም። ምክንያቱም የጠበቁት መሲሕ ክንዱ የሚያደቅ፣ ግርማው የሚያንቀጠቅጥ፣ ሮማውያንን አባሮ አገራቸው ኢየሩሳሌምን ነፃ የሚያወጣ ኃይለኛ ጦረኛ መሲሕን ነበርና።

መሲሕ ግን የመጣው ለአንዲት ፓለስታይን፣ ለተወሰኑ ሕዝቦች ነፃነት ሳይሆን መላው የሰው ዘርን ከዲያብሎስ ባርነት ነጻ ሊያወጣ በመሆኑ በትምህርቱ የዓለም መድኃኒትና የሁሉም ጌታ መሆኑን በገሃድ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ዐሳወቀ። አይሁድም ጠሉት። ተመቅኝተውም የሐሰት ምሥክር አቁመው ከሰሱት። ለክርስቲያኖች ሁሉ ቤዛና ዐብነት ሆኖ ሰላሳ ሦስት ዓመት ከሦስት ወር በዚህች ምድር ተመላለሰ። የመጣበትን ዓላማ ለመፈጸም በማዕከለ ምድር በቀራንዮ ኮረብታ ፍቅር አገብሮት ለሰው ዘር ሁሉ ድኅነት እንደ ብራና ተወጥሮ እርቃነ ሥጋውን ተሰቀለ። ክብርት ነፍሱንም ከቅዱስ ሥጋ በገዛ ሥልጣኑ ለየ። ወደ መቃብር ወረደ። ሦስት መዓልት ሦስት ሌሊት በመቃብር ውሎ ሙስና መቃብርን አጥፍቶ በሦስተኛው ቀን ተነሣ። ከሙታን ተለይቶ በአርባኛው ቀን ሐዋርያቱ እያዩት ወደ ቀድሞው አነዋወሩ አረገ።

ሕዝበ እግዚአብሔር እሥራኤል በተለያየ ወቅት በቅኝ ግዛት ወድቀው ይማቅቁ ነበር። በ586 ቅድመ ልደተ ክርስቶስ በናቡከደነጾር መሪነት ባቢሎናውያን ኢየሩሳሌምን አጠፉ። ሕዝቡንም ማርከው ወሰዱ። ሰባ ዓመት በምርኮ ቆይተው ከተመለሱ በኋላ ጥቂት እንደቆዩ በፋርስ ተወረሩ። አሁንም እንደገና በ330 ከጌታ ልደት በፊት ግሪኮች በዚህች ምድር ላይ ቅኝ ገዥዎች ኾኑ። በመጨረሻም 63 ዓመት ከጌታ ልደት በፊት ሮማውያን ተረከቧት።[7]

## ከልደተ ክርስቶስ እስከ ትንሣኤ

ትንቢት የተነገረላቸው ሱባዔ የተቆጠረላቸው ባለተስፋዎቹ ሕዝቦች አይሁድ ትንቢተ ነብያትን መሠረት አድርገው የመሲሑን መምጣት በትጋት ነቅተው ይጠባበቁ ነበር። በተለይ የቅኝ ገዥዎቻቸው የመከራ ዱላ ጠንክር በሚልበት ወቅት ተስፋቸው ይበልጥ ያብብ ነበር። ዓላማቸው ከቅኝ ገዥዎች መዳፍ ነጻ መውጣት በመሆኑ መሲሑንም ይጠብቁት የነበረው ከቅኝ ገዥዎቻቸው ባርነት ነጻ እንዲያወጣቸው ነበር።

በዚህ የተነሣ አመለካከታቸው ለየቅል የነበረ የተለያዩ ቡድኖች፣ ተፈጥረዋል። ፈሪሳውያን የሚባሉት ክፍሎች መሲሕ እንደሚመጣና ሀገራቸው ፍልስጥኤምን ከሮም ቅኝ ግዛት የጦር ኃይል አቋቁሞ ራሱ የጦር መሪ በመሆን የሮማን የቅኝ ግዛት ቀንበር አውልቆ ጥሎ የዳዊትን ቤተ መንግሥት ያድሳል የሚል እምነትና ተስፋ ነበራቸው።

ከፈሪሳውያን ተከፍለው በሙት ባሕር አካባቢ ገዳም መሥርተው ይኖሩ የነበሩ ኤሴይ በመባል የሚታወቁት ክፍሎች ደግሞ በተዓምራት በእግዚአብሔር ኃይል ፍልስጥኤም ነጻ ትወጣለች ብለው ያምኑ ነበር።

ኤሴዎችና ፈሪሳውያን በአንዳንድ አስተሳሰብ ቢለያዩም መሲሕ መምጣቱንና የተወሰኑ ምርጥ ጉሳዎችን ብቻ እንደሚያወጣ፣ ዓለም አቀፋዊ መሲሐዊ መንግሥት እንደሚያቋቁምና እነርሱ የመንግሥቱ ባለሚሎች እንደሚሆኑ ሁለቱም ቡድኖች ያምኑ ነበር።[8] ❖

ከእርገት በኋላ፣

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

(ይቀጥላል)

1. ኪዳን ወልድ ክፍሌ መዝገበ ቃላት ገጽ 369
2. በብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ከተዘጋጀ ትምህርት የተወሰደ(ያልታተመ)
3. ኤፌ.4፥5። ይሁዳ.3
4. የቤ.ክ. ታሪክ በዓለም መድረክ ገጽ 12
5. መጽሐፈ ሄኖክ ም.2፥1–3። ዘፍ.6፥1–2።
6. ታላላቅ ሃይማኖቶች እንዴት እንደተጀመሩ ገጽ 270
7. የቤ.ክ ታሪክ ገጽ 18
8. የቤ.ክ.ታሪክ ገጽ 19

በምእመናን፣ በወጣንያን፣ በባሕታውያን እንዲሁም በፍፁማን ላይ ከቀሩት አጽዋማት ይልቅ በዓቢይ ጾም የሰይጣን ጾር ጭንቅ የሚሆንባቸው ለምንድን ነው?

1. የእኛን ጾም በሚመስል በጌታ ጾም ሰይጣን ከጌታ ጋር ተዋግቶ ነበርና ጌታም እርሱን ድል ነስቶ ያመጣውን ክብር ሰጥቶናልና ስለዚህ ነው።
2. ምእመናን በዓቢይ ጾም ከፈቃደ ሥጋ ከፈቲው ጾር (ከኃጢአት) ለመጠበቅ፣ ኃጢአትንና አጋንንትን ለመዋጋት ይጸናሉና። ስለዚህም ሰይጣን ጾሩን ያጸናባቸዋል።
3. በዓመት በዓመት በሚሆን በጌታ ጾም ከትሩፋት ወገን ላይም የሚስማማ ሥራ ሲሠሩ ጌታ ረድኤት ይሰጣልና ስለዚህ ነው።

ምንጭ – ፊልክስዮስ

ከ–መ/ር ቴዎድሮስ በየነ (ቡሬ)


## የመጽሔታችን ደንበኛ ቢሆኑ አንዲትም እትም አታልፍዎትም

| | | |
|---|---|---|
| ለክፍለ ሀገር | የዓመት | 38.40 |
| | የ6 ወር | 19.20 |
| ለአዲስ አበባ | የዓመት | 37.80 |
| | የ6 ወር | 18.70 |
| ከሀገር ውጪ | የዓመት | 24 ዶላር |
| | የ6 ወር | 12 ዶላር |

አድራሻ ለወ/ት ዓይናለም ታዬ ደመቀ
4ኪሎ ባንክ ቅርንጫፍ – የሂሳብ ቁጥር 79808
ፖ.ሣ.ቁ. 80078
ስልክ 55–00–99 Exe 46




©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# አዲስ ኪዳን...

ከገጽ 25 የዞረ

ማለት ነው። ይህም የመጨረሻና መደምደሚያ ነው። ስለ አዲስ ኪዳን በብሉይ ኪዳን ዘመን ትንቢት ተነግሯል። ይህም «እነሆ ከእስራኤል ቤትና ከይሁዳ ቤት ጋር አዲስ ቃል ኪዳን የምገባበት ወራት ይመጣል ይላል እግዚአብሔር።» ተብሎ በግልጥ ተቀምጧል። ኤር.31፥31። አዲስ ኪዳን የተመሰረተው በክርስቶስ ደም ነው። ይህም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ የቅዱስ ቁርባንን ምሥጢር ባስተማረበት ዕለት ጽዋውን አንሥቶ «ይህ ጽዋ ስለ እናንተ በሚፈሰው በደሜ የሚሆን አዲስ ኪዳን ነው።» ሉቃ.22፥20። ብሎ ባስተማረው ትምህርቱ ተረጋግጧል። አዲስ ኪዳን ከብሉይ ኪዳን ቀጥሎ በመምጣቱ የቀደመውን ኪዳን አሮጌ አስብሎ እሱ አዲስ ተብሏል። ዕብ.8፥13።

ብሉይ ኪዳን እና አዲስ ኪዳን በገዳቸው ይኸን ቢመስሉም የሁለቱም ኪዳናት አስገኚ አንድ እግዚአብሔር በመሆኑ ዓላማቸው አንድ ነው። ምክንያቱም ስለመሲህ መምጣት ነቢያት በትንቢት፣ ሐዋርያት በትምህርት ገልጠውታልና። አዲስ ኪዳን የሚነግረን የአምላክን ሰው መሆንና የማዳኑን ሥራ ነው። ይህም እንደ እንግዳ ደራሽ እንደ ውኃ ፈሳሽ ሳይሆን አስቀድሞ ገና መሲሁ ሳይመጣ በፊት በኦሪትም በነቢያትም የተነገረ ነው። ፊልጶስ ናትናኤልን «ሙሴ በሕግ ነቢያትም ስለ እርሱ የጻፉትን የናዝሬቱን ኢየሱስን አግኝተነዋል።» ዮሐ.1፥46 ያለው ለዚህ ነው። ጌታም ከትንሣኤው በኋላ በኤማሁስ ጐዳና ለሉቃስና ለቀለዮጳ፣ ከሙሴና ከነቢያት ሁሉ ጀምሮ ስለ እርሱ በመጻሕፍት ሁሉ የተጻፈውን ተርጉሞላቸዋል። ሉቃ.24፥27።

ብሉይ ኪዳን ለአዲስ ኪዳን አምሳልና መርገፍ ነው። ብሉይ ኪዳን ንባብ ሲሆን አዲስ ኪዳን ደግሞ የብሉይ ኪዳን ትርጓሜ ነው። ብሉይ ኪዳን ለአዲስ ኪዳን መነሻ፣ አዲስ ኪዳን ደግሞ ለብሉይ ኪዳን መድረሻ ነው። አዲስ ኪዳንን ለማስተማር ከብሉይ ኪዳን ጥቅስ ይጠቀሳል። ብሉይ ኪዳንን ለመቀበል ደግሞ ፍጻሜው አዲስ ኪዳን ያስፈልጋል። ከዚህም የምንረዳው ብሉይ ኪዳን ያለ አዲስ ኪዳን፣ አዲስ ኪዳን ያለ ብሉይ ኪዳን ጐደሎ መሆናቸውን ነው። ምክንያቱም ብሉይ ኪዳንን ያላወቀ ሰው አዲስ ኪዳንን ማወቅ አይችልምና።

ለምሳሌ ሙሴ በኦሪቱ ለወገኖቹ ለእስራኤል «አምላክህ እግዚአብሔር ከወንድሞችህ እንደ እኔ ያለ ነቢይ ያስነሣልሃል እርሱንም ታዳምጣለህ» ዘዳ.18፥15 ብሎ የተናገረው ለኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ይህንንም ማረጋገጥ የምንችለው በአዲስ ኪዳን ነው። ይህንንም ቅዱስ እስጢፋኖስ በስብከቱ «እግዚአብሔር ከወንድሞቻችሁ እንደ እኔ ያለ ነቢይ ያስነሳላችኋል፤ እርሱን ስሙት ያላቸው ሙሴ ነው። የሐዋ.7፥37 በማለት መስክሯል። በዚህ ዓይነት ይህን የመሳሰሉ አያሌ ጥቅሶችን ለማገናዘብ ያህል ማውጣጣት ይቻላል።

ሀ. «በአንተና በሴቲቱ መካከል በዘርህና በዘርዋ መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ፣ እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል» ዘፍ.3፥15 ይላል። ይህንንም የተናገረው እግዚአብሔር ነው። ኦሪቱ አዳምንና ሔዋንን ያሳሳተው እባብ መሆኑን ይነግረናል። ይህም እባብ ዲያብሎስ መሆኑን የምናረጋግጠው በአዲስ ኪዳን ነው። ራእ.20፥2 አዲስ ኪዳኑም ቢሆን «የቀደመውንም እባብ ዘንዶውን እርሱም ዲያብሎስና ሰይጣን የተባለውን ያዘው።» የሚለውን ለማረጋገጥ የግድ ወደ ኦሪቱ መለስ ብሎ መመልከት ያስፈልጋል። እንግዲህ በጥቅሱ እንደተቀመጠው የእባቡን ራስ ይቀጠቅጣል የተባለለት የዲያብሎስን ሥራ ለማፍረስ መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ ከሌለባት ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም የተወለደው ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን አዲስ ኪዳን ያረጋግጥልናል። ገላ.4፥4፣ 1ኛ ዮሐ.3፥8።

ሐ. በኦሪት ዘሌዋውያን ምዕ. 1፥10 ላይ «ሰው ።በግ ወይም ከፍየል መንጋዎቹ አንዱን ለሚቃጠል መሥዋዕት ማቅረብ ቢፈልግ ምንም ነውር የሌለበት ተባዕት ይሁን» ይላል። ይህም መሥዋዕት ነውር የሌለበት መኾኑ ለክርስቶስ ምሳሌ መኾኑን ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ በመልእክቱ «ነውርና እድፍ እንደሌለው እንደ በግ ደም በክቡር የክርስቶስ ደም እንደተዋጃችሁ ታውቃላችሁ።» በማለት ገልጦታል። 1ኛጴጥ.1፥18።

ሠ. የልዑል እግዚአብሔር ካህን እና የሰላም ንጉሥ መልከ ጼዴቅ የክርስቶስ ምሳሌ ነው። ዘፍ.14፥18፣ መዝ.119፥4፣ ዕብ.7፥1–3። «አባትና እናት የትውልድም ቁጥር የሉትም ለዘመኑም ጥንት ለሕይወቱም ፍጻሜ የለውም ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ልጅ ተመስሎ ለዘላለም ካህን ሆኖ ይኖራል።» የተባለለት መልከ ጼዴቅ ኅብስትና ወይን ለአብርሃም ማቅረቡ ጌታ በዕለተ ዓርብ ለቆረሰውና ላፈሰሰው ሥጋውና ደሙ ምሳሌ ነው። ማቴ.26፥26።

ረ. በብሉይ ኪዳን የማመን ምልክት የነበረው ግዝረት የጥምቀት ምሳሌ ነው። ዘፍ.17፥10። ቅዱስ ጳውሎስ ለቁላስይስ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ «የሥጋንም ሰውነት በመገፈፍ፣ በክርስቶስ መገረዝ በእርሱ ሆናችሁ ደግሞ ተገረዛችሁ፤ በጥምቀትም ከእርሱ ጋር ተቀበራችሁ።» በማለት የገለጠው ምሳሌነቱን ሲናገር ነው። ቆላ.2፥11

ሰ. አብርሃም ስለ ይስሐቅ ፈንታ የሰዋው በግ ስለ አዳም ተላልፎ በመልዕልተ መስቀል ለተሰዋው ክርስቶስ ምሳሌ ነው። ዘፍ.22፥13 «በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይ ጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።» ዮሐ.3፥16።

ሸ. የሙሴ ወገኖቹን ከግብፅ ባርነት ነፃ ማውጣት ክርስቶስ የአዳም ልጆችን ከሰይጣን ተገዢነት ከሲኦል ባርነት ነፃ የማውጣቱ ምሳሌ ነው። ዘጸ.7፥6፣ ኤፌ.2፥13።

ቀ. እሥራኤል ዘሥጋ ቀይ ባህርን መሻገራቸው የጥምቀት፣ የተመገቡት መንፈሳዊ ምግቧ የሥጋ ወደሙ፣ ውኃ ያፈለቀው ድንጋይ የክርስቶስ ምሳሌዎች ናቸው። ይህንንም ጥሩ አድርጐ የተረጐመው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ነው። ዘጸ.17፥6፣ 1ኛቆሮ.10፥1።

ከዚህም ሌላ ይኸንን የመሳሰሉ ጥቅሶች ሁሉ የሚያስገነዝቡን ብሉይ ኪዳን ለአዲስ ኪዳን አምሳልና መርገፍ መሆኑን ነው። ✣

(ይቀጥላል።)



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

## ትምህርት ይሰጥ

አንዳንድ ሰዎች የሙጥኝ ብለው የያዝዋቸው ከቤተ ክርስቲያን ትምህርት ጋርም የማይሄዱና የሚቃረኑ ልማዶችና እምነቶች አሉ። እነዚህም ቃለ እግዚአብሔርን ካለመስማትና ከቤተ ክርስቲያን ከመራቅ የሚመጡ ናቸው። ከነዚህም አንዱ እና ዋንኛው ውቃቢ አምላክ ወይም በሌላ አባባል የአባት የእናቴ አምላክ (ውቃቢ) የሚባለው ነው። በመሠረቱ ቤተ ክርስቲያን የምታስተምረው ሁሉን በፈጠረና ማድረግ በሚቻለው እግዚአብሔር መታመንና በእርሱም መጽናትን ነው። ነገር ግን አንዳንድ ሰዎች ይህንን ካለመረዳት ባለ ውቃቢ ነኝ፣ ዛር ተነሣብኝ፣ ወዘተ. እያሉ ቀን ወስነው እንዲያውም በቅዱሳን መታሰቢያ ዕለታት የሚያደርጉት ሥርዓትና ማጓራት እየበዛ መጥቷል። በጣም የሚያሳዝነው ደግሞ፣ እነዚሁ ሰዎች «ክርስቲያኖች ነን» ብለው ሲናገሩና አልፎ አልፎ ቤተ ክርስቲያን መጥተው እንደነገሩ ተሳልመው ሲመለሱ ማየታችን ነው። እንዲያውም አንዳንዶቹ በቤተክርስቲያን የተለያዩ ክፍሎች (ሰበካ ጉባዔ በመመረጥ) ሲያገለግሉ ይታያሉ። ይሁን እንጂ በመጽሔትም ሆነ በመድረክ ይህ ነገር በፍጹም ትክክል እንዳልሆነ በቂ ትምህርት አልተሰጠም እና ይታሰብበት። ሌላው ደግሞ ከሥራ አጥነት መብዛትም የተነሣ ሊሆን ይችላል የጠንቋዮች ቁጥር እየበዛ ነውና ሕብረተሰቡ አንድ ነገር በተነሣ ቁጥር ወዲያና ወዲህ ከመወላወል እምነቱን ዐውቆ ሊጸና ያስፈልገዋል። በዚህም ላይ በቂ ትምህርት ቢሰጥ መልካም ነው።

ዶ/ር መዝገቡ መርዕድ – ምስ.ጎጃም–ቢቸና

## ስም ብቻ ምን ሊጠቅመኝ

መጠሪያ ብቻ ከሆነኝ – እኔ ክርስቲያን መባሌ፣
በግብሬ ካላሣየሁት – ካልተዋሐደ ከአካሌ፣
በጨለማ መቅረዝ ሆኖኝ – እግሬን ከእንቅፋት ካላዳነ፣
ጌታዬ በኔ ካልከበረ – ስሙ በኔ ካልገነነ፣
ሻማ ሆኜ ካላበራሁ – ጨለማ ለዋጠው ወገኔ፣
ስሙ ብቻ ምን ሊጠቅመኝ – ምን ሊሠራልኝ ነው ለኔ?
በአርባ ቀኔ ስጠመቅ – ክርስቲያን ተብዬ ልጠራ፣
በእምነት ዳብሬ እንዳድግ – መልካም ፍሬን እንዳፈራ፣
ሥነ–ምግባሬ መጠነቁን – እንዲያሳይልኝ አጉልቶ፣
ክርስትናዬን እንዲናገር – በደረስኩበት ሁሉ ገብቶ
የተቀበልኩት ልጅነት – በእኔነቴ ዙሪያ አብርቶ፣
ለዚህ ነበር ምክንያቱ – በጥምቀት ክርስቲያን መሆኔ፣
በጠበሉ ነጽቼ – ልጁ የተባልኩት እኔ።
በአነጋገር በሥራዬ – ክርስትናዬን ካላሣየሁ፣
ጌታዬ በሰጠኝ መክሊት – አትርፌበት ካልተገኘሁ፣
እንደተዘናጋሁ ካለቀ – ከተጨረሰ ዘመኔ፣
ክርስቲያን መባሌ ምን ሊረባኝ – ምን ሊጠቅመኝ ነው ለእኔ?!

ሳህሉ ወንድሙ

ደ/ፀ/ቁስቋም ማርያም ሰንበት ት/ቤት – ጎንደር

## ሥነ ግጥም

## እንደ አባቶቻችን

በቀደመችዋ በተዋሕዶ መንገድ፣
እንደ አባቶቻችን በጽናት እንሂድ፣
ምግባርን ተላብሰን ፍቅርን ተጐናጽፈን፣
ነውር ሳይኖርብን ትሕትናንም ይዘን፣
እንኑር እንደ ጥንቱ እንደ አባቶቻችን።

ፍቅርተ ማርያም

(አሰላ ደ.መ.ቅ.ጊዮርጊስ ሰ/ት/ቤት)


## ሊለመድ የሚገባው!

በደሴ ከተማ የመንበረ ፀሐይ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን የዓምደ ሃይማኖት ሰንበት ትምህርት ቤት ተማሪ ዎችና ሌሎች የሚተባበሯቸው ወጣቶች እየሠሩት ያለው ሥራ ደስ የሚያሰኝ ነው። ይኸውም በአካባቢው ለሚገኙ የመንግሥት ሠራተኞች ለ6 ወራት ያህል በየመሥሪያ ቤቱ እየዞሩ በተልእኮ ትምህርት በማስተማር ብዙ ወጣቶችን ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲመጡ አድርገዋል። በዚህም ከእናት ቤተ ክርስቲያናቸው ርቀው የነበሩ ወጣቶች ተመልሰ ዋል። እናም ይህ ተግባራቸው ሊበረታታና ሊቀጥል የሚገባው ሲሆን ሌሎቻችንም እንደዚህ ዓይነቱን የተቀደሰ ተግባር ልንለምድና ልንጠቀምበት ያስ ፈልጋል።

ፀደይ ስምረት ወ/ኢየሱስ

ከሠናይ አማተር ጋዜጠኞች ክበብ

ደሴ



ዋጋው 3 ብር ብቻ

በንግድ ማተሚያ ድርጅት ታተመ

©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

©ማኅበረ ቅዱሳን

ይህን መጽሔት ያለ ማኅበረ ቅዱሳን ፈቃድ በከፊልም ሆነ በሙሉ ማሳተም ፣እንዲሁም በማንኛውም መልኩ ለሽያጭ ማዋል በህግ የተከለከለ ነው፡፡